በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

# ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ በየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት

በ

ራሔል ቶላ

ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ በየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ
የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

በ

ራሔል ቶላ

ነሐሴ 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ-ምረቃ መርሐ-ግብር

# ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና፣

# በጉለሌ ክፍለ ከተማ፣ በየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት

# በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት

የፈተና  ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

አማካሪ፡- ደረጀ ገብሬ (ረ/ፕ) ቀን ________________ ፊርማ _________

ፈታኝ፡- ጌታቸው እንዳላማው (ዶ/ር) ቀን ________________ ፊርማ _________

ፈታኝ፡- ግርማ ገብሬ (ዶ/ር) ቀን ________________ ፊርማ _________

# ምስጋና

ጀምሮ መጨረስ ከባድ በሆነበት ዓለም ውስጥ ጅማሬን አበርትቶ፣ አቅምና ጤና ሠጥቶ ጥናቴን ላስጨረሠኝ ለልዑል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር እና ምስጋና ይሁን፡፡

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ጊዜያቸውን ሰውተው ፅሁፉን በማረም፣ ጠቃሚ አስተያየቶችን እና መረጃዎችን በመስጠት ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለመምህሬ እና ለአማካሪዬ ለአቶ ደረጀ ገብሬ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ ፍቃደኝነታቸውን ለገለፁልኝ ለየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን እና መረጃዎችን ለመሰብሰብ በጠየኳቸው ጊዜ ለተባበሩኝ ተማሪዎች እንዲሁም ትምህርቱን በማስተማር፣ ፈተናውን በመፈተን እና በማረም ላገዙኝ መምህራን መምህርት አስራደች አንበርብር፣ መምህር ሲሳይ ቴሌ፣ መምህርት አዱኛ መኮንን ከዚህም ባለፈ በሞራል ሲያበረታቱኝ ለነበሩት የየካቲት 12 መሠናዶ ትምህርት ቤት መምሕራን ሁሉ ከልብ የሆነ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የትምህርት ዕድሉን ላመቻቸልኝ የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ እና የምርምር ማካሄጃ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የፅሁፍ መጠይቁን በመገምገም እና ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለዶ/ር ግርማ ገብሬ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም መረጃዎችን ከበይነ መረብ በመፈለግ፣ በማበረታታት እና ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በመስራት ለተባበረኝ ባለቤቴ እሸቱ ብሩ ይትባረክ እንዲሁም ውድ ጊዜያችሁን ለተሻማሁባችሁ፣ ይህንንም ለተረዳችሁኝ ውድ ልጆቼ አትናቴዎስ እሸቱ እና ሚኪያስ እሸቱ በተለይም ልቦለዶችን ወደ ኮምፒውተር ስገለብጥ በማንበብ ለረዳኸኝ ልጄ ሚኪያስ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# ማውጫ

**ርዕስ** **ገፅ**

ምስጋና…………………..……………………………………………….…… I

ማውጫ…………………………………………………………..……….....… II

አህፅሮተጥናት……………………………...………………………..…… VI

**ምዕራፍ አንድ**

መግቢያ………………………………………………………….………… 1

1.1. የጥናቱ ዳራ………………………………………………………….…. 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት.............................................................. 3

1.3. የጥናቱ አላማ……………………………………………………..…...… 5

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ……………………………………………….……….. 5

1.5. የጥናቱ ወሰን…………………………………….…………….…… 5

**ምዕራፍ ሁለት**

ክለሳ ድርሳናት …………………………..………………………….……7

2.1. የመፃፍ ክሂል ምንነት፣ አስፈላጊነት እና አቀራረቦች………….………….. 7

2.1.1. የመፃፍ ክሂል ምንነት………………………………………….………… 7

2.1.2. የመፃፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት……………………………..…….7

2.1.3. የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች……………………………….....…9

2.2. ቋንቋን በማስተማር ረገድ የስነፅሁፍ ፋይዳ………………………………13

2.3. ስነፅሁፍ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ፋይዳ ………………………. 15

2.4. ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ……….....…16

2.5. የስነፅሁፍ ስራዎችን የመምረጫ መስፈርቶች…………………….……… 17

2.6. የቋንቋን ትምህርት መሰረት ያደረገ አቀራረብ…………………….……… 20

2.7. በረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ........................................................22
2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........................................................27

## ምዕራፍ ሶስት

የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ........................................................33
3.1. የጥናቱ ንድፍ........................................................33
3.2. የተጠኚዎች አመራረጥ........................................................34
3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ........................................................34
3.2.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ ........................................................34
3.2.3. የተማሪዎች አመራረጥ........................................................34
3.3. በረዥም ልቦለድ መፃፍን የማስተማሪያ/የማሰልጠኛ ማቴሪያል......... 35
3.3.1. የቅንጫቢዎች አዘገጃጀት........................................................35
3.3.2. የመልመጃዎች አዘገጃጀት........................................................ 36
3.4. የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን አሰልጣኝ መምህር አመራረጥ............37
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች........................................................38
3.5.1. ምልከታ........................................................38
3.5.2. ፈተና........................................................ 38
3.5.2.1. የፈተና አዘገጃጀት........................................................ 39
3.5.2.2. የፈተና አስተራረም........................................................ 39
3.5.3. የፅሁፍ መጠይቅ........................................................ 40
3.6. የመረጃ አተናተን........................................................41

## ምዕራፍ አራት

የመረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ ........................................................42
4.1. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ....................42
4.2. ከፈተናዎች ውጤት የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ........44
4.2.1. ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ................................44

4.2.2. ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የተገኙ
መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ…………………..……………46
4.3. ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ……..…..49

## ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ እና አስተያየት ………………………………………………..……… 65
5.1. ማጠቃለያ……………………………………………………..……... 65
5.2. አስተያየት…………………………………………………..……... 66
ዋቢ ፅሁፎች ………………………………………………………..…..…... 68
አባሪዎች……………………………...….……………………………….…... 74
ማረጋገጫ ……………………….………..……………………………....…...138

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ አንድ ……………………………………………………..……………...36

ሰንጠረዥ ሁለት ……………………………………….……………….………...  39

ሰንጠረዥ ሶስት …………………………………………..……………………... 45

ሰንጠረዥ አራት ……………...………..…………………………………………...46

ሰንጠረዥ አምስት………………………………………………………………... 47

ሰንጠረዥ ስድስት……..…..…………………………………………………... 48

ሰንጠረዥ ሰባት……..……..………………………………………………...51

ሰንጠረዥ ስምንት…..…………..…………………………………………...52

ሰንጠረዥ ዘጠኝ……………………………………………………………...54

ሰንጠረዥ አስር……………………………………………………………... 56

ሰንጠረዥ አስራ አንድ……….……………………………………………... 57

ሰንጠረዥ አስራ ሁለት…………………………………………………... 60


## የግራፍ ማውጫ


ግራፍ አንድ ……………………...…………………………………………... 49

ግራፍ ሁለት፡-……………...……………………………………………...58

ግራፍ ሶስት…………………………………….………………………………..59

# አህፅሮተጥናት

*የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና መፈተሽ ነው። ተጠኚዎች በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኘው በየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት የሚማሩ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠው አመቺ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ነው። ጥናቱ ሙከራዊ በመሆኑ ለዚሁ ያመች ዘንድ ካሉት የመማሪያ ክፍሎች ሁለቱን በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ በመምረጥ የ$11^{07}$ ተማሪዎች የሙከራ ቡድን ሲሆኑ የ$11^{18}$ ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ሆነው ተመርጠዋል። የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ሲሆኑ እነሱም ምልከታ፣ ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው። ከምልከታ የተገኘው መረጃ የተሰበሰበው የረዥም ልቦለድ ቁርጭኞችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን ሲለማመዱ የማስተማር ሂደቱን በመመዝገብ ነው። ሌላው ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ በመሆን ያገለገለው ፈተና ሲሆን ቅድመ ሙከራ እና ድህረ ሙከራ ፈተናዎች ለሁለቱም ቡድኖች ተሰጥተዋል። ቅድመ ትምህርት ፈተና ከወሰዱ በኋላ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች ለአንድ ወር ያህል በረዥም ልቦለድ ቁርጭኝ አማካነት የመፃፍ ክሂልን እንዲማሩ ተደርጓል። ከዚያም ውጤታቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል። በመጨረሻም የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን መማር የሚኖረውን አስተዋፅ እንዲገልፁ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል። መጠናዊ እና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ከምልከታ፣ ከፈተና እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነዋል። የቅድመ ትምህር ፈተናው ውጤት በቲ ቴስት ቀመር ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.56 ሲሆን ይህ የሚያሳየው ሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ትምህርት ፈተና ጉልህ ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ነው። የድህረ ትምህርት ፈተናው የቲ ቴስት ውጤት ደግሞ 6.56 ሲሆን ሁለቱ ቡድኖች ጉልህ ልዩነት አሳይተዋል። ይህ የሚያሳየው ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ሚና እንዳለው ነው። ከምልከታው የተገኘው መረጃ ተማሪዎች አዎንታዊ ክንውን እንዳሳዩ ጠቁሟል። እንዲሁም በሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተሞላው መጠይቅ እንደሚያስረዳው ተጠኚዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን መማር ለክሂሉ መዳበር አስተዋፅኦ እንዳለው ገልፀዋል። ከተገኘው ውጤት በመነሳት በረጅም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ማስተማሩ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስተያየት ተሰንዝሯል።*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የመፃፍ ክሂል ትምህርት ከቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች አንዱ ነው፡፡ የመፃፍ ትምህርት ዓላማም ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ጠብቀው ሀሳባቸውን በፅሁፍ አቀናብረው እንዲገልፁ ማስቻል እንደሆነ ተስፋዬ (1981፣59) ይገልፃሉ፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች ተፈላጊውን ችሎታ አዳብረዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ ይህን ሀሳብ በሚመለከት ማረው (1996፣ vi) አምሳሉ እና ደምሴ (1982)ን ጠቅሰው የገለፁት በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመፃፍ ክሂል ትኩረት እንደተነፈገውና የተማሪዎችም የመፃፍ ችሎታ ደካማ እንደሆነ ነው፡፡ ባየ (1997፣ xxvi) እና ተስፋዬ (1986፣ 9-10) ተማሪዎች ሀሳብን በተስካከለ ዓረፍተ ነገር የመግለፅ ብቃት እንደሌላቸው እና በዚህም የተነሳ ትምህርታቸውን አጠናቀው በስራ አለም ሲሰማሩ የተለያዩ ፅሁፎችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ችሎታ የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች ከተካሄዱ ረዥም ጊዜ ያስቆጠሩ ቢሆንም ችግሩ አሁንም ያለ ስለመሆኑ በቅርብ ጊዜ የተደረጉ የምርምር ስራዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ የአምላክሥራ (2008) እንደሚገልፁት ተማሪዎች ድርሰት ሲፅፉ በርካታ ስህተቶችን እንደሚፈፅሙ ጠቅሰዋል፡፡ እነዚህ ችግሮች የቃላት ድግግሞሽ፣ የሆሄያት ግድፈት፣ ተገቢ ያልሆነ የሆሄያት ቅርጽ፣ ኢ-መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የመስተዋድድ አገባብ ስህተት፣ የዓረፍተ ነገር ስምምነት ስህተት ፣ የቃላት አጠቃቀም ስህተት እና የሥርዓተነጥብ አጠቃቀም ስህተት መሆናቸውን በጥናታቸው አረጋግጠዋል፡፡

ተስፋዬ (1986፣ 9) እና የአምላክሥራ (2008፣77) ለዚህ ችግር መከሰት በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ከነዚህ ችግሮች መካከል የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት፣ የማስተማር ስልት፣ የክፍለ ጊዜ መብዛት የተማሪዎች ቁጥር መብዛት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የተማሪዎች የመፃፍ ክሂል እንዲዳብር ከሚያደርጉ የማስተማሪያ ስልቶች መካከል ስነፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት መጠቀም ተጠቃሽ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ እንደ Shazu (2014፣29) አገላለፅ ቀደም ባሉት የቋንቋ ማስተማሪያ ስነዘዴዎች ስነፅሁፍን

ለቋንቋ ትምህርት መጠቀም ትኩረት ተነፍጎት የቆየ ጉዳይ ቢሆንም ከ1980ዎቹ በኋላ ግን ትልቅ ዋጋ ተሰጥቶታል።

እንደ Collie እና Slater (1987፣ 4) አገላለፅ ምንም እንኳን ስነፅሁፍን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ቢታወቅም በሌላ በኩል ይህን የሚቃወሙ እንዳሉ ይጠቁማሉ። Mckay (1982፣ 529) እንደሚገልፁት ተከራካሪዎች የሚያቀርቧቸው ሶስት የመከራከሪያ ሀሳቦች ናቸው። የመጀመሪያው፣ ቋንቋን የማስተማር ዋና ዓላማ የቋንቋውን ሰዋስው ማስተማር ነው። የስነፅሁፍ የቋንቋ መዋቅር ደግሞ ውስብስብ እና ለየት ያለ በመሆኑ ሰዋስውን ለማስተማር ያለው አስተዋፅኦ ኢምንት ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው የመከራከሪያ ሀሳብ ደግሞ ስነፅሁፍን ማጥናት ለተማሪዎች እውቀት እና በስራ አለም ለሚከውኑት ተግባር ምንም አስተዋፅ አያበረክትም ይላል። ሶስተኛ ሀሳብ ስነፅሁፍ ሁል ጊዜ የሚያንፀባርቀው የአንድን ማህበረሰብ ውስን ባህል ነው። ያንን ባህል የማያውቁ ተማሪዎች ትምህርቱ አስቸጋሪ እና ከባድ ይሆንባቸዋል የሚሉ የመከራከሪያ ሀሳቦች ናቸው። በሌላ በኩል እነዚህ ወገኖች የስነፅሁፍ ቋንቋ ከዘወትራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ያፈነገጠ በመሆኑ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ ተማሪዎች እንጂ በዝቅተኛ የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች አያገለግልም የሚል አመለካከት አላቸው።

ምሁሩ ይህ የተከራከሪዎች ሀሳብ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ስነፅሁፍን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር ከተማሪዎች እድሜ እና የክፍል ደረጃ ጋር ተገናዝቦ በስፋት መዘውተር አለበት ይላሉ። አክለውም ስነፅሁፍን እንደማስተማሪያ መሳሪያ መጠቀም መሰረታዊ ክሂሎችን (ማዳመጥ፣መናገር፣ ማንበብና፣ መፃፍ) ከዚህም ባለፈ ሰዋስው፣ ቃላት፣ ድምፀት ለማስተማር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት አገልግሎት ላይ መዋል እንዳለበት ይመክራሉ።

በስነፅሁፍ አማካይነት ቋንቋ ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ ሌሎች ምሁራንም ሀሳብ ሰንዝረዋል። ከነዚህም ውስጥ ፈቃደ (1991፣111) ‹‹ የቋንቋ ትምህርት በስነፅሁፍ ስራዎች አማካይነት ማከናወን የራሱ አላማዎች፣ ጠቀሜታዎች፣ ብርታቶችና ድክመቶች አሉት። ዓላማዎቹን በተግባር ለማዋል የሚደረግ ጥረት ተማሪዎቹን የማስተማር ዋና ትኩረት ግን በተመረጡ የፈጠራ ፅሁፎች አማካይነት ልዩ ልዩ የቋንቋ ክሂሎችን ማስተማር ነው ›› በማለት ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ትምህርት ማዋል ክሂሎችን ለማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቁመዋል። በድሉ (2007፣ 16) ስነፅሁፍን

በቋንቋ ትምህርት መጠቀም የተማሪዎችን የማንበብ፣ የማዳመጥ፣ የመናገር እና የመፃፍ ክህሎት ለማዳበር ፋይዳው የጎላ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

ይህን በተመለከተ Collie እና Slater (1987፣5-6) በበኩላቸው ተማሪዎች በስነፅሁፋዊ ስራዎች ቋንቋን ሲማሩ ግላዊ ተሳትፏቸውን በከፍተኛ ደረጃ የማጎልበት ሀይል ያገኛሉ፡፡ ራሳቸውን የድረጊቱ ተሳታፊ አድርገው እንዲመለከቱ ስለሚያደርጋቸው የታሪኩን ድባብ ይፈጥራሉ፡፡ የፈጠራ ስራው አስደሳች ከሆነ ተማሪዎችን ወደ ራሱ አለም ያስገባል፡፡ የቀደመ እውቀታቸውንም እንዲጠቀሙ ያደርጋል በማለት የስነፅሁፍ ሚና ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የፈጠራ ስራዎች ተማሪዎችን ተሳታፊ የሚያደርጉ በመሆናቸው ይህን መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ በፅሁፍ የሚመለሱ መልመጃዎችን በማቅረብ የተማሪዎችን የመፃፍ ክህሎት ማዳበር ይቻላል፡፡

ከምሁራኑ አስተያየት መረዳት እንደሚቻለው ስነፅሁፋዊ ስራዎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ የጥበብ ዘውግ አግባብነት ባለው መልኩ የመፃፍ ክሂልን ማስተማር ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከላይ የቀረቡትን የምሁራን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሙከራዊ ጥናት በማካሄድ ያረጋግጣል፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሰረታዊ ጥያቄዎች ይመልሳል፡፡

- ረዥም ልቦለድ ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግርን ለማቃለል ሚና አለው?
- መፃፍን በረዥም ልቦለድ አማካይነት የተማሩ ተማሪዎች ውጤት በረዥም ልቦለድ ካልተማሩት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ይሆናል?

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህን ጥናት ለማካሄድ በምክንያትነት ከሚቀርቡ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አጥኚዋ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን በማስተማር ሂደት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር ያለባቸው መሆኑን አስተውላለች፡፡ በሌላ በኩል ስነፅሁፋዊ ምንባቦችን ለማንበብ እና ስነፅሁፍን መሰረት አድርገው የሚዘጋጁ መልመጃዎችን ለመስራት የመምህር ግፊት የማይፈልጉ በመሆናቸው ተግባራቱን በፍላጎትና በራስ ተነሳሽነት ሲያከናውኑ ተመልክታለች፡፡ ስነፅሁፋዊ ስራዎች ባልሆኑት

ላይ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው የመስራትም ሆነ የማንበብ ፍላጎታቸው አናሳ መሆኑን አስተውላለች፡፡ እንዲሁም መማሪያ መፅሀፉን መሰረት በማድረግ አልፎ አልፎ በክፍል ውስጥ በሚዘጋጀው የስነፅሁፍ ዕለት ተማሪዎች ከፍተኛ ዝግጅት አድርገው ስነፅሁፋዊ ስራዎችን አንብበው፣ ፅፈው፣ የሰሟቸውንም ለማቅረብ ተዘጋጅተውና በክፍል ውስጥ የሚቀርቡትን ስራዎች ለማድመጥ በከፍተኛ ፍላጎት ተነሳስተው ይመጣሉ፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ስነፅሁፋዊ ስራዎች እንዲያነቡ፣ እንዲፅፉ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ ስለሚያደርግ የቋንቋ ክሂላቸውን እንደሚያዳብር መገመት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ይህንን በስራ ዓለም ያየችውን ትዝብቷን ወይም ምልከታዋን በተጨባጭ በምርምር፣ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ማረጋገጥ ስለፈለገች ይህንን ጥናት እንድትሰራ አነሳሽ ምክንያት ሆኗታል፡፡

ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ስነፅሁፍ ለቋንቋ ትምህርት የሚኖረውን አስተዋፅኦ በሚመለከት የተካሄዱ ጥናቶችን ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ የተወሰኑ ጥናቶችን ለማግኘት ተችሏል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዘመንፈስ (1991)፣ ጌትነት (2001)፣ ታዬ(2002)፣ ነብዩ (2005) ጥናቶች ይገኙበታል፡፡ በእነኚህ አጥኚዎች የተካሄዱት የምርምር ስራዎች ስነፅሁፍ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ፋይዳ የመፈተሽ አላማ ቢኖራቸውም ትኩረታቸው ግን የስነፅሁፍ ስራው የቀረበበት ስነዘዴ (ፈጠራዊ ዘዴ) ላይ ነው፡፡ ጥናቶቹ ለሁለቱም ቡድኖች (ለቁጥጥር እና ለሙከራ ቡድኑ) ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመስጠት እና በተለያዩ ዘዴዎች ማለትም በነባሩ እና በአዲሱ (ፈጠራዊ ዘዴ) በማስተማር የተካሄዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በአጥኚዋ አመለካከት የጥናቶቹ ትኩረት ስነዘዴው ላይ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ለሙከራ ቡድኑ ብቻ በመስጠት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና ይፈትሻል፡፡ በዚህ መልኩ የተሰራ ጥናት ባለመኖሩ ጥናቱን ለማካሄድ ተጨማሪ ምክንያት ሆኗል፡፡

በአጠቃላይ አጥኚዋ፣ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር ያለባቸው መሆኑን እንዲሁም ስነፅሁፋዊ ስራዎችን መሰረት በማድረግ በሚቀርቡ ተግባራት ላይ ያላቸውን ተሳታፊነት በማስተማር ልምዷ ተገንዝባለች፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመፈተሽ ወይም በስራ ልምድ የተገነዘበችውን ለማረጋገጥ በተለያዩ መስፈርቶች በተመረጡ የረዥም ልቦለድ ቅንጫዎች አማካይነት ሙከራ የሚካሄድባቸውን ተማሪዎች በማስተማር የመፃፍ ክሂላቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ የተካሄደ ነው፡፡

## 1.3. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዓላማ ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ሲሆን የሚከተሉትን ንዑሳን ዓላማዎች ይይዛል፡፡

- ረዥም ልቦለድ ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግርን ለማቃለል ያለውን አስተዋጽኦ መፈተሽ
- መፃፍን በረዥም ልቦለድ አማካይነት የተማሩ ተማሪዎች ውጤት በረዥም ልቦለድ ካልተማሩት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ

**መላምት፡-** ስነፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት መጠቀም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ከፍ ለማድረግ ሚናው የጎላ እንደሆን በጥናቱ ዳራ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም የምሁራኑን ሀሳብ መነሻ በማድረግ የሚከተለው አቅጣጫ አመላካች መላምት ቀርቧል፡፡

በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች ውጤት ይሻሻላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ትኩረት ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን አስተዋፅኦ የሚፈትሽ እንደመሆኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ዙሪያ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

1. የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ በመማሪያ እና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም በመምህራን ስልጠና ወቅት በረዥም ልቦለድ አማይነት የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ሊደረግ የሚገባው ትኩረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያስችላል፡፡
2. መምህራን ረዥም ልቦለድን ተጠቅመው ቋንቋን ሲያስተምሩ ትምህርቱን እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ጥቆማ እንደሚሰጥ ይገመታል፡፡
3. ወደፊት በዚሁ ርዕስ ዙሪያ ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ተተኳሪ በሆነው ክልል፣ ክፍለ ከተማ፣ የክፍል ደረጃ እና ትምህርት ቤት የተወሰነ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ፣ በጉለሌ ክፍለ ከተማ በሚገኘው በየካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት ላይ ሲሆን ተተኳሪ የሆነው የክፍል ደረጃም 11ኛ ክፍል ሆኖ ረዥም ልቦለድ ለመፃፍ ክሂል መዳበር ያለውን ሚና በሙከራ ለማረጋገጥ ያለመ ነው፡፡

የጥናቱ ትኩረት ረኸርም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር እንዴት መቅረብ እንዳለበት በዘርፉ ያሉ ምሁራንን ንድፈ ሀሳባዊ ገለፃዎች መሰረት በማድረግ እና ቅንጫቢዎችን በመምረጥ ለሙከራ ቡድኑ ትምህርቱን በማቅረብ ረኸርም ልቦለድ የተማሪዎቹን የመፃፍ ክሂል ማዳበር አለማዳበሩን መፈተሽ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የመፃፍ ክሂል ምንነት፣ አስፈላጊነት እና አቀራረቦች

### 2.1.1. የመፃፍ ክሂል ምንነት

መፃፍ በቋንቋ ውክልና አማካይነት የሀሳብ ማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ እንደ Elhabiri (2013፣19) አገላለፅ በአሁኑ ጊዜ በአለማችን ላይ ካሉት የተግባቦት መንገዶች መካከል ከፍተኛውን ድርሻ የያዘው ፅሁፋዊ ተግባቦት ነው፡፡ የመፃፍ ክሂልን በተመለከተ የተለያዩ ባለሙያዎች ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ Byrne (1988፣1) መፃፍ የአንድ ቋንቋ ድምፆች ከምልክቶቻቸው ጋር እያዛመድን የቋንቋው ህግ በሚፈቅደው መሰረት በወረቀት ላይ እያሰፈርን ሀሳባችንን የምንገልፅበት መንገድ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ Elhabiri (2013፣19) በበኩላቸው መፃፍ ማለት አንባቢ በሚረዳው መልኩ ሀሳብን አቀናጅቶ በፅሁፍ ማስፈር ነው ይላሉ፡፡ የሻው (1996፣14) የመፃፍ ክሂልን ሲገልፁ ፅሁፍ ውክልና በመሆኑ በጋራ የተስማማንባቸውን ቅርፃዊ ምልክቶች በመጠቀም ቋንቋን በውክልና ማስፈር ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው መፃፍ በቅርፃዊ ምልክቶች አማካይነት ሀሳብን ማስፈር ነው፡፡ የመፃፍ ክሂል በመደበኛ ትምህርት የሚዳብር በመሆኑ በመማሪያ ክፍልም ሆነ ከመማሪያ ክፍል ውጪ መለማመድን ይጠይቃል፡፡

### 2.1.2. የመፃፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

ማስታወሻዎችን፣ ዘገባዎችን፣ ደብዳቤዎችን፣ የቤት ስራዎችን፣ ገጠመኞችን ወዘተ መፃፍ አብዛኞቻችን በእለት ተለት ህይወታችን የምናከናውናቸው ተግባራት ሲሆኑ ጥቂቶቻችን ደግሞ ልቦለድ እና ግጥም እንፅፋለን፡፡ እነዚህ የፅህፈት ተግባራት በሙሉ ተግባቦታዊ አላማ አላቸው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በዚህ ክሂል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ሊያዳብሩት ይገባል፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በርካታ በመሆናቸው እነዚህን ተግባራት ለማከናወን እና ሀሳባቸውን በፅሁፍ ለማስፈር የመፃፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊ ነው፡፡ የመፃፍ ክሂል ትምህርትን አስፈላጊነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡

ግርማ (1990፣6) "ጥሩ የመፃፍ ክሂል ተማሪዎች የሚማሯቸውን የተለያዩ አካዳሚያዊ የትምህርት አይነቶች በተሳካ ሁኔታ እንዲከታተሉ ከማስቻሉም በላይ ወደፊት ለሚጠብቋቸው ሙያዎች እና የስራ መስኮች ጠቃሚያቸው ነው። ጋዜጠኞች፣ የታሪክ ፀሀፊዎች፣ የሳይንስ ባለሙያዎች መሀንዲሶች ወዘተ. ሁሉ በተለያየ ደረጃም ቢሆን የፅህፈት ክሂል ያስፈልጋቸዋል። "በማለት ሲገልፁ Harmer (2004፣ 3) በበኩላቸው የመፃፍ ክሂል ከአራቱ መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ በመሆኑ ተማሪዎች ሊማሩት ይገባል። የዘገባዎችን እና የደብዳቤዎችን አፃፃፍ፣ እንዲሁም የአንቀፅን ግንባታ፣ የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም ለማስተማር የመፃፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊ ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

Byrne (1988፣ 6-7) የመፃፍ ክሂል ትምህርት አስፈላጊነትን እንደሚከተለው በዝርዝር ያቀርባሉ።

1. የመፃፍ ክሂል ትምህርት የተለያዩ የመማር ስልቶችን ለመቅሰም ያስችላል። በተለይም ቃላዊ በሆነ የትምህርት አሰጣጥ በቀላሉ መማር ለሚቸግራቸው ተማሪዎች  እንደ አጋዥ በመሆን ትምህርቱን ዘና ብለው እንዲማሩ ይረዳል።
2. በፅሁፍ የቀረበ ስራ ለተማሪዎች ተጨባጭ መረጃ በመሆን ስለሚያገለግላቸው አዕምሮአዊ ፍላጎታቸውን ያሟላሉ።
3. የመፃፍ ክሂልን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት መማር ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ ተማሪዎች በዚህ ተጠቃሚ ይሆናሉ።
4. መፃፍ ልዩ ተግባር በመሆን ያገለግላል። ይኸውም ተማሪዎች በቃል ሲማሩ ከቆዩ በኋላ  በመሀል እንደ እረፍት ማድረጊያ ተግባር ይጠቀሙበታል።
5. መደበኛ እና ኢ መደበኛ ፈተናዎችን ለመስጫነት አስፈላጊ ነው።

ተመስገን (2001፣8) Mercer እና Mercer (1989) ን ጠቅሰው እንደገለፁት የመፃፍ ክሂል ትምህርት ሶስት ጠቀሜታዎች አሉት። እነሱም የመጀመሪያው ተማሪዎች በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት የሚሰጡ ትምህርቶችን ለመከታተል እንዲችሉ ያደርጋል። ሁለተኛ ተማሪዎች የፅህፈት ቅርፆችን በማስተማር ከትምህርት ቤት ውጪ በሚሰሩ ስራዎች ማለትም ደብዳቤ መፃፍ፣ ማመልከቻ መፃፍ፣ ቅፆችን መሙላት፣ ማስታወሻ መያዝ በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ጥሩ ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ሶስተኛው ደግሞ ተማሪዎች የፈጠራ ፅሁፎችን ማለትም ልቦለድ፣ ግጥም ወዘተ መፃፍ እንዲለማመዱ ያስችላል።

በአጠቃላይ የመፃፍ ክሂልን ማስተማር በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የመፃፍ ክህሎት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚያከናውኗቸው ልዩ ልዩ ተግባራት አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር ከትምህርት ቤት ውጪ፣ በእለት ተለት ህይወት ለሚሰሩት ስራ ያስፈልጋል፡፡

## 2.1.3. የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያገለግሉ በርካታ አቀራረቦች ቢኖሩም በአብዛኞቹ ምሁራን የሚጠቀሱት ዋና ዋናዎቹ ውጤታዊ አቀራረብ እና ሂደታዊ አቀራረብ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት ተማሪዎች የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን መነሻ በማድረግ መፃፍን ሲለማመዱ ውጤታዊ እና ሂደታዊ አቀራረቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

### 1. ውጤታዊ አቀራረብ

Pincas (1982፣32) እንደሚገልፁት ይህ ዘዴ በአለም አቀፍ ደረጃ በስፋ ያገለገለና ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ ነው ፡፡ ውጤታዊ አቀራረብ ትኩረቱ ተማሪዎች በሚፅፉት የመጨረሻ ስራ ላይ ነው፡፡ ዓላማው ተማሪዎች በሚያከናውኑት የመፃፍ ክሂል ትምህርት ተግባራት፣ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ማለማመድ ነው፡፡ እንደ Elhabiri (2013፣21) አገላለፅ ውጤታዊ አቀራረብ በቋንቋው ቅርፅ ማለትም አገባብ ሰዋስው፣ አደረጃጀት ወዘተ ላይ ያተኩራል፡፡

ይህ ዘዴ ሞዴል ፅሁፎችን በማቅረብ ተማሪዎች የሰዋስው ህጎችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው በማሳየት እና በተግባር በማለማመድ አስመስለው እንዲፅፉ የሚጠይቅ ነው፡፡ የእጅ ፅህፈት፣ ስርዓተ ነጥብ፣ የፊደል አጣጣል፣ የቃላት አገባብ በትምህርትነት የሚሰጡ ሲሆን የትምህርቱ አላማ ተማሪዎች በትምህርት ተቋማት ወይም በግል ህይወታቸው የሚተገብሯቸውን ፅሁፎች እንዲለማመዱ ማስቻል ነው፡፡ ይህን ሀሳብ በሚመለከት Pincas (1982፣34) ውጤታዊ አቀራረብ ሞዴል ፅሁፍን መነሻ በማድረግ ሰዋስዋዊ ህጎችን፣ አደረጃጀትን የአፃፃፍ ስልትን በማሳየት ተማሪዎች ይህንኑ በፅሁፋቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ሲሆን ትኩረቱ የቋንቋውን ሰዋስው ማሳየት ነው ብለዋል፡፡

### 2. ሂደታዊ አቀራረብ

ሂደታዊ አቀራረብ በ1970ዎቹ አጋማሽ ውጤታዊ አቀራረብን በመተካት ብቅ ያለ የመፃፍ ክሂልን ማስተማሪያ ዘዴ ነው (Benaissa 2010፣31)፡፡ በዚህ አቀራረብ ትኩረት

የሚደረገው በፅሁፉ የመጨረሻ ውጤት ላይ ሳይሆን የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር በሚከናወኑ ተግባራት እና ወደውጤት ለመድረስ በሚያስችለው ሂደት ላይ ነው፡፡ የፀሀፊው ትኩረት ፅሁፉን እንዴት እንደሚጀምር እና እንደሚያደራጀው በመወሰን ላይ ነው፡፡

ይህ አቀራረብ ሞዴል ፅሁፎች ላይ በማተኮር የመፃፍ ክሂልን ማስተማር ውጤታማ አያደርግም በሚል አትኩሮቱን ከመዋቅር ወደ ይዘት የመለሰ ዘዴ በመሆኑ መጻፍን በማስተማር ሂደት ለውጥ ያመጣ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ የተማሪን እና የመምህርን ሚና እንዲሁም በማስተማሪያ ክፍል የሚከናወኑ ተግባራትን ለይቶ በማስቀመጥ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይኸውም በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ተማሪዎች በራሳቸው የመማር ፍጥነት እንዲለማመዱና በተማሪዎች መካከል እርስበርስ ተባብሮ የመስራት ሁኔታ እንዲኖር የሚፈቅድ ከመሆኑም ባሻገር ተማሪዎች ርዕስ መምረጥ፣ ሀሳብ ማመንጨት፣ እቅድ ማዘጋጀት፣ ማርቀት፣ መከለስ እና የመሳሰሉ ሂደቶችን እንዲያልፉ የሚያበረታታ ነው፡፡ በሂደታዊ አቀራረብ የመምህሩ ሚና በክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሂደት ማመቻቸት ነው (Pincas 1982፣32)፡፡

እንደ Raimes (1983፣ 10) እና Pincas (1982፣ 37) አገላለፅ ዘዴው ተማሪዎች በራሳቸው እንዲማሩ እና ከመምህራን ጋርም ተባብሮ የመስራት ልምድ እንዲያዳብሩ የሚያስችል በመሆኑ አሳታፊ ነው፡፡

በሂደታዊ አቀራረብ ተማሪዎች ጥሩ የመፃፍ ችሎታ እንዲያዳብሩ ልዩ ልዩ ንዑሳን ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡ እነዚህ ንዑሳን ተግባራት/ደረጃዎች Pincas (1982፣ 41) ፤ Sorenson (2010፣ 3) እና Albesher (2012፣ 17) በሶስት ይከፍሏቸዋል፡፡ እነሱም ቅድመ መፃፍ /ማሰላሰል፣ መፃፍ/ማርቀቅ፣ እና ድህረ መፃፍ/ክለሳ ናቸው፡፡

### ሀ. ቅድመ መፃፍ

ቅድመ መፃፍ ተማሪዎች ወደዋናው የመፃፍ ደረጃ ለመግባት የሚዘጋጁበት ክፍል ነው፡፡ ወደመፃፍ ተግባር ከመግባታቸው በፊት ስለሚፅፉት ርዕሰ ጉዳይ ግልፅ ሀሳብ የሚይዙበት በመሆኑ ሀሳባቸውን የሚያሰባስቡበት፣ ርዕስ የሚመርጡበት፣ ስለርዕሱ መረጃ የሚሰበስቡበት እና እቅድ የሚነድፉበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎች ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር ረዘም ላለ ጊዜ መወያየት መፃህፍትን ማንበብ፣ ሰዎችን መጠየቅ፣ ከቤተሰብ ጋር

መወያየት እና ጥርት ያለ ሀሳብ ለመያዝ የሚረዱ ተግባራት ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ በድሉ (2007፣ 78) ለአንባቢ ማስተላለፍ የምፈልገው ምንድ ነው? የትኛውን የአፃፃፍ ስልት ብጠቀም መልዕክቴን ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ መግለፅ እችላለሁ? የሚሉ ጥያቄዎች በዚህ ደረጃ መመለስ አለባቸው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ርዕስ መፈለግ፣ የሀሳብ ማፈላለጊያ ዘዴዎችን መለየት፣ አንባቢያችንን ማወቅ እና የርዕሰ ጉዳያችንን ወሰን መለየት በቅድመ መፃፍ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው (ማረው 1996፣10)፡፡

ቅድመ መፃፍ ተግባራት ጥሩ ርዕስ ለመምረጥ እና የፅሁፉን ዓላማ ለመለየት ያግዛሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በቂ ጊዜ ወስደው ተግባራቱን እንዲያከናውኑ የመምህራን ክትትል እና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡

**ለ. ጊዜ መፃፍ**

ይህ ደረጃ ሀሳብን በወረቀት ላይ በረቂቅ መልክ ማስፈርን ይመለከታል፡፡ ጊዜ መፃፍ ትክክለኛው የመፃፍ ተግባር የሚጀመርበት ነው፡፡ ተማሪዎች፣ በቅድመ መፃፍ ጊዜ የሰበሰቧቸውን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ያዳበሩትን ሀሳብ ተጠየቃዊ በሆነ ቅደም ተከተል የሚያሰፍሩበት ሂደት በመሆኑ የመጀመሪያ ረቂቅ መፃፍ፣ የተፃፈውን የማንበብ እና የመከለስ ፅሁፉ የሚዳብርበት ሀሳብ የመፈለግ ተግባር ያከናውናሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ማረው (1996፣16) ጊዜ መፃፍ፣ ዓረፍተ ነገሮችን ባግባቡ ማዋቀርን፣ አረፍተ ነገርን አደራጅቶ አንቀፅ መመስረትን እና አንቀፅን አደራጅቶ ሙሉ ድርሰት መፃፍን የሚመለከት እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

**ሐ. ድህረ መፃፍ**

ድህረ መፃፍ በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ የማሻሻያ ስራ የሚሰራበት ሂደት ሲሆን ፀሀፊው የፅሁፉን መልዕክት፣ ቅርፅ እና ተደራሲን ደግሞ የሚያስብበት የመልዕክቱን ግልፅነት የሚገመግምበት እና የመጨረሻ ማስተካከያ የሚያደርግበት ደረጃ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ሀሳባቸውን በአግባቡ ለማስተላለፍ ቃላት ሊቀይሩ፣ ሀሳብን እንደገና በተለየ መንገድ እና ቅደም ተከተል ሊያደራጁ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል ደረጀ (1996፣ 90-109) የመፃፍ ክሂልን በመለማመድ ሂደት በየደረጃው የምንከተላቸው የተለያዩ አካሄዶች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡ እነዚህም አካሄዶች ርዕስ መምረጥ ርዕስ መወሰን፣ የመፃፍ ዓላማ፣ ተደራሲ እና አውድን መለየት፣ ቢጋር መንደፍ፣ መረጃ

ማፈላለግ፣ እና ረቂቅ መፃፍ እንደሆኑ ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህን በአጭሩ ለማየት እንሞክር፡፡ አንድ ፅሁፊ በሚገባ የሚያውቀውን እና የመፃፍ ፍላጎቱን ሊቀሰቅስ የሚችል ርዕስ መምረጥ አለበት፡፡ የሚፅፈው ርዕሰ ጉዳይም ሊፅፍ ከተነሳበት ዓላማ ጋር የሚጣጣም ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህ እንዲሆን ርዕሱ ከምንፅፍበት ጊዜ እና የፅሁፉ ርዝማኔ ተገናዝቦ መጥበብ/መወሰን ይኖርበታል፡፡ ድርሰት የመፃፍ  አላማ የሚወሰነው ምን? ለምን? ለማን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎችን በመመለስ ነው፡፡ ለማን የሚለው ጥያቄ ተደራሲን የሚመለከት ሲሆን የፅሁፍ ዓላማ ፅሁፉ ታላሚ ከሚያደርገው አንባቢ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ በመሆኑም የተደራሲን ፍላጎት ገምቶ ፅሁፍን መፃፍ ፅሁፉ የተዋጣለት እንዲሆን በማድረግ እገዛ ያደርጋል፡፡

በመፃፍ ሂደት ርዕስ የመምረጥ፣ የማጥበብ፣ ዓላማ እና ተደራሲን የመለየት ስራዎች ከተወሰኑ በኋላ አስተዋፅኦ መንደፍ ቀጣዩ ተግባር ነው፡፡ አስተዋፅኦ/ ቢጋር መንደፍ ድርሰት በመፃፍ ሂደት ዋናው ሀሳብ ከመስፈሩ አስቀድሞ የፅሁፉን አካሄድ በዝርዝር የምናሳይበት ነው፡፡ አፅመ ንድፉን በመያዝ ከሚፃፈው ርእስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ሀሳቦች ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ማሰባሰብ እና በቢጋሩ መሰረት አብረው የሚሄዱ ሀሳቦችን በማቀናጀት በቅደም ተከተል ማስፈር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ ምሳሌዎችን እና ሌሎች የማስፋፊያ ስልቶችን በመጠቀም የመጀመሪያ፣ ከዚያም የመጨረሻ ረቂቅ ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡

ከቀረበው ሀሳብ የምንረዳው ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን በሚለማመዱበት ጊዜ በቅድመ መፃፍ፣ በጊዜ መፃፍ እና በድህረ መፃፍ ጊዜ ተግባራዊ የሚያደርጓቸው ክንውኖች ነው፡፡

### 3. የተመጣጠነ አቀራረብ /Balanced Approach

ውጤታዊ እና ሂደታዊ አቀራረቦች የየራሳቸው ጥንካሬ እና ድክመት ያላቸው በመሆኑ መምህራን በአንዱ ላይ አተኩረው ሌላውን መተው ሳይሆን ሁለቱንም ዘዴዎች እንደአስፈላጊነታቸው እያፈራረቁ እና እያዋሀዱ ቢጠቀሙ ውጤቱ ያማረ ይሆናል፡፡ Raimes (1983፣11) እና Elhabiri (2013፣ 22) ይህን በሚመለከት ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት የተሻለ ወይም የተዋጣለት የሚባል ዘዴ እንደሌለ በመጠቀም መምህራን ከየዘዴዎቹ በማውጣጣት እንዲያስተምሩ ይመክራሉ፡፡

## 2.2. ቋንቋን በማስተማር ረገድ የስነፅሁፍ ፋይዳ

የፈጠራ ፅሁፎችን በቋንቋ ክፍለ ጊዜ መጠቀም ተማሪዎችን በማነቃቃት ለቀረበው ፅሁፍ ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ ይኸውም የሰዎችን የእለት ተለት ህይወት አስውቦ ስለሚያቀርብ ተማሪዎች ለስራው አፅንኦት እንዲሰጡ እና ራሳቸውም የድርጊቱ ተሳታፊ እዲሆኑ ስለሚያስችል ገጠመኞቻቸውን እንዲፁፉ፣ እንዲናገሩ ፍላጎት ያሳድርባቸዋል፡፡ የቋንቋ ትምህርትን በስነፅሁፍ አማካይነት ማስተማር በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡

ስነፅሁፍን እንደ መሳሪያ ተጠቅሞ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ሊገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ ዘመንፈስ (1991፣ 2) Ibsen (1995) ን ጠቅሰው ሁለት ነጥቦችን ያስቀምጣሉ፡፡ የመጀመሪያው የስነፅሁፍ ቋንቋ እውናዊ (Authentic) በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ መማር ሂደት ያፋጥናል፡፡ ይህ የሚሆነው የስነፅሁፍ መለያ ባህሪው አሻሚነቱ ስለሆነ ፅሁፉን ካነበቡ በኂላ በተማሪዎች መካከል የተለያየ አመለካከት እና ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡ የፅሁፉን አሻሚነት ለመረዳት በሚደረገው ጥረትም ተማሪዎችን ሊስቡ የሚችሉ አከራካሪ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ፡፡ የተማሪዎች ምላሽ በፅሁፉ ከሰፈረው ሀሳብ ጋር ባለመስማማቱ ምክንያት የሚፈጠረው ክርክር ጥሩ የክፍል ውስጥ መልመጃ ይፈጥራል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተጠቀሰው ጠቀሜታ ከዕውቀት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ስነፅሁፍን ማንበብ ብሎም ስለሱ መናገርና መፃፍ ቋንቋን በመማር ረገድ ስሜታዊ (Affective) እና አፅምሮታዊ (Cognitive) ሂደትን የተከተለ ነው፡፡ ስሜታዊ የእውቀት ዘርፍ አንባቢ ከፅሁፍ ጋር ተገናኝቶ ስሜቱን እና ተሞክሮውን እንዲያንፀባርቅ እድል ይሰጣል፡፡ በዚህም ምክንያት ራሳቸውን አልያም የሚያውቁትን ማህበራዊ ሁኔታ እንዲያንፀባርቁ ያስችላል፡፡ ትምህርቱን በትኩረት ይከታተላሉ፡፡ በአፅምሮታዊ የዕውቀት ዘርፍም ተማሪዎች የቃላት እና የአረፍተ ነገሮችን መዋቅር ይረዳሉ፡፡

በስነፅሁፍ ስራ ውስጥ የምናገኘው የቋንቋ አጠቃቀም መለያ ባህሪ አሻሚነት መሆን፣ የቃላት እና የሀረጋት ትርጉም በቀላሉ የሚገኝ አለመሆን እና አንድን የስነፅሁፍ ስራ ሁላችንም አንብበን ስለስነፅሁፉ የሚኖረን አስተያየትም ሆነ በፅሁፉ የተነሳ የተሰማን ስሜት አንድ አይነት አለመሆን በስነፅሁፍ አማካይነት ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ እንዲሆን የሚያደርጉ ምክንያቶች እንደሆኑ (ፈቃደ 1991፣111-112) ይገልፃሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ተማሪዎች ስነፅሁፋዊ ስራዎችን አንብበው የተፈለገውን ትርጉም ለማግኘት

ሲጠያየቁ እና ሲወያዩ ስለቋንቋው ልዩ ልዩ ባህሪያት በራሳቸው ጥረት ይማራሉ። ኢ ርዕቱ በሆነ መንገድ የቋንቋ እና የአስተሳሰብ ችሎታቸውን እንዲያበለፅጉ ያደርጋቸዋል።

በድሉ (2007፣ 28) ስነፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት መጠቀም የተማሪዎችን ትኩረት በመሳብ በክፍል ውስጥ ተግባራት ራሳቸውን ተሳታፊ አድርገው እንዲመለከቱ ያደርጋል። ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በሚያነቡ ጊዜ የታሪኩን ድባብ ይፈጥራሉ። እንዲሁም ከሚያነቡት ስራ ጋር ተዛማጅ የሆነ ቀዳሚ እውቀታቸውን እና ልምዳቸውንም እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል ሲሉ ስነፅሁፍ የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ይገልፃሉ።

Hill (1986፣ 7) በበኩላቸው ስነፅሁፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ፋይዳ ሲገልፁ የተማሪዎችን አጠቃላይ እውቀት እና አስተሳሰብ ለማስፋት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ እንዲሁም ሁለንተናዊ ስሜቶችን ለመቀስቀስ ባለው ሀይል በቋንቋ ትምህርት ለመካተቱ ምክንያት እንደሆነ ይገልፃሉ። ከዚህ በተጨማሪ

- ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት መግባባት እንዲችሉ ያደርጋል።
- ከፍተኛ የመገፋፋት እና የማነቃቃት ሀይል አለው ሲሉ ይገልፃሉ።

Lazar (1993፣14-15) በስነፅሁፋዊ ስራዎች ቋንቋን የማስተማር ምክንያቶች የሚከተሉት እንደሆኑ ይገልፃሉ።

- በከፍተኛ ሁኔታ አነቃቂ እና ቀስቃሽ መሆኑ
- እውናዊ የማስተማሪያ መሳሪያ መሆኑ
- ትምህርታዊ ዋጋ እና ደረጃ ስላለው
- በመርሀ ትምህርቶች መካተቱ
- ቋንቋን ለመልመድ የሚያነሳሳ በመሆኑ
- ትርጓሜ የመስጠት ችሎታን ስለሚያዳብር
- አዝናኝ በመሆኑ ደስታን ስለሚፈጥር
- የቋንቋ እውቀትን ስለሚያሰፋ
- ተማሪዎች ሀሳባቸውን እና ስሜታቸውን እንዲገልፁ ስለሚያበረታ

ስነፅሁፍ የሰው ልጅን የህይወት ገጠመኝ አስውቦና ሳቢነት ባላቸው ቃላት ከሽኖ ስለሚያቀርብ ቀልብ የመሳብ ሃይሉ ከፍተኛ ነው። ከዚህ የተነሳ ተማሪዎች በስራው በመሳብ በክፍል ውስጥ ተግባራት ራሳቸውን ተሳታፊ በማድረግ ትምህርቱን በትኩረት

ይከታተላሉ፡፡ በዚህም ምክንያት የቋንቋ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ፤ አጠቃላይ አስተሳሰባቸውን ያጎለብታሉ፡፡ በመሆኑም ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡

## 2.3. ስነፅሁፍ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ፋይዳ

ስነፅሁፍ የቋንቋ ትምህርትን ለማዳበር ያለውን ድርሻ በሚመለከት በ2.2 ተገልጿል፡፡ ይኸውም በአጠቃላይ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እና ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች ለማዳበር ያለውን ጠቀሜታ የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና ይቀርባል፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት ዓብይ አላማ ስነፅሁፍ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና የሚመለከት በመሆኑ፡፡

ፈቃደ (1991፣111-112) ስነፅሁፋዊ ስራዎች የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያላቸውን አስተዋጽኦ ይገልፃሉ፡፡ የተለመደው የሰዋስው ትምህርት እና ተርታ ፅሁፎችን (ስነፅሁፍ ያልሆኑ ስራዎች) ለማስተማሪያ መሳሪያነት መጠቀም፣ ስነፅሁፍን የመጠቀምን ያህል የሀረጋትን እና የዓረፍተ ነገሮችን አወቃቀር ለማስተማር ምቹ እንዳልሆነ እና ረብ ያለው ውጤት እንደማያስገኝ ያስረዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ስነፅሁፋዊ ስራዎች የማወያየት እና የማከራከር ባህሪ ስላላቸው ተማሪዎች ስለቋንቋው ባህሪያት የራሳቸው መደምደሚያ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ለተለያዩ የሀረጋት እና የአረፍተ ነገሮች አወቃቀር ዘዴዎች ስለሚጋለጡ ተቆጥሮ ከማያልቀው አወቃቀር ዘዴ መሃል አንዱን ከአንዱ እያዳቀሉ የራሳቸውን ዘዴ ፈልገው በማግኘት ጥሩ ዓረፍተ ነገሮችን መፃፍ እንዲጀምሩ ያስችላቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

Santhi (2012፣ 19) ይህን በተመለከተ ስነፅሁፍ የተማሪዎችን የመፃፍ ፍላጎት በመቀስቀስ ከፍተኛ ድረሻ እንዳለው አስረድተዋል፡፡ ይኸውም ስነፅሁፋዊ ስራዎችን እንደ ሞዴል በማቅረብ ተማሪዎች ያንን አስመስለው እንዲፅፉ ማድረግ ይቻላል፡፡ የሚቀርብላቸውን ስነፅሁፋዊ ስራዎች ይዘት፣ ጭብጥ፣ አደረጃጀት እና የአፃፃፍ ስልት ተከትለው በማስመሰል ይፅፋሉ፡፡ ይህም ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸው እንዲዳብር ያስችላቸዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን የተለያዩ መልመጃዎችን ማለትም ምልልሶችን፣ ጅምር ዓረፍተ ነገሮችን እንዲሁም ውስብስብ የሆኑ ሌሎች የመፃፍ ክሂል ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸውን ማዳበር እንዲችሉ እገዛ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

## 2.4. ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው ጠቀሜታ

እንደ Lazar (1990፣ 204-205) አገላለፅ ረዥም ልብ ወለድን በቋንቋ ትምህርት መጠቀምን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ጉዳዮች ቢኖሩም የተማሪዎችን ፍላጎት ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ፣ በጥንቃቄ እና በአግባቡ ከተመረጠ ለስነ ትምህርታዊ ተግባራት ምንጭ በመሆን ያገለግላል ይላሉ። ተማሪዎች የማሰብና የመመራመር፣ የስሜት እንዲሁም ስለቋንቋው ያላቸው እውቀት እንዲጨምር ያደርጋል። የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትንም ለማዘጋጀት ምቹ ነው።

ስለዚህ ልብ ወለዱ በአግባቡ በመምህራን ከተመረጠ እና የተማሪዎችንም ፍላጎት የሚያሟላ ከሆነ፣ ተማሪዎች በትምህርቱ ደስተኛ ይሆናሉ። በዚህም የክፍል ውስጥ ተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊ በመሆን የመፃፍ ክሂላቸውን ያዳብራሉ።

Hişmanoğlu (2005፣ 63) እንደሚያስረዱት በረዥም ልቦለድ ገፀባህሪያት የሚያንፀባርቁት ባህሪ ሰዎች በለት ተለት ህይወት የሚተገብሩት ነው። ይህ ከተማሪዎች የግል ህይወት ጋር በተቆራኘ መልኩ ቋንቋን ለማስተማር ጠቀሜታው የጎላ ነው። ይኸውም በልቦለዱ ታሪክ መነሻነት ተማሪዎች በግል ህይወታቸው ያጋጠማቸውን እንዲፅፉ ማድረግ ይቻላል።

እንደምሁሩ አገላለፅ ረዥም ልቦለድን በቋንቋ ትምህርት መጠቀም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል።

- ተማሪዎች የተለያዩ የማህበረሰብ አባላትን እና ባህላቸውን እንዲያውቁ ያግዛል።
- የሂሳዊ አስተሳሰብ ክህሎትን ያሻሽላል።
- የፅህፈት እና ንግግር ክህሎትን ያሳድጋል።
- ተማሪዎች የገፀባህሪያትን ህይወት በመረዳት በለት ተለት ህይወት የሚያጋጥማቸውን ችግር የመፍታት ክህሎትን ያሳድጋሉ።
- መረጃን የመፈለግ፣ የተገኘውን መረጃ ወደ እውቀት የመለወጥ፣ አማራጮች እንዳሉ የማሰብ እና ትርጉም ያለው ትምህርት የመማር ልምዳቸውን ያዳብራል።
- የመማር ፍላጎትን በመቀስቀስ የተለየ የማስተማሪያ ዘዴን ያቀርባል።

ረዥም ልቦለድ ከላይ በዝርዝር የቀረቡ እውቀቶችን እና ክህሎቶችን ያስጨብጣል። በመሆኑም ልቦለድን በማንበብ እነዚህን እውቀቶችና ክህሎቶች ያገኙ ተማሪዎች

ልምዳቸውን መሰረት አድርገው የመፃፍ ክሂልን እንዲለማመዱ በማድረግ ማስተማር ይቻላል፡፡

## 2.5. የስነፅሁፍ ስራዎችን የመምረጫ መስፈርቶች

ቋንቋን ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን መምረጥ ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸውን መሰረታዊ መስፈርቶች የተለያዩ ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ ይህን በተመለከተ Lazar (1993፣ 48) ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስንመርጥ በዋናነት ስለሶስት ነገሮች ማሰብ አለብን ይላሉ፡፡ እነሱም የምናስተምረው የትምህርት ዓይነት፣ ተማሪዎች እና ስነፅሁፋዊ ስራው ናቸው፡፡ እነዚህን ሶስት ነገሮች ታሳቢ በማድረግ የተለያዩ መስፈርቶችን ማዘጋጀት እንደሚቻልም ይገልፃሉ፡፡

ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ለመምረጥ የሚያገለግሉ መስፈርቶችን Lazar (1993፣ 53-54) እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡፡

***የተማሪዎች ባህላዊ ዳራ፡-*** ስነፅሁፋዊ ስራው ለተማሪዎች ባህል፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች የቀረበ ወይም የራቀ መሆኑን ማጤን አለብን፡፡ የመረጥነው ስራ ለተማሪዎች ባህል በጣም የቀረበ ወይም የራቀ ከሆነ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይኸውም የተማሪውን ባህላዊ ዳራ ያገናዘበ ስራ ከተመረጠ ተማሪዎች ትምህርቱን በፍላጎት እና በጉጉት እንዲከታተሉ ይረዳቸዋል፡፡

***የተማሪዎች ስነልሳናዊ ዳራ፡-*** ተማሪዎች የቀደመ እውቀታቸው ምን ያህል ነው የሚለው ጥያቄ ሊመለስ ይገባዋል፡፡ ማለትም የሚመረጠው ስነፅሁፋዊ ስራ በቃላት፣ በሰዋስው አጠቃቀም እና አገባብ የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ፣ እድሜ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባዋል፡፡

***የተማሪዎች ስነፅሁፋዊ ዳራ ፡-*** በስነልሳናዊ እና ስነፅሁፋዊ ዳራ መካከል የጠበቀ ግንኙነት አለ፡፡ ይኸውም ተማሪዎች የስነልሳን እውቀታቸው ከፍተኛ ሆኖ የስነፅሁፍ እውቀታቸው ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች ቃላትን በተናጠል ቢያውቋቸውም ስነፅሁፋዊ ስራውን ግን አንብበው ላይረዱት ይችላሉ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹ ስነልሳናዊ እውቀት ብቻ ሳይሆን ስነፅሁፋዊ ዳራቸውን ያገናዘበ ስራ መምረጥ ይገባል፡፡ ተማሪዎች ከዚህ በፊት

ስነፅሁፋዊ ስራዎችን አንብበው የሚያውቁ ከሆነ የቀረበው ቅንጫቢ እንግዳ አይሆንባቸውም፡፡

***የስነፅሁፋዊ ስራው ርዝማኔ፡-*** ስነፅሁፋዊ ስራዎችን እንዳሉ ማቅረብ ተማሪዎችን የሚያሰለች በመሆኑ ቅንጫቢዎችን ማቅረብ ተመራጭ ነው፡፡ ቅንጫቢዎችም ቢሆኑ በክፍለ ጊዜው የሚጠናቀቁ መሆን አለባቸው፡፡

***ከመርሀ ትምህርቱ ጋር የመዛመድ ሁኔታ፡-*** የሚመረጠው ቅንጫቢ በመርሃ ትምህርቱ ከተጠቀሱት የቋንቋ ክሂሎች፣ ሰዋስው እና ልዩ ልዩ የዕውቀት ዘርፎች ጋር የተገናዘበ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም በመርሃ ትምህርቱ ከቀረቡ ስነዘዴዎች ጋር የተጣጣሙ ተግባራትን ለማዘጋጀት የሚያስችል ስነፅሁፋዊ ስራ ቢመረጥ የቋንቋ ትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ ያስችላል፡፡

***ተበርባሪነት/EXPLOITABILITY፡-*** ተበርባሪነትን በተመለከተ ለማስተማሪያነት የሚቀርበው የስነፅሁፍ ቅንጫቢ የተለያዩ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ በርካታ ተግባራትን ማለትም ቃላትን ዘይቤዎችን፣ አረፍተ ነገር ምስረታን አንቀፅ ግንባታን ወዘተ ለማዘጋጀት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡

**የስነፅሁፍ ስራው ለተማሪዎች የመዳረስ ሁኔታ፡-** የሚመረጠው ቅንጫቢ በምን ያህል መጠን እንደሚገኝ እና ለተማሪዎች በምን መልኩ መዳረስ እንዳለበት መታወቅ አለበት፡፡ በበቂ ሁኔታ አዘጋጅቶ ማዳረስ እንደሚቻል አስቀድሞ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

ከላይ በLazar ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ሌሎች ምሁራን የስነፅሁፋዊ ስራዎችን መምረጫ መስፈርቶች እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡፡

በድሉ (2007፣ 32) የሚመረጠው ስነፅሁፋዊ ስራ የተማሪዎችን የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ መሆን አለበት ሲሉ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

*የተማሪዎችን ደረጃ የጠበቀ ስራ መቅረብ አለበት ስንል፣ ከደረጃቸው በላይ የከበደ ወይም ከደረጃቸው በታች የቀለለ መሆን የለበትም ማለታችን ነው። የቀረበው ስራ በየአረፍተነገሮቹ እንግዳ ቃላትን ከያዘ፣ አገባቡ እና አገላለፁ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁት ጋር ብዙ ልዩነት ካለው በርግጥም ስራው ከባድ ነው። በዚህ ሁኔታ የቃላትን ፍቺ ከአገባብ አውድ ለመፈለግ ይቸገራሉ፤ የመማር ፍላጎታቸው ይቀንሳል፤ በስነፅሁፍ መማርም ሆነ በግል ስነፅሁፍ ማንበብ ይፈራሉ።*

በመሆኑም ቋንቋን በስነፅሁፍ ለማስተማር ሲታሰብ ለተማሪዎች የሚቀርቡ ስነፅሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ በማገናዘብ የተመረጡ መሆን አለባቸው።

ስነፅሁፋዊ ስራዎች ለቋንቋ ትምህርት ሲውሉ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ ባህላዊ ዳራ የቋንቋ ችሎታ ወዘተ. መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው። የተማሪዎችን ተሳትፎ በመጨመር አዎንታዊ ምላሽ እንዲሰጡ የሚያስችል ስራ ተመራጭ ሲሆን የስነፅሁፋዊ ስራው የቋንቋ ክብደትም ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ነው (Collie እና Slater 1987፣12)።

Hill (1986፣15) እንደሚገልፁት ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ትምህርት ለመጠቀም በሶስት መሰረታዊ መስፈርቶች መፈተሽ ይገባል ይላሉ። እነሱም

1. የተማሪዎች ፍላጎት እና ችሎታ
2. የስነፅሁፋዊ ስራው ስነልሳናዊ እና ስልታዊነት ደረጃ
3. የተማሪዎች ዳራዊ እውቀት

የሚመረጡት ስነፅሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያሟሉ እንዲሆኑ ቋንቋ የመማር ዓላማን እና እድሜን መሰረት ያደረጉ መሆናቸው ሊጤን ይገባል። የተማሪዎችን የማንበብ እና ጥያቄዎችን የመመለስ ችሎታ ከግንዛቤ በማስገባት ስነፅሁፍን መምረጥ ተገቢ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የስነፅሁፋዊ ስራው ስነልሳናዊ ደረጃ ማለትም አዳዲስ ቃላት፣ ዘዬ ቃላት፣ አራድኛ ቃላት፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ወዘተ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። እንዲሁም የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት መሰረት ያደረጉ ስራዎች መመረጥ አለባቸው።

ስነፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስንመርጥ የተማሪዎች ባህላዊ፣ ስነልሳናዊ እና ስነፅሁፋዊ ዳራን ያገናዘበ መሆን አለበት። እንዲሁም የተማሪዎችን እድሜ፣ የቋንቋ

ችሎታ የትምህርት ደረጃ፣ ፍላጎት እና ተነሳሽነት መሰረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው ከላይ ከቀረበው የምሁራን አስተያየት መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.6. የቋንቋን ትምህርት መሰረት ያደረገ አቀራረብ

Lazar (1993፣ 23) ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በቋንቋ ትምህርት በመጠቀም ሂደት የትምህርቱን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ የተለያዩ አቀራረቦች እንዳሉ ይገልፃሉ፡፡ አቀራረቦቹን መለየት በማስተማር ሂደት የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ለመምረጥ እና ለመቅረፅ ጠቀሜታ እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ እነዚህ አቀራረቦች ተከታዮቹ እንደሆኑ Lazar ይገልፃሉ፡፡

- የስልታዊነት አቀራረብ
- የስብዕና እድገት ማበልፀግን መሰረት ያደረገ አቀራረብ
- ይዘት ተኮር አቀራረብ
- የቋንቋ ክሂሎችን መሰረት ያደረገ አቀራረብ

### 1. የስልታዊነት አቀራረብ

Lazar (1993፣ 30) ሲገልፁ የስልታዊነት አቀራረብ ስነፅሁፋዊ ስራውን ማጥናትን ይመለከታል፡፡ የዚህ ዘዴ አቢይ አላማ ተማሪዎች ለስነፅሁፋዊ ስራው ትርጉም እንዲሰጡ ማስቻል እና ስለቋንቋው ያላቸውን እውቀት ማስፋት ነው፡፡ በአጠቃላይ ስነፅሁፋዊ ስራውን በተሟላ መልኩ እንዲያጠኑ በማድረግ ጥሩ የቋንቋ ችሎታ እንዲኖራቸው ያስችላል፡፡ ነብዩ (2005፣ 21) Widdowson (1975) እና Carter (1986)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ስልታዊነት ሁለት የትምህርት ዘርፎችን ማለትም ስነልሳንን እና ስነፅሁፍን ለማገናኘት እንደድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ዘርፍ ነው፡፡ ዋና ትኩረቱ ከስነልሳናዊ እውነታዎች ጋር በተያያዙ ገለፃዎች ላይ ተመርኩዞ በተቻለ መጠን ትርጉምን ግልፅና ምልዑ በሆነ መንገድ ማቅረብ ነው፡፡ የስልታዊነት ባለሙያዎች ስራም ስነልሳንን መሰረት በማድረግ ስነፅሁፋዊ ስራው እንዴት እንደተዋቀረ መተንተን ነው፡፡ ስለዚህም በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኘው ማንኛውም ከቋንቋ ጋር ተዛምዶ ያለው የፅሁፍ አካል ይተነተናል፡፡

## 2. የስብዕና እድገት ማበልፀግን መሰረት ያደረገ አቀራረብ

ስነፅሁፍ ተማሪዎች ግላዊ ልምዳቸውን፣ ስሜታቸውን እና አስተሳሰባቸውን እንዲያጎለብቱ በማገዝ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ በመሆኑም ይህ አቀራረብ ተማሪዎች ግላዊ ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ በሚያስችል ሁኔታ ስነፅሁፋዊ ስራዎች እንዲቀርቡ የሚያስችል ነው፡፡ ተማሪዎች በግላዊ ህይወታቸውም ሆነ በትምህርታቸው ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

## 3. ይዘት ተኮር አቀራረብ

ይዘት ተኮር አቀራረብ ስነፅሁፍን ራሱን እንደ ርዕሰ ጉዳይ ተጠቅሞ ማጥናትን ይመለከታል፡፡ ስነፅሁፍን ማጥናት ስለስነፅሁፍ እውነታዎች፣ የደራሲያን የህይወት ታሪክ፣ የፅንሰ ሀሳቦች ስያሜ፣ የስነፅሁፍ ታሪክ፣ ዘውግ ወዘተ. የመሳሰሉትን ለተማሪዎች ማስጨበጥ ላይ ያተኩራል፡፡ ዓላማው ተማሪዎች ከትምህርቱ በኋላ ጥሩ ስነፅሁፋዊ እውቀት እንዲኖራቸው እና ሂሳዊ ትንታኔ እንዲሰጡ ማስቻል ነው፡፡ አቀራረቡ በአብዛኛው ተግባራዊ የሚሆነው በከፍተኛ ደረጃ በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ነው (Khatib 2011፣ 5 ፤ Lazar 1993፣ 24)፡፡

## 4. የቋንቋ ክሂሎችን መሰረት ያደረገ አቀራረብ

በዚህ ስነዘዴያዊ አቀራረብ በስነፅሁፍ መሳሪያነት ቋንቋን ማስተማር ትምህርቱን ከመርሀ ትምህርት ጋር ለማገናኘት ይረዳል፡፡ ዓላማውም የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ብቃት ማሻሻል ነው፡፡ የቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ከማድረጉም በላይ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው እና ቃላትን እንዲያውቁ ያስችላል፡፡ ይህ ዘዴ አቢይ ትኩረቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመሳሪያነት/በምንጭነት በመጠቀም የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል ማዳበር ላይ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ ይህ አቀራረብ ስነፅሁፍን እንደ አንድ የጥናት መስክ ማጥናት ላይ ትኩረት አያደርግም (Lazar 1993፣ 24)፡፡

ስነፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት እንደ ምንጭ መጠቀም እና እንደ አንድ የጥናት መስክ ማጥናት የተለያዩ ናቸው፡፡ ስነፅሁፍን እንደ ማስተማሪያ ምንጭነት መጠቀም ማለት ስነፅሁፍን ራሱን እንደ አንድ የትምህርት አይነት ማጥናት ማለት አይደለም፡፡ ስነፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት እንደ መሳሪያ መጠቀም በስነፅሁፋዊ ስራዎች አማካይነት አራቱን

የቋንቋ ክሂሎች ማዳበር ሲሆን እንደ ጥናት መስክ ማጥናት ደግሞ የስነፅሁፋዊ ስራዎች ምንነት እንዴትነት ወዘተ መመርመር ነው፡፡

የእያንዳንዱን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ አቀራረቦች ያሉ ሲሆን የዚህ ጥናት ትኩረት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣መናገር፣ መፃፍ እና ማንበብ) ለማዳበር በሚያግዘው የቋንቋ ክሂሎችን መሰርት ያደረገ ዘዴ ላይ ነው፡፡

## 2.7. በረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

ረዥም ልቦለድን መሰረት በማድረግ ቋንቋን ለማስተማር የሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራትን መምህራን ማዘጋጀት እንደሚችሉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ የመፃፍ ክሂል ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ይህን ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ተግባራትን ብቻ በዚህ ክፍል መመልከቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ Collie እና Slater (1987) ስነፅሁፋዊ ስራዎችን እንደምንጭነት በመጠቀም የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራትን ማዘጋጀት እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ተግባራት እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 1. ጅምር ዓረፍተነገሮችን ማሟላት

ጅምር ዓረፍተነገሮችን ማሟላት የሚተገበረው ተማሪዎች ቅንጫቢውን በክፍል ውስጥ አልያም ቤታቸው አንብበው ነው፡፡ ቅንጫቢውን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ጅምር ዓረፍተነገሮችን አሟልተው እንዲፅፉ በመጠየቅ ይከናወናል (Hişmanoğlu 2005፣ 58)፡፡ ይህ ተግባር የመፃፍ ክሂልን ከማዳበሩም በላይ የቋንቋውን መዋቅር ለማለማመድ ይረዳል፡ ፡ እንደ Lazar (1990፣ 211) አገላለፅ በታሪኩ ውስጥ የተፈፀሙ ድርጊቶችን ምክንያት እንዲገልፁ በሚያስችል መልኩ ጅምር ዓረፍተነገሮችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህ ተግባር ሁለት ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ተማሪዎች የምክንያት እና ውጤት ግንኙነትን እንዲረዱ ያስችላቸዋል፡፡ ሁለተኛው ጠቀሜታ ደግሞ ሁነቶችን በጊዜ ቅደም ተከተል የማቅረብ ልምዳቸውን ያዳብራል፡፡

## 2. ቁልፍ ቃላት እና ዓረፍተነገሮች

እንደCollie እና Slater (1987፣ 18) አገላለፅ ይህ ተግባር ተማሪዎች ቅንጫቢውን ከማንበባቸው በፊት የሚከናወን ሲሆን እንዳስፈላጊነቱ በቃላት ወይም በዓረፍተ ነገሮች ሊካሄድ ይችላል፡፡ በቃላት የሚከናወን ከሆነ መምህራን ከቅንጫቢው መጀመሪያ ክፍሎች (አንቀፆች) ውስጥ ተለቅመው የወጡ ቃላትን ለተማሪዎች ይሰጣሉ፡፡ ተማሪዎችም ቃላቱን ተጠቅመው እንዴት አንድ ታሪክ ፈጥረው መፃፍ እንደሚችሉ ይነጋገራሉ፡፡ ከዚያም ቃላቱን አቀናጅተው አንድ ወጥ ታሪክ ይፅፋሉ፡፡ በመቀጠልም የየቡድኑ ስራ ለክፍሉ ይቀርባል፡፡ የዚህ ተግባር ጠቀሜታ የቃላት እና የፅሁፍ ችሎታን ያዳብራል፡፡ ልምምዱ በዓረፍተነገሮች በሚካሄድ ጊዜ የቅንጫቢውን ዋና ዋና ሀሳብ የያዙ ዓረፍተነገሮችን ለተማሪዎች በመስጠት ያንን ተመርኩዘው አንድ ታሪክ እንዲፅፉ ይበረታታሉ፡፡ ከዚያም ቁልፍ ቃላትን ወይም ዓረፍተነገሮችን ተጠቅመው ያዋቀሩትን ታሪክ ለክፍሉ ያቀርባሉ፡፡ በመጨረሻም ቅንጫቢውን እንዲያነቡ ይደረጋል፡፡ እነሱ ከፃፉት ታሪክ ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት በተመለከተ ውይይት ይካሄዳል፡፡

## 3. ቅድመ ታሪክን መፃፍ

Collie እና Slater (1987፣ 31) ይህ ክንውን ተግባራዊ የሚሆነው ተማሪዎች ቅንጫቢውን ካነበቡ ወይም ካዳመጡ በኋላ መሆኑን ይገልፃሉ ፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ካነበቡት ወይም ካዳመጡት ቅንጫቢ በፊት ያለውን ታሪክ በቡድን፣ በጥንድ ወይም በግል ገምተው እንዲጽፉ በማድረግ ይከናወናል፡፡ ይህ ተግባር በቡድን ወይም በጥንድ ቢከናወን ተማሪዎች በሰፊው እንዲወያዩ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች በቀረበው ቅንጫቢ ውስጥ ገፀባህሪያት የነበሩበትን ግጭት መሰረት በማድረግ ያ ከመሆኑ በፊት ምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እንደነበሩ በመገመት ቅድመ መነሻ ታሪክን ይፅፋሉ፡፡

## 4. የፈጠራ ምልልስ መፃፍ

ይህ ተግባር የሚከናወነው የገፀባህሪያትን ምልልስ የያዘ ስራ በማቅረብ ነው፡፡ ይኸውም የተወሰነውን ክፍል መምህራን ካነበቡ በኋላ ንባቡን በማቆም ተማሪዎች በዚያ ሁኔታ ገፀባህሪያት ምን ሊሉ እንደሚችሉ በመገመትና ገፀባህሪያቱን በመወከል ምልልስ እንዲፅፉ በማድረግ ነው፡፡ ምልልሱን ወደ መጻፉ ስራ መግባት ያለባቸው ገፀ ባህሪያቱን በበቂ ሁኔታ አውቀዋቸው ሊሆን ይገባል፡፡ ተግባሩ በቡድን አልያም በጥንድ ሊከናወን ይችላል፡፡

በጥንድ ሲከናወን የተለመደው የምልልስ አፃፃፍ ዘዴ ተማሪዎች ምንም አይነት ቃላዊ የሀሳብ ልውውጥ ሳያደርጉ ምልልሱን እንዲፅፉ በማድረግ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው መምህሩ የገፀባህሪውን ንግግር በንባብ አቅርቦ ንባቡን ይገታል፤ ከዚያም ተማሪዎች ቀጣዩን ምላሽ እንዲፅፉ በማድረግ ነው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ወረቀቱን (ምልልሱ የተፃፈበትን) ይለዋወጡና ሀሳባቸውን ቀጥለው ይፅፋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ምልልሱ ይቀጥላል፡፡ ተማሪዎች በምልልሱ ከጓደኞቻቸው ያላሰቡትን ምላሽ ስለሚያገኙ ልምምዱ አጓጊና አስደሳች ይሆናል፡፡ ምልልስ መፃፍ ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት ከገፀባህሪው አመለካከት አንፃር ለመመርመር ያስችላቸዋል (Collie እና Slater 1987፣ 49)፡፡

## 5. ትንበያን መጻፍ

ትንበያን የመፃፍ መልመጃዎች የሚሰሩት ቅንጫቢውን በሁለት ክፍሎች በመክፈል ነው፡፡ ተማሪዎች የቅንጫቢውን የመጀመሪያ ክፍል ካነበቡ በኋላ ያንን መሰረት አድርገው ሊሆን ይችላል ብለው የሚገምቱትን ታሪክ ወይም ቀጣዩን ክፍል አሟልተው እንዲፅፉ ይጠየቃሉ፡፡ በመቀጠልም ከቀጣዩ ክፍል ጋር ይበልጥ ተቀራራቢነት ያላቸውን የጥቂት ተማሪዎች ፅሁፍ በመውሰድ በዚያ ላይ መወያየት ያስፈልጋል (በድሉ 2007፣111-112)፡፡

## 6. ፅሁፍን ማሳጠር

ፅሁፍ ማሳጠር አንድ ፅሁፍ ያነሳውን ርዕሰ ጉዳይ በሰፊው በመቃኘት የፅሁፉን ፍሬ ነገር ጨምቆ በማውጣት በሚፈለገው መጠን በማሳጠር በራስ አገላለፅ እንደገና መፃፍ ነው፡፡ የፅሁፉ ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በማተኮር ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የፅሁፉን ፍሬ ነገር በሚገባ መረዳትን ይጠይቃል፡፡ በዚህ ስር የሚካተቱ ልዩ ልዩ ፅሁፍን የማሳጠር ዘዴዎች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

### ሀ. ማጠቃለያን ማጠቃለል

ማጠቃለያን ማጠቃለል ተማሪዎች ያሳጠሩትን ፅሁፍ በተደጋጋሚ መልሰው የሚያሳጥሩበት ሂደት እንደሆነ Collie እና Slater (1987፣ 49) ይገልፃሉ፡፡ በመጀመሪያ ተማሪዎች የተመረጠውን ቅንጫቢ እንዲያነቡ ማድረግ በመቀጠልም የክፍሉን ተማሪዎች በቡድን በመክፈል የመጀመሪያውን የማሳጠር ተግባር እንዲያከናውኑ መመሪያ መስጠት (ለምሳሌ፡- ፅሁፉን በሰማኒያ ቃላት እንዲያሳጥሩ)፣ በመቀጠልም አንዱ ቡድን ከሌላው

ቡድን ጋር የሰሩትን በማቀያየር ያጠረውን ፅሁፍ እንደገና እንዲያሳጥሩ ማበረታታት (በሰማኒያ ቃላት ያጠረውን በአርባ ቃላት ማሳጠር)፡፡ በዚህ ሁኔታ ስራው በጋራ ውይይት እየተካሄደበትና ማሻሻያዎች እየተጨመሩበት እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

### ለ. አያያዦችን በመጠቀም ማጠቃለያ መፃፍ

እንደ Collie እና Slater (1987፣ 49) ይህ ክንውን ሲካሄድ ተማሪዎች በመጀመሪያ ቅንጫቢውን ያነባሉ፡፡ ከዚያም በርካታ ቁጥር ያላቸውን አያያዥ ቃላት በደብተራቸው እንዲፅፉ ይደረጋል፡፡ ከፃፏቸው አያያዦች መካከል የተወሰኑትን በመምረጥ ወይም በመምህሩ የተዘጋጀ እጣ በማውጣት ይከናወናል፡፡ መምህሩ በርካታ አያያዦችን በወረቀት ላይ በመፃፍ የሚፈለገውን ያህል ቁጥር ተማሪዎች እንዲያነሱ ማድረግ ይችላል፡፡ በመጨረሻም አያያዦቹን ተጠቅመው ያነበቡትን ቅንጫቢ በሚፈለገው መጠን ያሳጥራሉ፡፡ ከደረሷቸው አያያዦች መካከል ለስራው የማይጠቅሟቸው ካሉ ምክንያታቸውን ገልፀው ሌላ መቀየር እንደሚችሉ ይነገራቸዋል፡፡ ይህ ተግባር ተማሪዎች ሀሳብን የማቀናጀት ችሎታቸው የዳበረ እንዲሆን ይረዳቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ድርሰት ለመፃፍ የመዘጋጃ ተግባር በመሆን ያገለግላል፡፡

## 7. የአፋልጉኝ ማስታወቂያ

ይህን በተመለከተ Collie እና Slater (1987፣ 56) ሲገልፁ ተግባሩ የሚከናወነው ተማሪዎች ቅንጫቢውን ካነበቡ በኋላ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ ናሙና እንዲያዘጋጁ በመጠየቅ ነው፡፡ በአነበቡት ቅንጫቢ ውስጥ ካሉት ገጸባህሪያት አንዱን በመውሰድ መልኩን እድሜውን እንዲሁም በጠፋበት ወቅት የለበሰውን ልብስ ወዘተ. በመግለፅ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ እንዲፅፉ ይደረጋል፡፡

## 8. ደብዳቤ መፃፍ

አንድ ገፀባህሪ ለተለያዩ ገፀባህሪት ደብዳቤ ሊፅፍ ይችላል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች አንዱን ገፀባህሪ በመወከል ለሌላ ገፀባህሪ ማለትም ለእናት፣ ለአባት፣ ለልጆች፣ ለወንድም፣ ለጓደኛ ወዘተ. ደብዳቤ እንዲፅፉ ይጠየቃሉ፡፡ በተመሳሳይ ሌላው ገፀባህሪ ለሌሎች ገፀባህሪያት ይፅፋሉ፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ከዋና ዋና ገፀባህሪያት አንዱን በመምረጥ እሱን መሰረት አድርገው ደብዳቤ እንዲፅፉ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም የፃፉትን ደብዳቤ

ተቀያይረው በማንበብ የተፃፈለትን ገፀባህሪ በመወከል ምላሽ ይፅፋሉ (Collie እና Slater 1987፣ 74)፡፡

## 9. የድረሱልን ጥሪ መፃፍ

ይህ በተራ ቁጥር ስምንት ከቀረበው ጋር የሚመሳሰል ሲሆን ልዩነቱ የደብዳቤው ይዘት ላይ ነው፡፡ Collie እና Slater (1987፣ 51) ይህን ተግባር ለማለማመድ የሚመረጠው ስራ ገፀባህሪው/ያት በተለያዩ ምክንያቶች ችግር ውስጥ ሲገባ/ቡ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ ተማሪዎች ራሳቸውን በገፀባህሪያቱ ቦታ በማስቀመጥ ለችግሩ መፍትሄ ሊሰጣቸው ለሚችል አካል/ገፀባህሪ/ ደብዳቤ/ማስታወሻ እንዲፅፉ ይበረታታሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ Hişmanoğlu (2005፣ 59) ችግር ውስጥ ለገባ አንድ ገፀባህሪ ተማሪዎች ራሳቸውን ወክለው በደብዳቤ ምክር እንዲሰጡት በማድረግ የመፃፍ ክሂልን ማለማመድ እንደሚቻል ይገልፃሉ፡፡

## 10. የውሳኔ ነጥቦችን መፃፍ

ይህን ተግባር ለማለማመድ ጥያቄዎች የሚቀርቡት ‹‹ለምን›› የሚለውን መጠይቀ ቃል በመጠቀም ነው፡፡ በዚህ መልክ ቅንጫቢውን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች አረፍተነገር እንዲመሰርቱ ወይም አንቀፅ እንዲገነቡ ይጠየቃሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ገፀባህሪ ‹ሀ› ይህን ውሳኔ ለምን የወሰነ ይመስላችኋል? ገፀባህሪ ‹ሀ› ገፀባህሪ ‹ለ› ለምን ገደለው? የሚሉ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህን ተግባር ማለማመድ ይቻላል Collie እና Slater (1987፣ 47)፡፡

## 11. ህጎችን ማውጣት

ይህ ተግባር ተማሪዎች በቡድን የሚያከናውኑት ነው፡፡ ይኸውም ያነበቡትን ቅንጫቢ መሰረት በማድረግ በተወሰኑ ሁኔታዎች ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ህግ በፅሁፍ ያዘጋጃሉ፡፡ ህጉን የሚያዘጋጁት ራሳቸውን በጉዳዩ በማስገባት አልያም መሆን አለበት ብለው የሚያምኑትን ሀሳብ በመመርኮዝ ነው (Collie እና Slater 1987፣ 62)፡፡

ከላይ በዝርዝር የቀረቡ ተግባራት አብዛኞቹ በጥንድ እና በቡድን የሚሰሩ ናቸው፡፡ ይህ በመሆኑ ተማሪዎች እርስበርስ ተረዳድተው የመፃፍ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይረዳል፡፡ በዚህም ልምድ ስለሚለዋወጡ የመፃፍ ክሂላቸውን ለማዳበር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

ይህን በተመለከተ Collie እና Slater (1987፣ 10) በቡድን እና በጥንድ የሚሰሩ ተግባራት የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ያዳብራሉ። ልምድ መጋራታቸውም በግል የሚከናወኑ ተግባራትን በፍላጎት እና በራስ ተነሳሽነት እንዲሰሩ ያግዛቸዋል በማለት ያስረዳሉ።

## 2.8. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው ስራዎችን ለመቃኘት ተችሏል። ይኸውም አንድ በትምህርታዊ ጉባኤ ላይ የቀረበ ጥናት እና ሰባት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች ናቸው። ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ከተሰሩት ምርምሮች መካከል ሁለቱ በመማሪያ መጻሕፍት የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን አመራረጥ እና አደረጃጀት የሚመለከቱ ናቸው። አንዱ ደግሞ የስነፅሁፋዊ ስራዎች አተገባበር ፍተሻ ላይ ትኩረቱን ያዋለ ነው። ሌሎቹ አራት ጥናታዊ ፅሁፎች እስካሁን ከተጠቀሱት በይበልጥ ለዚህ ጥናት ቅርበት ያላቸው ሲሆን ስነፅሁፍ ለቋንቋ ትምህርት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ የመፈተሽ ዓላማ ያላቸው ናቸው። እነዚህ ስራዎች እንደሚከተለው ይቃኛሉ።

በትምህርታዊ ጉባኤ ላይ የቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ፈቃደ (1991) ‹‹ አንዳንድ ነጥቦች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ስለመማሪያ መፅሀፍ እና የስነፅሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት (1944-1983) ›› በሚል ርእስ የቀረበ ጥናት ሲሆን በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ገልፀው በስርአተ ትምህርቱ የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን በመጠቆም ስነፅሁፋዊ ስራዎች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቢካተቱ በተለይም ክሂሎችን ለማስተማር ከፍተኛ ፋይዳ እንዳላቸው ገልጸዋል።

ዳዊት (2000) ‹‹ በደቡብ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋንቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች ጥንካሬና ድክመት በመለየት የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆም ነው። ጥናቱ ገላጭ ምርምር ሲሆን መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም የሰነድ ምርመራ፣ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ናቸው። የጥናቱ ውጤት እንደሚያስረዳው በመማሪያ መፃሕፍቱ

ውስጥ ለስነፅሁፋዊ ስራዎች የተሰጠው ሽፋን አነስተኛ ነው፡፡ እንዲሁም የተመረጡት ብዙዎቹ ስነፅሁፋዊ ይዘቶች የአመራረጥ መስፈርቶቹን የሚያሟሉ ሆነው አልተገኙም፡፡

አስቴር (2003) ‹‹ ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አመራረጥ እና አደረጃጀት ፍተሻ ›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በተጠቀሱት መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን አደረጃጀትና አመራረጥ መፈተሽ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም የሰነድ ፍተሻ፣ ቃለመጠይቅና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

ከላይ የቀረቡት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉት ስነፅሁፍ ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸው ልዩነት ሰፊ ነው፡፡ ምክንያቱም የነዚህ ጥናቶች ትኩረት በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አመራረጥ እና አደረጃጀት የሚፈትሽ በመሆኑ ነው፡፡

ሰለሞን (2003) ‹‹ ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍሎች መማሪያ መፃሕፍት ማሳያነት ›› በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ አላማ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ ልቦለዶች ከአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ እና ከጥሩ ምንባብ ባህሪያት አንፃር መፈተሽ እና መተንተን ነው፡፡ ጥናቱ የተጠቀማቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ፣ የሰነድ ፍተሻ እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ በውጤቱም የየክፍል ደረጃው መምህራን ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎችን ዓላማ በአግባቡ ለይተው ተግባራዊ እንደማያደርጉ በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡ በመማሪያ መፃሕፍቱ ውስጥ የሚገኙ ልቦለዶች ከጥሩ ምንባብ ባህሪያት አንፃር መልካም እንደሆኑ ከጥናቱ ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት በሰለሞን ከተካሄደው ጋር የሚያመሳሰለው የስነፅሁፍ ስራ ላይ በማተኮሩ ነው፡ ፡ ልዩነቱ ደግሞ የሰለሞን ጥናት ትኩረቱ የስነፅሁፋዊ ስራዎችን አተገባበር እና በመማሪያ መፃሕፍቱ የተካተቱ ልቦለዶች አመራረጥ መስፈርቱን የሚያሟሉ መሆናቸውን የሚፈትሽ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና የሚመረምር ነው፡፡

ዘመንፈስ (1991) "በስነፅሁፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት" በሚል ርዕስ ጥናት አድርገዋል፡፡ ይህ ጥናት ስነፅሁፍን በተመለከተ ከተሰሩ የመመረቂያ ፅሁፎች ቀዳሚው ነው፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በአጭር ልቦለድ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ የመግለፅ ችሎታቸውን ማዳበራቸውን በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመረጃ መተንተኛነት ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ ለጥናታቸው ይረዳቸው ዘንድ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ቅድመ እና ድህረ ፈተና እንዲሁም የፅሁፍ መጠይቅ ተጠቅመዋል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚጠቁመው በአዲሱ ዘዴ (በፈጠራዊ ዘዴ) የተማሩ የተጠኚ ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ እንዲማሩ ከተደረጉት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ሀሳባቸውን በፅሁፍ በመግለፅ ረገድ የተሻሉ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማሳደግ ስነፅሁፍን በመጠቀም ማስተማር የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው አስተያየት ሰንዝረዋል፡፡

ይህ ጥናት በዘመንፈስ ከተካሄደው የሚመሳሰለው ስነፅሁፍን መሰረት ያደረገ በመሆኑ፣ በተተኳሪ ት/ቤት እና በተማሪዎች የክፍል ደረጃ ነው፡፡ ከልዩነቶቹ መካከል አንዱ በዚህ ስራ የተመረጠው የስነፅሁፍ ዘርፍ አጭር ልቦለድ ሲሆን በእኔ ስራ ደግሞ ረዥም ልቦለድ ነው፡፡

ጌትነት (2001) ‹‹ በረጅም ልብ-ወለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ›› በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በረዥም ልቦለድ አማካይነት መፃፍን እና አንብቦ መረዳትን ማስተማር ያለውን ውጤታማነት እና ተተግባሪነት በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ጥናቱ የተሞከረው በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ ጥናቱ መጠናዊ የምርምር ዘዴን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎችን በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድን በመለየት፣ አጥኚው የሙከራ ቡድኑን በፈጠራዊ ዘዴ ያስተማረ ሲሆን መደበኛዋ መምህርት ደግሞ የቁጥጥር ቡድኑን በነባሩ ዘዴ አስተምራለች፡፡ በዚህ መሰረት ውጤቱ እንደሚያመለክተው በፈጠራዊ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡

የጌትነት ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስነፅሁፍን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር ያለውን ውጤታማነት የሚፈትሽ በመሆኑ እና ከስነፅሁፍ ስራዎች የተጠቀመው ረዥም ልብ ወለድን በመሆኑ ነው፡፡ ከላይ በተገለፁት ጉዳዮች ተመሳስሎ ቢኖራቸውም ልዩነታቸው ሰፊ ነው፡፡ እነዚህ ጥናቶች በጊዜ በቦታ እና በክፍል ደረጃ ይለያያሉ፡፡ ይኸውም የጌትነት ስራ በምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በ2001 የተካሄደ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በየካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ በ2010 የተካሄደ ነው፡፡

ታዬ (2002) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፍ ባቀረቡት ጥናት በፈጠራ ፅሁፎች አማካይነት ድርሰትን ማስተማር ያለውን ፋይዳ አጥንተዋል፡፡ ጥናቱ በ10ኛ ክፍል ኢ አፈፌት ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ነው፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ ተማሪዎችን በሙከራ እና በቁጥጥር ክፍል ከፍለው ሲያስተምሩ ቆይተዋል፡፡ በፈጠራ ስራ ሲማሩ የቆዩት ተማሪዎች (የሙከራ ቡድን) መደበኛውን ትምህርት ሲማሩ ከቆዩት ተማሪዎች (የቁጥጥር ቡድን) በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የተሻሉ መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም በፈጠራ ፅሁፎች ድርሰትን ማስተማር ፋይዳው የጎላ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

የኔ ጥናት በታዬ ከተካሄደው ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ስነፅሁፍን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥን አልሞ የተነሳ በመሆኑ እና ከስነፅሁፍ ዘርፎች መካከል ረዥም ልቦለድ ላይ ማተኮሩ ነው፡፡ ጥናቱ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ከኔ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም ልዩነቶች ግን አሉት፡፡ በቦታ እና በጊዜ የተለየ መሆኑ ከልዩነቶቹ መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡ ይኸውም በቦታ በሰንዳፋ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ የተካሄደ ሲሆን ጊዜውም በ2001 ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የተካሄደው በየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት በ2010 ነው፡፡ ሌላው ልዩነት የተተኳሪ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ሲሆን በታዬ ጥናት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በእኔ ጥናት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች መሆናቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የታዬ ጥናት ኢ አፈፌት ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ነው፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ጥናታቸውን ያቀረቡት ነብዩ (2005) ናቸው፡፡ የተካሄደው ጥናት ‹‹በግጥም አማካይነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ችሎታን ማዳበር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት›› በሚል

ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ዋነኛ አላማ በአማርኛ የአንብቦ መረዳት እና የመፃፍ ችሎታ ለማዳበር ግጥም ያለውን ሚና በሙከራ ማረጋገጥ ነው፡፡ ጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና፣ የፅሁፍ መጠይቅ እና ኢ መደበኛ ቃለመጠይቅ ተጠቅሟል፡፡ ተግባራዊ ያደረገው የመረጃ መተንተኛ ስልት መጠናዊ የምርምር አቀራረብ ነው፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው በአዲሱ ዘዴ የተማሩ ተጠኚ ቡድን ተማሪዎች በተለመደው ዘዴ እንዲማሩ ከተደረጉት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማሳደግ ስነፅሁፍን በመጠቀም ማስተማር የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው አስተያየት ሰንዝረዋል፡፡

የነብዩ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ስነፅሁፍን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን የማስተማር ውጤታማነት ማረጋገጥን አልሞ የተነሳ በመሆኑ እና በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ነው፡፡ በተጠቀሱት ጉዳዮች የሚመሳሰል ቢሆንም መሰረታዊ ልዩነቶች አሉት፡ ፡ ይኸውም የነብዩ ጥናት ግጥምን በምንጭነት የተጠቀመ ሲሆን የእኔ ጥናት ግን ረዥም ልቦለድን በመጠቀሙ ይለያል፡፡ እንዲሁም ጥናቱ በአንብቦ መረዳት እና በመፃፍ ክሂል ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ትኩረቱ በመፃፍ ክሂል ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥናቶቹ ከተከናወኑበት ጊዜ፣ ቦታ እና የተማሪዎች የክፍል ደረጃ አንፃር ልዩነት አላቸው፡፡ የነብዩ ጥናት የተካሄደው በደንበጫ ከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በ2005 ዓ.ም ሲሆን የእኔ ግን በየካቲት 12 መሰናዶ ት/ቤት፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በ2010 የተካሄደ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ከተዘረዘሩት ጥናቶች (ዘመንፈስ፣ ጌትነት፣ ታዬ እና ነብዩ) ጋር በዋናነት የሚለየው ጥናቶቹ ስነፅሁፋዊ ስራዎቹን በማቅበቢያ ስነዘዴው ላይ በማተኮራቸው ነው፡፡ ይኸውም በእነዚህ አጥኚዎች የተካሄደው ጥናት ለሙከራ እና ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመስጠትና ሁለቱን ቡድኖች በተለያዩ ዘዴዎች በማስተማር ማለትም የሙከራ ቡድኑን በፈጠራዊ ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ በነባሩ ዘዴ በማስተማር የተካሄዱ በመሆናቸው ነው፡፡ ይህ ጥናት ግን የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ለሙከራ ቡድኑ ብቻ በመስጠት ይካሄዳል፡፡

እስካሁን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከጥናቱ ጋር በተገናኘ መልኩ ከመፃፍ ክሂል ምንነት አስፈላጊነት እና አቀራረቦች በመነሳት ከስነፅሁፍ ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶች ጋር በማጣመር

ለማየት ተሞክሯል፡፡ የቋንቋ ትምህርት በስነፅሁፋዊ ስራዎች አማካይነት ቢሰጥ ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን ባለሙያዎቹ ከሰነዘሯቸው ሀሳቦች መረዳት ይቻላል፡፡ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር የሚያስችሉ ስነፅሁፋዊ ስራዎች ምርጫ ምን መምሰል እንዳለበት እና እንዴት ተግባራዊ መሆን እንዳለበት፣ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራት እና አተገባበራቸው ቀርበዋል፡፡ በመቀጠል እነዚህን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን በመምረጥ እና በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ በተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ለማየት ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ንድፍ እና የአጠናን ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ጥናቱ ለመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛነት የተጠቀመው በዋናነት መጠናዊ ዘዴን፣ በአጋዥነት ደግሞ አይነታዊ የምርምር ዘዴን በመሆኑ ቅይጥ ዘዴ (Mixed Methods Research) አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ይህ ዘዴ በአንድ የምርምር ስራ መጠናዊ እና አይነታዊ የምርምር አቀራረቦችን በጣምራ መጠቀም እንደሆነ (Almalk 2016፣ 291) ይገልፃሉ፡፡ በዚህ መሰረት የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤቶች በቲ ቴስት ተተንትነዋል፡፡ ከምልከታ እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎችም በገለፃ ስልት ተተንትነዋል፡፡

ጥናቱ ሙከራዊ የምርምር አይነት ሲሆን በተጠኚ ቡድኖች ላይ አግባብነት ያለው ሙከራ ተካሂዷል፡፡ በጥናቱ የ True Experimental designs አይነት የሆነው የሁለት ቡድን ቅድመ እና ድህረ ሙከራ ፈተና አጠናን ንድፍ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የአጠናን ስልቱን Beaumont (2009፣9) በሚከተለው መንገድ ያስቀምጡታል፡፡

| ቡድን | ቅድመ ሙከራ ፈተና | ኢ- ጥገኛ ተለዋዋጭ | ድህረ ሙከራ ፈተና |
|---|---|---|---|
| የሙከራ | $Y_b$ | X | $Y_a$ |
| የቁጥጥር | $Y_b$ | - | $Y_a$ |

የአጠናን ሂደቱ እንደሚያሳየው በቅድሚያ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖችን በእድል ሰጪ ንሞና ዘዴ በመለየት ቅድመ ሙከራ ፈተና ($Y_b$) ይሰጣል፡፡ በመቀጠልም የሙከራ ቡድኑ ላይ ኢ- ጥገኛ ተለዋዋጩ (X) (የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ) ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በመጨረሻም ለሁለቱ ቡድኖች ድህረ ሙከራ ፈተና ($Y_a$) ይቀርባል፡፡

በዚህ መሰረት የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኖችን በመለየት ቅድመ ትምህርት እና ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፡፡ ቅድመ ትምህርት ፈተናው ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት የተሰጠ ሲሆን ድህረ ትምህርት ፈተናው የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የረዥም ልቦለድ

ቅንጫቢዎችን መሰረት በማድረግ መፃፍን ከተለማመዱ በኂላ ነው። ይህም ውጤታቸው መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ አስችሏል።

## 3.2. የተጠኚዎች አመራረጥ

### 3.2.1. የትምህርት ቤት አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ በሚገኘው የካቲት 12 መሰናዶ የመንግስት ትምህርት ቤት ነው። ይህ ትምህርት ቤት የተመረጠው አመቺ የንሞና ዘዴን በመጠቀም ነው። ያለው (2004፣132) እና Cohen, Manion እና Morrison (2005፣ 102) አንድ ተመራማሪ በቅርበት ባገኛቸውና ጥናቱን ለማካሄድ አመቺ በሆኑለት ሰዎች ወይም ነገሮች ላይ ተመርኩዞ ምርምሩን ሊያካሂድ እንደሚችል ይገልፃሉ። ጥናቱ ሙከራዊ በመሆኑና ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ ስለሆነ መደበኛውን የትምህርት ጊዜ የሚሻማ ነው። ስለዚህ የዕጣ ንሞና ዘዴን በመጠቀም በሌሎች ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናቱን ማካሄድ አልተቻለም። አጥኚዋ በዚሁ ትምህርት ቤት በማስተማር ላይ የምትገኝ በመሆኗ እና አስተዳደሩ እና መምህራን ጥናቱ እንዲካሄድ የፈቀዱ ስለሆነ መረጃ ለመብሰብ አመቺ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም በዚህ ትምህርት ቤት ጥናቱን ማካሄድ ለጥናቱ ውጤት ማማር አስተዋፅዖ ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል።

### 3.2.2. የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ውስጥ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ ። ጥናቱ በሚካሄድ ወቅት የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለብሔራዊ ፈተና ዝግጅት የሚያደርጉበት ጊዜ በመሆኑ ጥናቱ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተካሂዷል።

### 3.2.3. የተማሪዎች አመራረጥ

በዚህ ትምህርቤት አስራ ስምንት የ11ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች ሲኖሩ በቅድሚያ ቀላል የእጣ ዘዴን በመጠቀም በናሙና ጥናት (Pilot Study) ተሳታፊ የሚሆን አንድ ክፍል ($11^{09}$) ተመርጧል። በመቀጠልም የናሙና ጥናት ተማሪዎችን በማግለል ቀላል የእጣ ዘዴን በመጠቀም $11^{07}$ እና $11^{18}$ ተመርጠዋል። ከዚያም የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድኑን ለመለየት ሁለቱ ክፍሎች በእጣ ተለይተው $11^{07}$ የሙከራ፣ $11^{18}$ የቁጥጥር ቡድን ሆነዋል።

## 3.3. በረዥም ልቦለድ አማካነት መፃፍን የማስተማሪያ/የማሰልጠኛ ማቴሪያል

ለሙከራ ቡድን የተዘጋጀው የማስተማሪያ ማቴሪያል የተዘጋጀው የ11ኛ ክፍል መርሀ ትምህርትን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ማቴሪያሉ በረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማካይነት ተማሪዎች ልምምድ ሲያደርጉ በቅድመ መፃፍ፣ በጊዜ መፃፍ እና በድሕረ መፃፍ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት የያዘ ሲሆን ልምምዱ የሚከናወነው ለአንድ ወር (አስራ ሶስት ክፍለጊዜያት) ነው፡፡ (በአባሪ አንድ ገፅ 74 ይመልከቱ፡፡) ይህንን የማስተማሪያ ማቴሪያል ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል እለታዊ የትምህርት ዝግጅት ቀርቧል፡፡ (በአባሪ አንድ ገፅ 91 ይመልከቱ፡፡)

### 3.3.1. የቅንጫቢዎች አዘገጃጀት

የጥናቱ አላማ ከግብ ይደርስ ዘንድ ለማስተማሪያነት የሚውሉ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ቅንጫቢዎችን ለመምረጥ ደግሞ በቅድሚያ የረዥም ልቦለድ ስራዎች መመረጥ አለባቸው፡፡ በመሆኑም በምዕራፍ ሁለት 2.5 ስር የተካተቱት የስነፅሁፍ ስራዎች መምረጫ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ ስድስት የረዥም ልቦለድ ስራዎች ተመርጠዋል፡፡ እነዚህን ልቦለዶች ለመምረጥ ሁለት በፎክሎር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በመቀጠልም ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በአጥኚዋ ከልቦለድ ስራዎቹ ውስጥ ሰባት ቅንጫቢዎች ተመርጠዋል፡፡ ቅንጫቢዎቹ በአማካሪ መምህር ታይተው ተገቢነታቸው ተረጋግጧል፡፡

ከዚያም እነዚህን ቅንጫቢዎች በናሙና ጥናቱ ለተሳተፉ የ11$^{09}$ ተማሪዎች በመስጠት ከሰባቱ አምስቱን እንዲመርጡ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት አብዛኞቹ ተማሪዎች ሶስና፣ ባለውለታ፣ የጳጉሜን ሶስት ገፅታ፣ ቀጠሮ እና የጠፋ ሲገኝ በሚል ርዕስ የቀረቡትን ቅንጫቢዎች መርጠዋል፡፡ እነዚህን ቅንጫቢዎች የሚመለከት ዝርዝር መግለጫ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አንድ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ አንድ፡- ለማስተማሪያነት የዋሉ ቅንጫቢዎች መግለጫ

| ተ.ቁ | ቅንጫቢ | የቅንጫቢ ርዕስ | የደራሲ ስም | የመፅሀፍ ርዕስ | ዓ.ም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቅንጫቢ አንድ | ሶስና | ምህረት ደበበ | የተቆለፈበት ቁልፍ | 2005 |
| 2 | ቅንጫቢ ሁለት | ባለውለታ | የዝና ወርቁ | የደራሲዋ ፋይል | 2002 |
| 3 | ቅንጫቢ ሶስት | የጳጉሜን ሶስት ገፅታ | ይስማዕከ ወርቁ | ዴርቶጋዳ | 2001 |
| 4 | ቅንጫቢ አራት | ቀጠሮ | ምህረት ደበበ | የተቆለፈበት ቁልፍ | 2005 |
| 5 | ቅንጫቢ አምስት | የጠፋ ሲገኝ | ካሳሁን ንጉሴ | ጥልፍልፍ | 2009 |

### 3.3.2. የመልመጃዎች አዘገጃጀት

የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን መሰረት በማድረግ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበር ልዩ ልዩ ተግባራት ተዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ መልመጃዎች በ2.7 ስር የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ተግባራትን መነሻ በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ተግባራቱ የተዘጋጁት በናሙና ጥናቱ ተሳታፊ የነበሩ ተማሪዎች የመረጧቸውን ቅንጫቢዎች መሰረት በማድረግ ነው፡፡

**ቅንጫቢ አንድ (ሶስና)፡-** ተማሪዎች የልቦለዱን ታሪክ ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት እንዲያሳጥሩ፣ በቅንጫቢው የቀረበውን ታሪክ መሰረት በማድረግ የግለሰቦችን መጥፎ ድርጊት ለማስወገድ የሚረዳ መመሪያ በፅሁፍ እንዲያዘጋጁ እና ጅምር ሀሳቦችን እንዲያሟሉ የሚያለማምዱ ተግባራትን የያዘ ነው፡፡

**ቅንጫቢ ሁለት (ባለውለታ)፡-** ይህን ቅንጫቢ መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ተግባራት ሁለት ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ገፀባህሪን ወክለው ደብዳቤ መፃፍ ሲሆን ሁለተኛው ጥንድ ጥንድ በመሆን የፈጠራ ምልልስ መፃፍን የሚያለማምዱ ናቸው፡፡

**ቅንጫቢ ሶስት (የጳጉሜን ሶስት ገፅታ)፡-** ይህ ቅንጫቢ በገለፃ የአንቀፅ ማስፋፊያ ዘዴ የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች ይህንኑ አስመስለው እንዲፅፉ እና ልቦለዱን ከማንበባቸው በፊት ከልቦለዱ ተመርጠው የወጡ ቁልፍ ዓረፍተነገሮችን መሰረት በማድረግ አንድ ታሪክ መፃፍን እንዲለማመዱ የቀረበ ነው፡፡

**ቅንጫቢ አራት (ቀጠሮ)፡-** የቅንጫቢውን ታሪክ መሰረት አድርገው ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ከሰባ ባላነሱ ቃላት ቀጣዩን ታሪክ አሟልተው እንዲፅፉ ተዘጋጅቷል፡፡

**ቅንጫቢ አምስት (የጠፋ ሲገኝ)፡-** ይህ ተግባር ያነበቡትን ቅንጫቢ መነሻ በማድረግ ቀደም ብሎ የተፈፀመውን ድርጊት የሚያሳይ ታሪክ እንዲፅፉ (ምዕራፍ ዜሮን እንዲያሟሉ)፣ ከተሰጡ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ ድርሰት እንዲፅፉ እና የገፀባህሪውን ቤተሰብ በመወከል የአፋልጉኝ ማስታወቂያ እንዲፅፉ ቀርቧል፡፡

ቅንጫቢዎች ተመርጠው እና እነሱን መሰረት አድርገው የተለያዩ መልመጃዎች ከተዘጋጁ በኋላ የ11[09] ክፍል ተማሪዎችን ለአንድ ሳምንት በረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን በማለማመድ የናሙና ጥናት (Pilot Study) ተካሂዷል፡፡ ይህም የመመሪያዎችን ግልፅነት እና የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ብቃት በመፈተሽ ማሻሻያ ለማድረግ አስችሏል፡፡

(ለማስተማሪያነት የዋሉ ቅንጫቢዎችን እና መልመጃዎችን በአባሪ አንድ ይመልከቱ፡፡)

## 3.4. የሙከራ ቡድን ተማሪዎችን አሰልጣኝ መምህር አመራረጥ

ጥናቱ ሙከራዊ በመሆኑ ለሙከራ ቡድኑ ከላይ የተገለፀውን የማሠልጠኛ ማቴሪያል በልምምድ ተግባራዊ ለማድረግ አሠልጣኝ መምህር መምረጥ የግድ ነው፡፡ በመሆኑም አመቺ የንሞና ዘዴን በመጠቀም በተመረጠው የመማሪያ ክፍል በማስተማር ላይ የነበረችውን መምህርት ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች አሠልጣኝ እንድትሆን ተመርጣታለች፡ ፡ አሠልጣኝ መምህሯ ከማሠልጠኗ አስቀድሞ ስለምታሠለጥነው ትምህርት ለስምንት ሠዓታት ያህል ስልጠና ተሠጥቷታል፡፡

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነሱም ምልከታ፣ ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

### 3.5.1. ምልከታ

ምልከታ ተጠኚዎች የሚያደርጉትን እና የሚናገሩትን በቅርበት ሆኖ በማየት እና በመስማት መረጃ የሚሰበሰብበት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን መሰረት በማድረግ በሙከራ ቡድን ክፍል ከ26/06/10 እስከ 21/07/10 የተካሄደውን የመማር ማስተማር ሂደት በመዘገብ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ይህም ለጥናቱ በተመረጠው ክፍል ትምህርቱ በታቀደው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ አገልግሏል፡፡ (የምልከታ ማስታወሻውን በአባሪ ሁለት ገፅ 94 ይመልከቱ፡፡) ከምልከታ አመዘጋገብ አይነቶች ውስጥ ተከታታይ ምልከታ ዘዴን የተከተለ ሲሆን በልምምዱ ወቅት በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ የተከናወኑ ተግባራት በጊዜ ቅደም ተከተል በትረካዊ ገለፃ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡ ምልከታው፣ ቅንጫቢው እንዴት ቀረበ? የተማሪዎች ተሳትፎ ምን ያህል ነው? የጥንድ እና የቡድን ተሳትፏቸው ምን ይመስላል? በተማሪዎች የመፃፍ ልምምድ ላይ ጎልተው የሚታዩ ችግሮች/ስህተቶች የትኞቹ ናቸው? ተማሪዎች ምን ጠየቁ ምንስ መለሱ? ወዘተ በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ (የምልከታ ቅፅ (check list) በአባሪ ሶስት ገፅ 107 ይመልከቱ፡፡)

(ምልከታው በፎቶ እና በቪዲዮ የተደገፈ ሲሆን ፎቶውን በአባሪ አስራ ሁለት ገፅ 136 ይመልከቱ፡፡)

### 3.5.2. ፈተና

ፈተና፣ የተፈታኞችን አዕምሯዊ ወይም ስነባህሪያዊ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መሳሪያ ሲሆን የሚዘጋጀውም ተፈታኙ ያለውን እውቀት፣ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ክሂል አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ ነው (ያለው 2004፣ 189)፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ሆኖ የሚያገለግለው ፈተና ሲሆን ይህም የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለመፈተሽ የሚውል ነው፡፡ ስለዚህ ለሙከራ እና ለቁጥጥር

ቡድን ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቷል፡፡ (ቅድመ እና ድህረ ሙከራ ፈተናዎችን በአባሪ አራት ገፅ 108 ይመልከቱ፡፡

### 3.5.2.1. የፈተና አዘገጃጀት

የቅድመ ትምህርት ፈተናው ከተሰጡት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ የአንቀፅ ማስፋፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም አንቀፅ እንዲገነቡ፣ ድህረ ፈተናው ደግሞ ከተሰጡ ርዕሶች መካካል አንዱን መርጠው ድርሰት እንዲፅፉ የተዘጋጀ ነው፡፡ ፈተናው በአጥኚዋ የተዘጋጀ ሲሆን 11ኛ ክፍል በሚያስተምሩ ሁለት የቋንቋ መምህራን እና በአማካሪ መምህር ተገምግሞ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ማሻሻያውም ሁለት ድርሰት የመፃፊያ ርዕሶች በሌላ እንዲተኩና ለፈተናው የተፈቀደው ጊዜ 1፡00 እንዲሆን ነው፡፡ የቅድመ እና ድህረ ሙከራ ፈተናዎች ርዕስ፣ ዓላማ፣ የማጠናቀቂያ ሰዓት እና ፈተናው የተሰጠበት ቀን እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ሁለት ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዝ ሁለት**፡- የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና መግለጫ

| የፈተናው አይነት | የፈተናው አላማ | ርዕስ | የተፈቀደው ሰዓት | ፈተናው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ሙከራ ፈተና | ያላቸውን ችሎታ ለመለካት | ከተዘረዘሩት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ አንቀፅ መፃፍ | 1፡00 | 19/06/2010 |
| ድህረ ሙከራ ፈተና | ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ለመለካት | ከተዘረዘሩት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ ድርሰት መፃፍ | 1፡00 | 24/072010 |

### 3.5.2.2. የፈተና አስተራረም

የፅሁፍ ፈተናዎች ላይ ሊከሰት የሚችለውን የእርማት ልዩነት ችግር ለመቅረፍ በዚሁ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው ሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ፈተናዎችን በማረም ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ለአራሚ መምህራን የማረሚያ መስፈርቱን እና የውጤት አሰጣጡን በተመለከተ ለሶስት ሰዓት ያህል ገለፃ ተሰጥቷል፡፡ የማረሚ መስፈርቱ

ከፅሁፉ ይዘት፣ አደረጃጀት፣ የቃላት አመራረጥ፣ ሰዋስዋዊነት እና የአፃፃፍ ስርዓታዊነት እንዲሁም ከነጥቦች አጠቃቀም አኳያ የተዘጋጀ ነው፡፡ (አባሪ አስራ አንድ በገፅ 128 ይመልከቱ) እያንዳንዱ ተማሪ የሚያገኘው ውጤትም አራሚዎች የሰጡትን ውጤት በመደመርና ለሶስት በማካፈል ነው፡፡ በአራሚዎች መካከል ያለው የመጣጣም ደረጃ በክሮንባክ ወይም ኮፊሸንት አልፋ (Cronbach alpha, Coefficient alpha) ቀመር ተሰልቶ፣ የቅድመ ትምህርት ፈተናው $11^{07}$ 0.93፣ $11^{18}$ 0.90 የድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ $11^{07}$ 0.89 ፣ $11^{18}$ 0.93 ሆኗል፡፡ ይህም በአራሚዎች መካከል ተጣጣሚነት መኖሩን ያሳያል፡፡ (ቀመሩን እና የተገኘውን ውጤት በአባሪ ሰባት ገፅ 119 ላይ ይመልከቱ፡፡)

### 3.5.3. የፅሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የሚዘጋጀው ፅሁፋዊ መጠይቅ ለሙከራ ቡድን ተማሪዎች ቀርቧል፡፡ (በአባሪ ስምንት ገፅ 121 ይመልከቱ፡፡) መጠይቁ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን ክፍል አንድ የተማሪዎችን ዳራዊ መግለጫ (እድሜ እና ፆታን) የሚጠይቅ ነው፡፡ ክፍል ሁለት አስራ ሶስት ጥያቄዎችን አካቷል፡፡ ይህ ክፍል ድርድር የጥያቄ አቀራረብ (Matrix Questions) ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ አቀራረቡ በርካታ የሬቲንግ ስኬል ጥያቄዎች ሆነው ተመሳሳይ አማራጮች ሲኖራቸው በእያንዳንዱ ጥያቄ ስር በመደርደር ፋንታ በሁሉም ጥያቄዎች ፊት ለፊት አማራጮችን በማመልከት መላሾች እየመረጡ እንዲመልሱ የሚደረግበት እንደሆነ (ያለው 2004፣ 165) ይገልፃሉ፡፡ አማራጮቹ በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አልስማማም እና በፍፁም አልስማማም በሚል ቀርበዋል፡፡

መጠይቁ ተማሪዎች ለጥያቄው መልስ ይሆናል ብለው የሚያምኑበትን የ √ ምልክት በማስቀመጥ እንዲመልሱ ይጋብዛል፡፡ በክፍል ሶስት ጥያቄ 14 እና 15 በሬቲንግ ስኬል (Rating scale) ዘዴ የተዘጋጀ ሲሆን 16 እና 17 ልቅ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከተሰጡት አማራጭ መልሶች መካከል በማክበብ እንዲመልሱ እንዲሁም ክፍት ቦታዎችን በመሙላት ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ይጠይቃል፡፡

መጠይቁ በዚህ መልክ ከተዘጋጀ በኋላ ለተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት በአንድ የቋንቋ መምህር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ኮርስ መምህር እንዲሁም በአማካሪ መምህር ተገምግሟል፡፡ በተሰጡት አስተያየቶች መሰረት ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ አስተያየቶቹ የመመሪዎች ግልፅ አለመሆን፣ የቃላት አመራረጥ እና ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን

ጥያቄዎች በአንድ ላይ ማካተትን የሚመለከቱ ናቸው። ተማሪዎች መጠይቁን ከመሙላታቸው በፊት ስለዓላማው እና አሞላሉን በተመለከተ በአጥኚዋ ገለፃ ተደርጎላቸዋል።

የተሰራጨው መጠይቅ 36 ሲሆን ተማሪዎች በአንድ ክፍለ ጊዜ አጠናቀው እንዲመልሱ ተጠይቀው ሁሉም መጠይቆች ተሰብስበዋል። ከተሰበሰቡት መጠይቆች ውስጥ አንዱ የአሞላል ችግር ያለበት በመሆኑ በትንተናው አልተካተተም።

በፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መልሶችን በሰንጠረዥ በማጠቃለል (የመልሶቹን ማጠቃለያ በአባሪ ዘጠኝ ገፅ 125 ይመልከቱ።) እና የመላሾችን ቁጥር ወደመቶኛ በመለወጥ እንዲሁም አዎንታዊ እና አሉታዊ መልሶችን በመለየት መረጃው ተተንትኗል።

የፅሁፍ መጠይቁን አስተማማኝነት ለመወሰን ክሮንባክ ወይም ኮፊሸንት አልፋ (Cronbach alpha, Coefficient alpha) የአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ አገልግሎት ላይ ውሏል። በአስተማማኝነት ቀመሩ ተሰልቶ የተገኘው ውጤት 0.73 ሲሆን ውጤቱ በመቶ ሲባዛ 73.71 ያስገኛል። ይህ ማለት በመለኪያው (በፅሁፍ መጠይቁ) ከተሰበሰበው መረጃ 73.7 % ያህሉ ተጠኚዎች በትክክል እውቀቱ ኖሯቸው የሰጡት ምላሽ መሆኑን ያሳያል። (የአስተማማኝነት ቀመሩን እና የተገኘውን ውጤት በአባሪ አስር ገፅ 127 ይመልከቱ።)

## 3.6. የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ከምልከታ፣ ከፈተና እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በምዕራፍ አራት ተተንትነዋል። ከምልከታ የተገኘው መረጃ በትረካዊ ገለፃ የተብራራ ሲሆን ከቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና የተገኘው ውጤት ደግሞ በመላምት መፈተሻ ዘዴ ቲ ቴስት (t-test) ተሰልቷል። ከጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ በመለየት ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ በመቶኛ ተሰልቶ ይህንኑ ውጤት በገለፃ ስልት በማስደገፍ መረጃው ተተንትኗል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ በፈተና፣ በምልከታ እና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ ቀርቧል። መረጃዎችንም ከቀረቡ የምርምር ጥያቄዎች አንፃር ለመተንተን ጥረት ተደርጓል። የምርምሩ ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው።

- ረዥም ልቦለድ ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግርን ለማቃለል ሚና አለው?
- መፃፍን በረዥም ልቦለድ አማካይነት የተማሩ ተማሪዎች ውጤት በረዥም ልቦለድ ካልተማሩት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ይሆናል?

እነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኙ ዘንድ ከምልከታ፣ ከፈተና እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ይቀርባሉ።

### 4.1. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ

ከምልከታ የተገኘው መረጃ የተሰበሰበው ከ26/06/10 እስከ 21/07/10 ተግባራዊ ከተደረገው የማስተማር ሂደት ነው። ምልከታው ረዥም ልቦለድን ተጠቅሞ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር ሲታሰብ ቅንጫቢዎቹን እንዴት መተግበር ይቻላል? ልምምዱስ ለተማሪዎች የመፃፍ ክሂል መዳበር ምን ያህል አስተዋፅኦ አለው? ለሚሉ ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ነው። በመሆኑም ተጠኚዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት የተሰጣቸውን ትምህርት ተግባራዊ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ያገለግላል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረቡ ቅንጫቢዎች አምስት ሲሆኑ እነዚህን መሰረት በማድረግ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያስችላሉ ተብለው በምሁራን የተጠቆሙ ተግባራት ቀርበዋል። እነዚህም ጅምር ሀሳቦችን ማሟላት፣ ደብዳቤ መፃፍ ፣ በገለፃ የተስፋፋ አንቀፅ መገንባት፣ የአፋልጉኝ ማስታወቂያ መፃፍ፣ ቅድመ መነሻ እና ትንበያን መፃፍ ወዘተ ናቸው።

ተማሪዎች ወደ መፃፍ ተግባራት ከመግባታቸው በፊት የቀረበላቸውን የልቦለድ ቅንጫቢ አንብበው ሊረዱት የሚገባ በመሆኑ አንብቦ ለመረዳት የሚያስችላቸውን የተለያዩ ተግባራት ለተማሪዎች ማቅረብ ተገቢ ነው። ስለሆነም የስነፅሁፋዊ ስራዎችን አቀራረብ የተሻለ ለማድረግ ቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ እና ድህረ ንባብ ተግባራት በልምምዱ ሂደት

ተተግብረዋል፡፡ እንዲሁም ከመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረቦች ውጤታዊ እና ሂደታዊ አቀራረብን በማጣመር የተመጣጠነ አቀራረብ /Balanced Approach/ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ውጤታዊ አቀራረብን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ለስርዓተ ነጥቦች፣ ለፊደል አጣጣል፣ ለሰዋስዋዊ ህጎች እና ለፅሁፉ አደረጃጀት ትኩረት እንዲሰጡ እዲሁም ሂደታዊ አቀራረብን መሰረት በማድረግ ደግሞ የቅድመ መፃፍ፣ ጊዜ መፃፍ እና የድህረ መፃፍ ተግባራትን እንዲያከናውኑ በቀረበላቸው ትምህርት አማካይነት ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

የመማሩ ሂደት በግል፣ በጥንድ እና በቡድን የተከናወነ በመሆኑ ተማሪዎች ትምህርቱ አሰልቺ እንዳይሆንባቸው አድርጓል፡፡ የቡድን እና የጥንድ ተግባራት ተማሪዎች ከቡድን አባላቱ የተለያዩ ሀሳቦችን እንዲያገኙ የራሳቸውንም ሀሳብ ለሌሎች እንዲያካፍሉ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ እና የግል ተግባራት ደግሞ የመፃፍ ስራ በአብዛኛው የሚከናወነው በግል  በመሆኑ ይህንኑ  እንዲለማመዱ ያስቻላቸው መሆኑ በምልከታው ታይቷል፡፡

ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችል ርዕስ ከመምረጥ ጀምሮ፣ ቢጋር በመንደፍና ድርሰት በመፃፍ ያሳዩት ተሳትፎ አዎንታዊ ነበር፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችል ርእስ በመምረጥ እና ሰፊ ርእሶችንም በማጥበብ በቡድን ቢጋር ነድፈዋል፡፡ አስታዋፅአውን መሰረት በማድረግም በየግላቸው ድርሰት ፅፈዋል፡፡

ፅሁፋቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር በመለዋወጥ አስተያየት ሰጥተዋል፤ ተቀብለዋል፡፡ ከአስተያየቶቹ መካከል ‹‹የአደረጃጀት ችግር ይታይበታል ማለትም በመደምደሚያ መስፈር ያለበት ሀሳብ በመግቢያ ላይ ሰፍሯል፡፡ ፊደላት በአግባቡ አልተፃፉም፡፡ ለምሳሌ አልኮን ሳይሆን አልኮል መባል ነበረበት፡፡ ስርዝ ድልዝ በዝቷል፡፡ መግቢያና መደምደሚያ መኖሩ ጥሩ ነው፡፡ በበቂ ማብራሪያ ቀርቧል፡፡ ቃላት ተደጋግመዋል፡፡ ፅሁፉ ምስል ከሳች አይደለም፡፡ እንደጥይት ተፈንጥሮ ከማለት ተስፈንጥሮ ብትለው ይሻላል፡፡›› የሚሉ አስተያየቶችን አስፍረዋል፡፡

ተማሪዎች ከመምህራቸው እና ከጓደኞቻቸው የተሰጣቸውን አስተያየት በመቀበል ፅሁፋቸውን በመከለስ ልምምድ አድርገዋል፡፡ በሂደቱም ያሳዩት ለውጥ አዎንታዊ ነበር፡፡ ይኸውም ድርሰቱ ከ20% የታረመ ሲሆን አብዛኞቹ ተማሪዎች ከ15 በላይ ውጤት አስመዝግበዋል፡፡ (ተማሪዎች በልምምድ ሂደት የፃፉትን ድርሰት በአባሪ አስራ ሁለት ገፅ

130 ይመልከቱ።) ተማሪዎች በድህረ ትምህርት ፈተና የፃፉት ድርሰትም ይህንኑ የምልከታ ግኝት የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል። በቅድመ ትምህርት ፈተናቸው በወጉ ያልተደራጁ ዓረፍተነገሮች፣ ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይበት፣ የቃላት አመራረጥ እና የስርዓተ ፅህፈት ችግር ጎልቶ የሚታይበት ሲሆን በልምምዱ ወቅት ግን የተማሪዎች ፅሁፍ መሻሻል እንዳሳየ የድህረ ትምህርተት ፈተና ውጤት ያሳያል። ከምልከታ የተገኙ ሌሎች መረጃዎችን ከፅሁፍ መጠይቁ ምላሽ ጋር በማዋሀድ ለማቅረብ ተሞክሯል።

## 4.2. ከፈተናዎች ውጤት የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ

ቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች ለተጠኚዎች የተሰጡ ሲሆን ቅድመ ትምህርት ፈተናው ተጠኚዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት መፃፍን ከመለማመዳቸው በፊት የነበራቸውን ችሎታ ለመለካት፣ ድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ የሙከራ ቡድን ተጠኚዎች ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ ለውጥ ማሳየት አለማሳየታቸውን ለመለየት የሚያስችሉ ናቸው። በመሆኑም ከቁጥጥር ተማሪዎች ውጤት ጋር በማወዳደር ውጤቱ ከፍተኛ መሆን አለመሆኑ በስታቲስቲካዊ ዘዴ ተረጋግጧል።

### 4.2.1. ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ

የቅድመ ትምህርት ፈተና ዓላማ ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ ለመለካት ነው። ይህንኑ ለማረጋገጥ የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ትምህርቱን ከመማራቸው በፊት ፈተና ተሰጥቷቸዋል። ፈተናውም በሶስት መምህራን ታርሟል። እያንዳንዱ አራሚ ለእያንዳንዱ ተማሪ የሰጠውን ውጤት በመደመር እና ለተማሪው ብዛት በማካፈል አማካይ ውጤት ተሰልቷል። (ውጤቱን በአባሪ አምስት ገፅ 110 ላይ ይመልከቱ) አማካይ ውጤቱን መሰረት በማድረግም ልይይቱ እና መደበኛ ልይይቱ ተገኝቷል። ውጤቱ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ሶስት ቀርቧል።

**ሠንጠረዥ ሶስት፡- ሦስቱ አራሚዎች በቅድመ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች የሠጡት አማካይ ውጤት እና ተሰልቶ የተገኘ ልይይት እና መደበኛ ልይይት**

| የፈተናው ዓይነት | ክፍል | ውጤት | አራሚዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በአራሚ አንድ የተሰጠ አማካይ ውጤት | በአራሚ ሁለት የተሰጠ አማካይ ውጤት | በአራሚ ሶስት የተሰጠ አማካይ ውጤት |
| ቅድመ ትምህርት | የሙከራ ($11^{07}$) | አማካይ | 41.9 | 43.1 | 47 |
| | | ልይይት | 128.57 | 235.30 | 153.25 |
| | | መደበኛ ልይይት | 11.33 | 15.33 | 12.37 |
| | የቁጥጥር ($11^{18}$) | አማካይ | 41.11 | 39.13 | 47.58 |
| | | ልይይት | 82.15 | 97.78 | 70.75 |
| | | መደበኛ ልይይት | 9.06 | 9.88 | 8.41 |

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው አራሚ አንድ ለሙከራ ቡድን ($11^{07}$) የሰጠው አማካይ ውጤት 41.9 ሲሆን ለቁጥጥር ቡድን ($11^{18}$) ደግሞ 41.11 ሰጥቷል፡፡ (አራሚዎች የሰጡት አማካይ ውጤት = እያንዳንዱ ተማሪ ያገኘውን ውጤት በመደመር ከዚያም ለተማሪው ብዛት በማካፈል የተገኘ ውጤት) በዚህ ውጤት መነሻነት ተሰልቶ የተገኘው ልይይት እና መደበኛ ልይይት የሙከራ ቡድን ($11^{07}$) 128.57 እና 11.33 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን ($11^{18}$) ደግሞ 82.15 እና 9.06 ነው፡፡ አራሚ ሁለትም በበኩሉ የሰጠው አማካይ ለሙከራ ቡድን ($11^{07}$) 43.1 ሲሆን ልይይቱ 235.30፣ መደበኛ ልይይቱ 15.33 ሆኗ፡፡ ለቁጥጥር ቡድን ($11^{18}$) አማካይ 39.13፣ ልይይት 97.78፣ መደበኛ ልይይት 9.88 ነው፡፡ የአራሚ ሶስት አማካይ ለሙከራ ቡድን ($11^{07}$) 47፣ ልይይት 153.25 እና መደበኛ ልይይት 12.37 ሲሆን ለቁጥጥር ቡድን ($11^{18}$) ደግሞ አማካይ 47.58፣ ልይይት 70.75 እና መደበኛ ልይይት 8.41 ሆኗል፡፡

ከላይ የቀረበውን መረጃ መሰረት በማድረግ ውጤቱ በቲ ቴስት ተሰልቷል። በዚህም በሁለቱ ቡድኖች ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለ ወይስ የለም የሚለውን ለማረጋገጥ ተችሏል። ይህም በሰንጠረዥ አራት እንደሚከተለው ይቀርባል።

**ሰንጠረዥ አራት፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና የቲ ቴስት ውጤት**

| የፈተናው ዓይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | ልይይት variance | የነፃነት ደረጃ | ቲ ቴስት (T-test) | የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ($11^{07}$) | 36 | 44 | 151.22 | 70 | 0.562 | 1.664 | 0.05 |
| | የቁጥጥር ($11^{18}$) | 36 | 42.61 | 69.85 | | | | |

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያስረዳው በሰንጠረዥ ሶስት የቀረበውን የእያንዳንዱን አራሚ ውጤት በመደመርና ለሶስት በማካፈል የየክፍሉን አማካይ ውጤት አስገኘ። ከዚያም አማካይ ውጤቱን፣ የሙከራ ቡድን 44 (41.9 + 43.1 + 47/3) እና የቁጥጥር 42.61 (41.11 + 39.13 + 47.58/3) ፣ ልይይቱን (151.22 እና 69.85) እና የአንዱን ናሙና ብዛት (36) በመያዝ በቲ ቴስት ቀመር ተሰላ። ውጤቱም 0.5627 ሆነ። በሌላ በኩል የጉልህነት ደረጃውን በመወሰን (0.05) እና የነፃነት ደረጃውን (70) በመያዝ የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ ተፈልጎ ተገኘ። የቲ ሰንጠረዥ ዋጋውም 1.6645 ሆነ። በዚህ መሰረት የቲ ቴስት ዋጋ ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ ሲወዳደር ያነሰ (0.5627 < 1.6645) ነው። ይህ የሚያሳየው በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው። (የቲ ቴስት ቀመር እና ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት በአባሪ ስድስት ገፅ 118 ይመልከቱ።)

### 4.2.2. ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ

ድህረ ትምህርት ፈተናው፣ የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት ለአንድ ወር (አስራ ሶስት ክፍለ ጊዜያት) ልምምድ ካደረጉ በኋላ የተሰጠ ነው። ዓላማውም

ተማሪዎች ከልምምዱ በኋላ ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ለመለካት ሲሆን ይህንኑ ለማረጋገጥ ለሁለቱም ቡድኖች ፈተና ተሰጥቷል፡፡ የእያንዳንዱ ክፍል ፈተና በሶስቱ መምህራን ታርሞ ውጤት ተሰጥቶታል፡፡ አራሚዎች የሰጡትን ውጤት በመደመርና ለክፍሉ ተማሪዎች ብዛት በማካፈል አማካይ ውጤት ተሰልቷል፡፡ በዚህም መነሻነት ልይይቱን እና መደበኛ ልይይቱን ለማግኘት ተችሏል፡፡ ይህም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ አምስት ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ አምስት፡-** ሦስቱ አራሚዎች በድህረ ትምህርት ፈተና ለሁለቱም ቡድኖች የሠጡት አማካይ ውጤት እና ተሰልቶ የተገኘ ልይይት እና መደበኛ ልይይት

| የፈተናው ዓይነት | ቡድን | ውጤት | አራሚዎች | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | በአራሚ አንድ የተሰጠ አማካይ ውጤት | በአራሚ ሁለት የተሰጠ አማካይ ውጤት | በአራሚ ሶስት የተሰጠ አማካይ ውጤት |
| ድህረ ትምህርት | የሙከራ ($11^{07}$) | አማካይ | 64.72 | 68.5 | 70.3 |
| | | ልይይት | 151.80 | 143.85 | 137.42 |
| | | መደበኛ ልይይት | 12.32 | 11.99 | 11.72 |
| | የቁጥጥር ($11^{18}$) | አማካይ | 48 | 50.4 | 56.61 |
| | | ልይይት | 132.34 | 96.54 | 102.59 |
| | | መደበኛ ልይይት | 13.06 | 9.82 | 10.12 |

በሰንጠረዡ የሁለቱ ቡድኖች አማካይ ውጤት፣ ልይይት እና መደበኛ ልይይት ቀርቧል፡፡ አራሚ አንድ የሰጠው አማካይ ውጤት ለሙከራ ቡድን ($11^{07}$) 64.72 ሲሆን ልይይቱ 151.80 መደበኛ ልይይቱ 12.32፣ የቁጥጥር ቡድን ($11^{18}$) አማካይ ውጤት ደግሞ 48 ልይይት 132.34 መደበኛ ልይይት 13.06 ሆኗል፡፡ በአራሚ ሁለት ለሙከራ ቡድን ($11^{07}$) የተሰጠው አማካይ ውጤት 68.5 ሲሆን ልይይቱ 143.85 መደበኛ ልይይቱ

11.99፣ የቁጥጥር ($11^{18}$) አማካይ 50.4 በመሆኑ የተሰላው ልይይት 96.54 መደበኛ ልይይት 9.82 ነው። በአራሚ ሶስት ለሙከራ ቡድን ($11^{07}$) የተሰጠው አማካይ 70.3 በመሆኑ ልይይት 137.42 እና መደበኛ ልይይት 11.72 አስገኘ። የቁጥጥር ቡድን ($11^{18}$) አማካይ 56.61፣ ልይይት 102.59 መደበኛ ልይይት 10.12 ነው። በሁለቱ ቡድኖች የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል። ይህ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ስድስት ቀርቧል።

**ሰንጠረዥ ስድስት** የድህረ ትምህርት ፈተና የቲ ቴስት ውጤት

| የፈተናው ዓይነት | ቡድን | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | ልይይት (variance) | የነፃነት ደረጃ | ቲ ቴስት (T-test) | የቲ ሰንጠረዥ ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድህረ ትምህርት ፈተና | የሙከራ ($11^{07}$) | 36 | 67.83 | 126.53 | 70 | 6.565 | 1.6645 | 0.05 |
| | የቁጥጥር ($11^{18}$) | 36 | 51.68 | 91.415 | | | | |

ከሰንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው የሶስቱን አራሚዎች አማካይ ውጤት በመደመር እና ለሶስት በማካፈል የክፍሉን አማካይ ውጤት አስገኘ። ይኸውም የሙከራ ቡድን 67.83 (64.72 + 68.5 + 70.3/3)፣ የቁጥጥር ቡድን ደግሞ 51.68 (48 + 50.4 + 56.61/3) ነው። ይህን አማካይ ውጤት ከእያንዳንዱ ተማሪ ውጤት በመቀነስ እና የተገኙትን ውጤቶች ካሬ በማድረግ በመቀጠልም ውጤቶቹን በመደመር እና ከናሙናው ብዛት አንድ ቀንሶ (36-1)፣ ለተገኘው ውጤት በማካፈል ልይይቱ ተገኘ። ውጤቱም የሙከራ ቡድን 126.532 ሲሆን የቁጥጥር ቡድን 91.68 ነው። አማካይ ውጤቱን ልይይቱን እና የአንዱን ክፍል የናሙና ብዛት በመያዝ የቲ ቴስት ውጤቱ ተሰላ። ስሌቱ 6.565 አስገኘ። (የቲ ቴስት ቀመር እና ተሰልቶ የተገኘውን ውጤት በአባሪ ስድስት ገፅ 118 ይመልከቱ።) የቲ ቴስት ውጤት ከቲ ሰንጠረዥ ውጤት ጋር ሲወዳደር 6.565 ከ1.6645 ይበልጣል። ይህ በሁለቱ ተጠኚ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን ያሳያል። በመሆኑም የመፃፍ ክሂልን በረዥም ልቦለድ አማካይነት የተማሩ ተማሪዎች ውጤት፣ በረዥም ልቦለድ

ካልተማሩት ተማሪዎች ውጤት ይበልጣል። ይህም ሙከራው የተካሄደባቸው ተማሪዎች ውጤት መሻሻሉን ያሳያል።

የሁለቱ ቡድኖች ቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ጥቅል ውጤት ገፅታ እንደሚከተለው በግራፍ አንድ ቀርቧል።

**ግራፍ አንድ፡- የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች ቅድመ እና ድህረ ሙከራ ፈተናዎች ጥቅል ውጤት ገፅታ**




ከግራፍ አንድ መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 44 ሲሆን የድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 67.83 ነው። የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 42.61፣ ድህረ ትምህርት ፈተናው ደግሞ 51.68 ሆኗል። የሙከራ ቡድን ድህረ ሙከራ ፈተና ውጤት በ23% መሻሻል አሳይቷል። በቲ ቴስት ስሌት እንደተረጋገጠው በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት የለም። ነገር ግን በድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩን የቲ ቴስት ስሌቱ ውጤት ያረጋግጣል።

## 4.3. ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እና ማብራሪያ

የፅሁፍ መጠይቁ ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን መማር ያለውን ሚና እንዲያመለክቱ የቀረበ ነው። መጠይቁ ለተማሪዎች የቀረበው ከልምምዱ በኋላ

ሲሆን በረዥም ልቦለድ አማካይነት መፃፍን ከመማራቸው በፊት የነበራቸውን ዳራ እና ከልምምዱ በኋላ የመፃፍ ክሂላቸው ስለመዳበሩ ያላቸውን አመለካከት ለመፈተሽ አስችሏል፡፡

መጠይቁ ሶስት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን ክፍል አንድ የተማሪዎችን ዳራዊ መግለጫ ማለትም ፆታ እና እድሜ የሚጠይቅ ነው፡፡ ክፍል ሁለት የሊከርት ስኬል ስብስብ ጥያቄዎች ሲሆኑ በውስጡ አስራ ሶስት ጥያቄዎችን ይዟል፡፡ አሉታዊ መልስ የሚሹ ሁለት ጥያቄዎች ሲኖሩት ቀሪዎቹ በአዎንታ የሚመለሱ ናቸው፡፡ መስማማትና አለመስማማትን ለመግለፅ ጥያቄዎች በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ አልስማማም እና ፈፅሞ አልስማማም በሚሉ አራት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ የነጥብ አሰጣጡም የሚጠበቀው ምላሽ አዎንታዊ ከሆነ በጣም እስማማለሁ 4፣ እስማማለሁ 3፣ አልስማማም 2 እና ፈፅሞ አልስማማም 1 ሲሆን የሚጠበቀው ምላሽ አሉታዊ ከሆነ ደግሞ በጭራሽ አልስማማም 4፣ አልስማማም 3፣ እስማማለሁ 2 እና በጣም እስማማለሁ 1 ይሆናል፡፡ ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ አራት ጥያቄዎች ተጠኚዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት ልምምድ ከማድረጋቸው በፊት ስለስነፅሁፍ እና ስለመጻፍ ክሂል የነበራቸውን አመለካከት ለመለየት ያስችላሉ፡፡ ዘጠኝ ጥያቄዎች ደግም ከልምምዱ በኋላ ለቀረበው ትምህርት ያላቸውን አመለካከት እንዲሁም በመፃፍ ችሎታቸው ላይ የመጣ ለውጥ/መሻሻል መኖሩን ለማረጋገጥ የቀረቡ ናቸው፡፡ በክፍል ሶስት የቀረቡት ጥያቄዎች አራት ናቸው፡፡ ጥያቄ አስራ አራት እና አስራ አምስት በአማራጮች የቀረበ ሲሆን ተማሪዎች ከአንድ በላይ ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ በመመሪያው ተገልፆላቸዋል፡፡ በጥያቄ ቁጥር አስራ ስድስት እና አስራ ሰባት የቀረቡት ደግሞ ልቅ ጥያቄዎች በመሆናቸው መላሾች ነፃ ሆነው ሀሳባቸውን እንዲገልፁ ቀርበዋል፡፡ ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ ምላሾች እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

**የተማሪዎች ዳራዊ መግለጫ**

በፅሁፍ መጠይቁ ክፍል አንድ ላይ ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተማሪዎች የተገኙ ምላሾች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ሰባት ቀርበዋል፡፡ ይህም መረጃ ስለተጠኚዎች አጠቃላይ ግንዛቤ ለመስጠት የቀረበ ነው፡፡ ነገር ግን የፅሁፍ መጠይቁ ምላሽ ከፆታ እና ከእድሜ አንፃር አይተነተንም፡፡

**ሰንጠረዥ ሰባት፡- የተማሪዎችን ዳራዊ መግለጫ የሚመለከት ሰንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የተጠኚ ተማሪዎች ዳራ | | የተገኘው መረጃ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | | ድምር |
| | | | በቁጥር | በመቶኛ | |
| 1. | ፆታ | ወ | 13 | 37.14 | 35 |
| | | ሴ | 22 | 62.85 | |
| 2 | እድሜ | ከ15 -18 | 32 | 91.42 | 35 |
| | | ከ18 አመትበላይ | 3 | 8.57 | |

ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በመጠይቁ ከተሳተፉ ተማሪዎች ውስጥ አስራ ሶስቱ (37.14 %) ወንዶች፣ ሃያ ሁለቱ (62.85 %) ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ እድሜን በተመለከተ መጠይቁ ከቀረበላቸው ሰላሳ አምስት ተማሪዎች ውስጥ ሰላሳ ሁለቱ (91.42 %) ከ15 እስከ 18 ባለው የዕድሜ ክልል የሚገኙ ሲሆን ሶስቱ (8.57 %) ደግሞ 18 ዓመት በላይ ናቸው፡፡

በክፍል ሁለት እና ሶስት ለቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ሰንጠረዥ ስምንት፡- ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ከመማራቸው በፊት የነበራቸው ዳራዊ አመለካከት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | የሚጠበቁ አዎንታዊ እና አሉታዊ መልሶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም | |
| 1 | ከዚህ በፊት ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ማለትም ረጅም ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት በትርፍ ጊዜዬ አነባለሁ፡፡ | በቁጥር | 5 | 24 | 6 | - | + |
| | | በመቶኛ | 14.2 | 68.5 | 17.1 | - | |
| 2 | ባለፉት የክፍል ደረጃዎች (ከ11ኛ ክፍል በፊት) በስነፅሁፋዊ ስራዎች አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ምልልሶችን እና ደብዳቤዎችን ፣ አንቀፅ መገንባት ድርሰት መፃፍ) የሚያስችል በቂ ትምህርት አግኝቻለሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ | በቁጥር | 11 | - | 17 | 7 | - |
| | | በመቶኛ | 31.4 | - | 48.5 | 20 | |
| 3 | ቀደም ሲል የተለያዩ ፅሁፎችን የምፅፈው የመፃፍ ችሎታዬን ለማሻሻል ሳይሆን በመምህራን ስለምታዘዝ (ለማርክ ብዬ) ነው፡፡ | በቁጥር | 19 | 12 | 4 | - | + |
| | | በመቶኛ | 54.2 | 34.2 | 11.4 | - | |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከአራቱ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ አንብቦ መረዳት እና መፃፍ) ለመማር የሚከብደኝ የመፃፍ ክሂል ነበር፡፡ | በቁጥር | 5 | 20 | 8 | 2 | + |
| | | በመቶኛ | 14.2 | 57.1 | 22.8 | 5.7 | |

ተማሪዎች ከስነፅሁፋዊ ስራዎች ጋር የነበራቸውን ትውውቅ ለመፈተሽ በተራ ቁጥር አንድ ‹‹ከዚህ በፊት ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ማለትም ረዥም ልቦለድ፣ አጭር ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት በትርፍ ጊዜዬ አነባለሁ፡፡›› ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ከሰጡት ውስጥ 29 ተማሪዎች (82.8%) መስማማታቸውን ሲገልፁ 6 ተማሪዎች (17.1%) አለመስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ በተራ ቁጥር ሁለት ከ11ኛ ክፍል በፊት በነበሩት የክፍል

ደረጃዎች በስነፅሁፋዊ ስራዎች አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ምልልሶችን እና ደብዳቤዎችን፣ አንቀፅ መገንባት፣ ድርሰት መፃፍ የሚያስችል በቂ ትምህርት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ 24 ተማሪዎች (68.1 %) አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 11 ተማሪዎች (31.4 %) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በጥያቄ ቁጥር አንድ ላይ ከቀረበው ምላሽ ለመረዳ እንደሚቻለው አብዛኞቹ ተማሪዎች ስነፅሁፋዊ ስራዎችን የማንበብ ልምድ አላቸው፡፡ ነገር ግን ይህን የማንበብ ልምዳቸውን ከመፃፍ ጋር አቀናጅተው እንዲጠቀሙበት የሚያስችል በቂ ልምምድ አለማድረጋቸውን በተራ ቁጥር ሁለት ከሰጡት ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡

በተራ ቁጥር ሶስት ቀደም ሲል የተለያዩ ፅሁፎችን የምፅፈው የመፃፍ ችሎታዬን ለማሻሻል ሳይሆን በመምህራን ስለምታዘዝ (ለማርክ ብዬ) ነው፡፡ ለሚለው ጥያቄ 31 ተማሪዎች (88.5 %) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 4 ተማሪዎች (11.4 %) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት የተለያዩ ፅሁፎችን ቢፅፉም የመፃፍ ችሎታቸውን የማሳደግ ዓላማ ኖሯቸው ሳይሆን ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ወይም ይዘቶች መማሪያነት እንደ መሳሪያ የሚገለገሉበት መሆኑን ነው፡፡

የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ሂደት ተማሪዎች ‹‹ይከብደኛል›› ብለው የሚያስቡት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ በቀረበው ጥያቄ 25 ተማሪዎች (71.3 %) የመፃፍ ክሂል እንደሆነ በመስማማት መልስ ሲሰጡ 10 ተማሪዎች (28.5 %) ተማሪዎች ደግሞ አለመስማማታቸውን በመግለፅ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከምልከታ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝተቷል፡፡ ይኸውም በማስተማር ሂደቱ በመጀመሪያዎቹ ቀናት ተማሪዎች የማንበቡን፣ የመወያየቱን እና የማዳመጡን ሂደት በሙሉ ተሳታፊነት አከናውነዋል፡፡ ነገር ግን ወደ መፃፍ ስራው ለመግባት የመፍራት እና በራስ ያለመተማመን ስሜት የታየባቸው ሲሆን በሂደት ችግሩን ለመቅረፍ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- ለማስተማሪያነት የዋሉ ቅንጫቢዎች ገፅታ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | አማራጮች | | | | የሚጠበቁ አዎንታዊ እና አሉታዊ መልሶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም | |
| 5 | ለማስተማሪያነት የዋሉት ቅንጫቢዎች የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡ | በቁጥር | 10 | 21 | 4 | | + |
| | | በመቶኛ | 28.5 | 60 | 11.3 | - | |
| 6 | ለትምህርት የቀረቡት ቅንጫቢዎች እንድፅፍ አነቃቅተውኛል፡፡ | በቁጥር | 13 | 16 | 5 | 1 | |
| | | በመቶኛ | 37.1 | 45.7 | 3.8 | 2.85 | + |
| 7 | የቀረቡት ቅንጫቢዎች እና ተግባራት (ጥያቄዎች) ጥብቅ ትስስር አላቸው፡፡ | በቁጥር | 21 | 11 | 1 | 2 | |
| | | በመቶኛ | 60 | 31.4 | 2.8 | 5.7 | + |
| 8 | ለትምህርት የቀረቡት ቅንጫቢዎች ከሌሎች ክሂሎች በይበልጥ የመፃፍ ክህሎትን ለማዳበር ያስችላሉ፡፡ | በቁጥር | 14 | 14 | 6 | 1 | + |
| | | በመቶኛ | 40 | 40 | 17.4 | 2.85 | |

ለማስተማሪያነት የዋሉት ቅንጫቢዎች የተመረጡት በምዕራፍ ሁለት በቀረቡት መስፈርቶች መመዘኛነት ነው፡፡ ይሁን እና ቅንጫቢዎቹ ለተማሪዎች በቀረቡ ጊዜ ምን ያህል ግባቸውን እንደመቱ ለመፈተሽ ይቻል ዘንድ እነዚህ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ቀርበዋል፡፡ ምላሾቹም እንደሚከተለው በዝርዝር ይቀርባሉ፡፡

ለማስተማሪያነት የዋሉት ቅንጫቢዎች የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ ስለመሆናቸው በቀረበው ጥያቄ 31 ተማሪዎች (88.5 %) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 4 ተማሪዎች (11.3 %) አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው የቀረቡ ቅንጫቢዎች የአብዛኞቹን ተማሪዎች ፍላጎት ያሚሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተራ

ቁጥር አምስት ላይ የቀረበው ጥያቄ ቅንጫቢዎቹን በማንበባቸው በመፃፍ ተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊነታቸው የጨመረ ስለመሆኑ በቀረበላቸው ጥያቄ 29 ተማሪዎች (82. 8%) የስምምነት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 6 ተማሪዎች (16.6 %) ደግሞ አለመስማማታቸውን ገልፀዋል፡፡ ከምልከታ የተገኘው መረጃም ይህን የሚደግፍ ሲሆን ተማሪዎች ቅንጫቢዎችን የሚያነቡት በራስ ፍላጎት እና ተነሳሽነት ነው፡፡ እንዲሁም አብዛኞቹ ተማሪዎች የቤት ስራዎችን፣ የክፍል ስራዎችን በአግባቡና በወቅቱ በመስራት፣ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እና በመመለስ ተግባራትን በንቁ ተሳታፊነት አከናውነዋል፡፡

የቀረቡ ቅንጫቢዎች እና እነሱን መሰረት አድርገው የመፃፍ ክሂልን ለማለማመድ የተዘጋጁ ተግባራት ጥብቅ ቁርኝት አላቸው ሲሉ 32 ተማሪዎች (91.4 %) አዎንታዊ መልስ ሲመልሱ 3 ተማሪዎች (8.5 %) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በተራ ቁጥር ስምንት ለትምህርት የቀረቡት ቅንጫቢዎች ከሌሎች ክሂሎች በይበልጥ የመፃፍ ክህሎትን ለማዳበር ያስችላሉ፡፡ ለሚለው ሀሳብ 28 መላሾች (80 %) መስማማታቸውን ሲገልፁ 7 መላሾች (20 %) አልተስማሙም፡፡ ቋንቋን በማስተማር ሂደት አራቱን ክሂሎች አስተሳስሮ ማቅረብ ተገቢነት ያለው ቢሆንም እንደ ትምህርቱ ዓላማ አንዱ ክሂል ላይ በይበልጥ ትኩረት በማድረግ ተማሪዎችን ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት መፃፍ ላይ በመሆኑ ለተማሪዎች የቀረቡ ቅንጫቢዎች እና ተግባራት ከሌሎች ክሂሎች በይበልጥ የመፃፍ ክሂልን የሚያለማምዱ መሆናቸው ከምልከታ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

ከመጠይቁ ምላሽ እና ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ለማስተማሪያነት የዋሉት ቅንጫቢዎች የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው አብዛኞቹ ተማሪዎች በልምምዱ ሂደት በንቃት እንዲሳተፉ አስችለዋል፡፡ ተግባራቱም ከቅንጫቢዎች ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸው እና ከሌሎች ክሂሎች በይበልጥ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በዚህም ቅንጫቢዎቹ የጥናቱ ዓላማ ከግብ ይደርስ ዘንድ ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## ሰንጠረዥ አስር፡- ተማሪዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት ያላቸው አመለካከት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | አማራጮች | | | | የሚጠበቁ አዎንታዊ እና አሉታዊ መልሶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም | |
| 10 | የቀረቡትን ልቦለዶች አንብበን በጥንድ እና በቡድን በመወያት መማራችን የመፃፍ ክህሎቴን ለማጎልበት ረድቶኛል፡፡ | በቁጥር | 16 | 12 | 4 | 3 | + |
| | | በመቶኛ | 45.7 | 34.2 | 11.4 | 8.5 | |
| 11 | ድርሰት ስፅፍ እያቀድኩ፣ እያረቀቅኩ እየከለስኩ መፃፌን ወድጄዋለሁ፡፡ | በቁጥር | 17 | 17 | 1 | - | |
| | | በመቶኛ | 48.5 | 48.5 | 2.8 | - | + |
| 12 | በረጅም ልቦለድ አማካይነት መፃፍን ስለማመድ መምህርቷ ያደረጉልኝ ድጋፍ/እያነበቡ የሰጡኝ አስተያየት ጠቅሞኛል፡፡ | በቁጥር | 23 | 10 | 2 | - | |
| | | በመቶኛ | 65.7 | 28.5 | 5.7 | - | + |

ተማሪዎች በቡድን እና በጥንድ ሆነው ተግባራትን ሲያከናውኑ ልምድ በመጋራታቸው፣ በራስ የመተማመን ስሜትን ስለሚያዳብሩ ተግባራትን በፍላጎት እና በራስ ተነሳሽነት እንዲሰሩ ያግዛቸዋል ሲሉ Collie እና Slater (1987፣ 10) ያስረዳሉ፡፡ ይህንኑ በተመለከተ በተራ ቁጥር አስር ለቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች በጥንድ እና በቡድን ተግባራትን ማከናወናቸው የመፃፍ ክሂላቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው 28 ተማሪዎች (79.9 %) አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት ሲያረጋግጡ 7 ተማሪዎች (19.9%) ደግሞ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በምልከታ የተገኘው መረጃም እንደሚያረጋግጠው ተማሪዎች በጥንድ እና በቡድን ተግባራትን በማከናወን ሂደት ንቁ ተሳትፎ እንደነበራቸው ያሳያል፡፡ ከዚህም ባለፈ በልምምዱ የመጀመሪያ ቀናት አብዛኞቹ ተማሪዎች ወደ መፃፍ ስራው ለመግባት ፍርሀት እና በራስ ያለመተማመን ስሜት የታየባቸው ሲሆን ተግባራትን በጥንድ እና በቡድን ማከናወናቸው ይህን ችግር ለመቅረፍ አስተዋፅኦ እንደነበረው ከምልከታ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

በሂደታዊ የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ጥሩ የመፃፍ ችሎታን እንዲያዳብሩ ልዩ ልዩ ንዑሳን ተግባራትን ያከናውናሉ። እነዚህ ተግባራት ማቀድ፣ ማርቀቅ እና መከለስ እንደሆኑ Pincas (1982፣ 41) ፣ Sorenson (2010፣3) ይገልፃሉ። እነዚህ የመፃፍ ተግባራት በተማሪዎች ተቀባይነት እንዳላቸው ለመፈተሽ በቀረበው ጥያቄ 34 ተማሪዎች (97%) አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ ከ1 ተማሪ (2.8%) አሉታዊ ምላሽ ቀርቧል።

በጥያቄ ተራ ቁጥር 12 ‹‹በረጅም ልቦለድ አማካይነት መፃፍን ስለማመድ መምህርቷ ያደረጉልኝ ድጋፍ/ እያነበቡ የሰጡኝ አስተያየት ጠቅሞኛል።›› ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 33 ተማሪዎች (94.2 %) መስማማታቸውን በመግለፅ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ 2 ተማሪዎች (5.7%) አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህም የተማሪዎችን ፅሁፋዊ ስራዎች በማረም ግብረ መልስ መስጠት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ከምልከታ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚደግፍ ነው። ይኸውም ተማሪዎች የተሰጣቸውን አስተያየት ተቀብለው ፅሁፉን በማስተካከል አሻሽለው ሲፅፉ ተስተውሏል።

**ሰንጠረዥ አስራ አንድ፡- ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸው ስለመዳበሩ ያላቸው አመለካከት**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | አማራጮች | | | | የሚጠበቁ አዎንታዊ እና አሉታዊ መልሶች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | አልስማማም | ፈፅሞ አልስማማም | |
| 9 | የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ማንበቤ ጅምር ዓረፍተነገሮችን ማሟላት፣ ዓረፍተነገሮችን በራስ አገላለፅ መፃፍ፣ በገለፃ ስልት አንቀፅ መገንባት፣ ድርሰት መፃፍ ወዘተን. በማለማመድ የመፃፍ ክህሎቴ እንዲዳብር ጠቅሞኛል። | በቁጥር | 16 | 12 | 5 | 2 | + |
| | | በመቶኛ | 45.7 | 34.2 | 11.4 | 8.5 | |
| 13 | በልቦለድ ቅንጫቢ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ብለማመድም የመፃፍ ችሎታዬን አሻሽያለሁ ብዬ አላስብም። | በቁጥር | 3 | 3 | 12 | 17 | - |
| | | በመቶኛ | 8.3 | 8.3 | 34.2 | 48.5 | |

በጥያቄ ቁጥር ዘጠኝ ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎች መነሻነት የቀረቡትን የተለያዩ ንዑሳን የመፃፍ ተግባራት ማከናወናቸው የመፃፍ ክህሎታቸውን ማዳበር ማስቻሉን ለተጠየቁት ጥያቄ 28 ተማሪዎች (79.9 %) አዎንታዊ መልስ በመስጠት የመፃፍ ክህሎታቸው እንደዳበረ ሲገልፁ 7 ተማሪዎች (19.9 %) ግን አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ በልቦለድ ቅንጫቢዎች አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ብለማመድም የመፃፍ ችሎታዩን አሻሽያለሁ ብዬ አላስብም በሚል ለቀረበው እና አሉታዊ ምላሽ ለሚሻው ጥያቄ 29 ተማሪዎች (82.7 %) አለመስማማታቸውን በመግለፅ የመፃፍ ችሎታችን ተሻሽሏል ሲሉ በአንፃሩ ደግሞ 6 ተማሪዎች (16.6 %) መስማማታቸውን (አለመሻሻሉን) ገልፀዋል፡፡ እነዚህ ሁለት ጥያቄዎች (ጥያቄ ቁጥር 9 እና13) ተመሳሳይ ሀሳብ የያዙ ቢሆንም በተቃራኒ የሚመለሱ ናቸው፡፡ በመሆኑም አንድ ተማሪ ለመጀመሪው ጥያቄ መስማማቱን ቢገልፅ ለሁለተኛው ግን አለመስማማቱን መግለፅ አለበት፡፡ ምክንያቱም በመጀመሪያው ጥያቄ የመፃፍ ችሎታዬ ተሻሽሏል ብሎ በሁለተኛው አልተሻሻለም ሊል አይገባውም፡፡ በዚህ መልኩ የተመለሰ አንድ መጠይቅ መረጃውን እንዳያዛባ ሲባል በትንተናው አልተካተተም፡፡

ከመጠይቁ የተገኘው ምላሽ ከምልከታ እና ከፈተና ውጤት ትንተና ከተገኙት መረጃዎች ጋር ስምሙ ነው፡፡ ይኸውም በምልከታው እንደታየው ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች ውጤት መሻሻል ያሳዩ ሲሆን ከፈተና ውጤት የተገኘው መረጃም በቲ ቴስት ቀመር ተሰልቶ ውጤቱ መሻሻሉን ያሳያል፡፡ እንዲሁም አብዛኞቹ ተማሪዎች የመፃፍ ችሎታቸው ስለመሻሻሉ በመጠይቁ ተራ ቁጥር 9 እና 13 የሰጡት ምላሽ ያስረዳል፡፡

**ግራፍ ሁለት፡- የጥሩ ፅሁፍ ባህሪያት**



በግራፍ አንድ የቀረበው መረጃ እንደሚጠቁመው በአብዛኞቹ ተማሪዎች የተመረጠው የጥሩ ፅሁፍ ባህሪ ሀሳቡ በአግባቡ የተደራጀ የሚለው ሲሆን ይህንን የመረጡ ተማሪዎች ቁጥር ሃያ ዘጠኝ (82.85 %) ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በሀያ ሰባት ተማሪዎች (77.14%) የተመረጠው የጥሩ ፅሁፍ ባህሪ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት የጠበቀ ነው የሚለው ሲሆን ሀያ ሶስት ተማሪዎች (65.71 %) በተመረጡ ቃላት የተፃፈ ነው ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ የፅሁፉ ይዘት በደንብ የተብራራ ሲሉ የመለሱት ደግሞ ሀያ (57.14 %) ናቸው፡፡ በመጨረሻም አስራ ዘጠኝ ተማሪዎች (54.28 %) ስርዓተ ነጥቦችን በአግባቡ የተጠቀመ ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ በአጠቃላይ በተጠኚዎች ከተሰጡት ምላሾች መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ከጥሩ ፅሁፍ ባህሪያት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጡት ለሀሳብ አደረጃጀት ሲሆን በአፃራዊነት የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ከቀረቡት አማራጮች በጥቂት ተማሪዎች የተመረጠ ሆኗል፡፡

**ግራፍ ሶስት፡- ተማሪዎች የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን በማንበባቸው ያገኙት ጠቀሜታ**




ይህ መጠይቅ የቀረበው፣ ተማሪዎች የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ማንበባቸው እና የተለያዩ የመፃፍ ተግባራትን ማከናወናቸው ጥሩ ፅሁፍ ማሟላት ከሚገባቸው ባህሪያት የትኞቹን ለማሻሻል እንዳስቻላቸው ለማወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ከግራፍ ሁለት መረዳት እንደሚቻለው 26 ተማሪዎች (74.28 %) ለቃላት ምርጫ ጠቅሞናል ሲሉ 19 ተማሪዎች (54.14 %) የፅሁፉን ሀሳብ በወጉ ለማደራጀት አስችሎናል ብለዋል፡፡ የአፃፃፍ ስርዓትን በመጠበቅ ለመፃፍ ጠቀሜታ አለው ያሉት ደግሞ 18 ተማሪዎች (51.42%) ናቸው፡፡ ስለምፅፈው ርዕስ በቂ እውቀት ለማግኘት ጠቅሞኛል ያሉት 14 ተማሪዎች (40 %)

ሲሆኑ 11 መላሾች (31.42 %) ሰዋስዋዊ ስህተት የሌለባቸውን ዓ/ነገሮች ለማዋቀር ጠቅሞኛል ሲሉ መልሰዋል፡፡

በመሆኑም ከተጠኚዎች ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ረዥም ልቦለድን በማንበብ የተለያዩ የመፃፍ ትምህርት ተግባራትን ማከናወን፣ ከሌሎች ንዑሳን የመፃፍ ክሂሎች በይበልጥ የቃላት አመራራጥ ችሎታን ለማዳበር ያስችላል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በእያንዳንዱ የማረሚያ መስፈርት ተማሪዎች ያስመዘገቡት አማካይ የፈተና ውጤት እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

**ሰንጠረዥ አስራ ሁለት፡- የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተናዎች በእያንዳንዱ የማረሚያ መስፈርት ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት**

| | ቅድመ ሙከራ ፈተና ውጤት በመቶኛ | ድህረ ሙከራ ፈተና ውጤት በመቶኛ | ልዩነት |
|---|---|---|---|
| የቃላት ምርጫ | 22.5 | 57.9 | 35.4 |
| አደረጃጀት/ቅንብር | 28 | 58.7 | 31.6 |
| የጽሑፉ ይዘት፡- | 42 | 68.2 | 25.3 |
| ሰዋስዋዊነት | 59.5 | 76.4 | 16.9 |
| የአጻጻፍ ሥርዓታዊነትና የነጥቦች አጠቃቀም | 68 | 78.1 | 10.1 |

ከቀረበው ሰንጠረዥ ለመረዳት እንደሚቻለው በቃላት ምርጫ ያስመዘገቡት ውጤት በቅድመ ሙከራ ፈተና 22.5% ሲሆን በድህረ ሙከራ 57.9% ነው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ሲሰላ 35 (59.9-22.5) ይሆናል፡፡ ይህ ማለት የቃላት ምርጫቸው በ35% ተሻሽሏል ማለት ነው፡፡ አደረጃጀት/ቅንብር ደግሞ በቅድመ ሙከራ 28%፣ በድህረ ሙከራ 58.7 ሲሆን ልዩነቱ 31.6 ነው፡፡ በመሆኑም በ31.6% መሻሻል ታይቷል፡፡ የፅሁፍ ይዘት በቅድመ ሙከራ 42% በድህረ ሙከራ 68.2 %፣ ሰዋስዋዊነት በቅድመ ሙከራ 59.5%፣ በድህረ ሙከራ 76.4%፣ የአፃፃፍ ሥርዓታዊነት እና የነጥቦች አጠቃቀም በቅድመ ሙከራ 68% በድህረ ሙከራ ደግሞ 78.1% ሲሆን ልዩነቱ እንደቅደም ተከተላቸው 25.3%፣

16.9% እና 10.1% ሆኗል። ይህ ውጤት ከፅሁፍ መጠይቁ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲነፃፀር የቃላት ምርጫ እና አደረጃጀት/ቅንብር በፈተናው ውጤት በአንደኛነት እና በሁለተኛነት መሻሻል ያሳዩ ሲሆን በመጠይቁ አብዛኞቹ ተማሪዎች የመረጡት እነዚህን ነው። በፅሁፍ ይዘት፣ በሰዋስዋዊነት፣ በአጻጻፍ ሥርዓታዊነትና የነጥቦች አጠቃቀም ላይ ከፅሁፍ መጠይቅ እና ከፈተና ውጤት የተገኙ መረጃዎች ልዩነት አሳይተዋል። ይህም ተማሪዎች ያሻሻሉትን ንዑስ ክሂል በትክክል ካለመረዳት እንደሚመነጭ ይገመታል።

### ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ቅር የተሰኙበት ጉዳይ

በልቦለድ ቅንጫቢዎች አማካይነት የመፃፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ቅር ያለህ/ያለሽ ነገር ምን ነበር? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ 1 ተማሪ ምላሽ አልሰጠም፤ 5 ተማሪዎች  ምንም ቅሬታ የለንም ሲሉ አጭር ምላሽ ሰጥተዋል፤ 14 ተማሪዎች ቅሬታ የሌላቸው መሆኑን ከነምክንያታቸው ገልፀዋል፤ 15 ተማሪዎች ደግሞ ቅር የተሰኙበትን ጉዳይ አስፍረዋል። ቅሬታ የለንም ብለው ያቀረቧቸው ምክንያቶች ለጥያቄ ተራ ቁጥር 17 ከተሰጡ ምላሾች ጋር ተመሳሳይነት ስላላቸው አንድ ላይ ተዋህደው ቀርበዋል። ቅሬታ አለን የሚሉ ተማሪዎች የሚከተሉትን ሀሳቦች አስፍረዋል።

### የልምምዱ ጊዜ ስለማነሱ የተሰጡ አስተያየቶች

‹‹የምንፅፈው በአንድ ክፍለ ጊዜ ስለሆነ አስቦ ለመፃፍ ጊዜ ያንሰኛል››፣ ‹‹ጊዜ ያነሰ ነው››፣ ‹‹በቂ የልምምድ ጊዜ አለመኖሩ››  የሚሉ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

ከቀረቡት ምላሾች ለመረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች የልምምዱ ጊዜ እንዳነሳቸው ገልፀዋል። መፃፍ በባህሪው በርካታ ተግባራትን (ርዕስ፣ መምረጥ ማጥበብ፣ ረቂቁን መፃፍ፣ መከለስ) በውስጡ ስለሚይዝ ከሌሎች ክሂሎች በአንፃራዊነት ረዘም ያለ ጊዜ ይፈልጋል። በምልከታ ማስታወሻ ላይ እንደሰፈረው አብዛኞቹ ተግባራት የተከናወኑት በክፍል ውስጥ ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው ጋር እየተወያዩ እንዲሰሩ እንዲሁም ከመምህራቸው ግብረመልሶችን በመቀበል ልምምዱን እንዲያካሂዱ በማሰብ ነው። ነገር ግን አንዳንዶቹ ተግባራት በአንድ ክፍለ ጊዜ የሚጠናቀቁ ባለመሆናቸው በቤት ስራ መልክ ሰርተው እንዲመጡ አልያም በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ እንዲሰሩት ማድረግ ተገቢ ነው። ከዚህም ባለፈ አንዳንድ ተማሪዎች የፅህፈት ስራዎችን ለማከናወን ረዘም ያለ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ የተወሰኑ መልመጃዎችን

በመስጠት የቤት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ በልምምዱ ጊዜ ይህ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

**የትምህርቱ አቀራረብ ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች ከሚያውቁት ጋር የተለየ ስለመሆኑ የተሰነዘሩ አስተያየቶች**

‹‹ትምህርቱ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ትምህርት በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ሳንማር አሁን ለምን መጣ?››

‹‹ያልለመድኩት ስለነበረ ትንሽ ተደናግጬ ነበር፡፡ ምክንያቱም ይህን መማር የነበረብን ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች ነበር››

ተማሪዎች እነዚህን አስተያየቶች ቅሬታ ብለው ቢገልጧቸውም ቅሬታቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ሳይሆን ቀደም ባሉት የክፍል ደረጃዎች በዚህ ስልት ባለመማራቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ በጥያቄ ተራ ቁጥር 2 ምላሻቸው ላይ እንደታየው በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን አለመማራቸውን ገልፀዋል፡፡

በቅሬታ መልክ ከቀረቡ ሌሎች ሀሳቦች መካከል አንድ ተማሪ ‹‹ሲደጋገም አሰልቺ ነው›› ሲል ገልጿል፡፡ ጥቂት ተማሪዎች የመሰላቸት ሁኔታ ይታይባቸው እንደነበረ ከምልከታ የተገኘው መረጃ የሚጠቁም ሲሆን አሰልቺነቱ ሊከሰት የቻለው ለአንድ ወር በተከታታይ መፃፍን ብቻ በመማራቸው እና በሌሎች ምክንያቶች ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ይህ በመደበኛው ትምህርት ተካቶ ሲሰጥ ከሌሎች ክሂሎች ጋር በስብጥር የሚቀርብ በመሆኑ አሰልቺ ሊሆን አይችልም፡፡

ሌላው አስተያየት ‹‹ የመፃፍ ክህሎት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው›› የሚል ሲሆን ይህ የጥናቱ ትኩረት የመፃፍ ክህሎት ላይ ብቻ እንደሆነ ባለመገንዘብ የተሰጠ አስተያየት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

**ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ያላቸው አጠቃላይ አስተያየት**

በአጠቃላይ ረዥም ልቦለድን በመጠቀም የመፃፍ ክሂልን መማርና ማስተማር ሂደት ላይ ያለሽን/ህን ሀሳብ ግለጪ/ፅ ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡ 2 ተማሪዎች፣ ጥሩ ነው ብለው በአጭሩ መልስ የሰጡ 2 ተማሪዎች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሁለቱ ምላሾች አሉታዊ ሲሆኑ ሌሎቹ አዎንታዊ ናቸው፡፡ አዎንታዊ ምላሽ

ከሰጡ ተማሪዎች አብዛኞቹ ከመማር ማስተማሩ ያገኙትን ጠቀሜታ በመግለፅ ሀሳባቸውን አስፍረዋል፡፡ አሉታዊ ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች የልምምዱ ጊዜ ማነሱን የገለፁ ሲሆን ሀሳቡ በጥያቄ ቁጥር 16 ተካቷል፡፡ አዎንታዊ ምላሾች እና በተራ ቁጥር 16 ቅሬታ የለንም ብለው ያቀረቧቸው ምክንያቶች እንደሚከተለው ተዋህደው ይቀርባሉ፡፡

‹‹ የመፃፍ ክሂሌን ያዳበርኩ ይመስለኛል፡፡››

‹‹ ይህ ትምህርት ድርሰቶች ላይ ያሉትን ስህተቶች እንድለይ ረድቶኛል፡፡››

‹‹ ጥሩ ፅሁፍ ሊያሟላ የሚገባቸውን ባህሪያት ለማወቅ ጠቅሞናል፡፡››

‹‹ ፅህፈትን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ክሂሎችን እንድናዳብር ረድቶናል፡፡››

‹‹ የመፃፍ እና የማንበብ ክሂላችንን አዳብሯል፡፡››

ከፍ ሲል ከቀረቡት ሀሳቦች ለመረዳት የሚቻለው ልቦለድን በመጠቀም በተደረገው ልምምድ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸው መዳበሩን ጠቁመዋል፡፡ ይህ ምላሽ በጥያቄ ተራ ቁጥር ዘጠኝ እና አስራ ሶስት ላይ የመፃፍ ክሂላቸው መዳበሩን አስመልክቶ ለቀረበው ጥያቄ ከተሰጡት ምላሾች ጋር ስምሙ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ‹‹ስህተቶችን መለየት ችለናል››፣ ‹‹የጥሩ ፅሁፉ ባህሪያትን አውቀናል›› የሚሉ ሀሳቦችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለመፃፍ ክሂል ልምምድ የቀረቡ ተግባራት ሌሎች ክሂሎችን ለማለማመድ ጠቀሜታ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡

ከአስተያየቶቹ መካከል የመማር ማስተማሩ ሂደት ቀጣይነት እንዲኖረው የተሰነዘሩም ነበሩ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ‹‹ ትምህርቱን በጊዜያዊነት ሳይሆን በዘላቂነት ብንማር ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ፡፡›› የሚል ሲሆን ሁለተኛው ‹‹የመማር ማስተማሩ ሂደት ጥሩ ነው፡፡ ግን ሁሉንም የክፍል ደረጃ ያማከለ ቢሆን የበለጠ የተሻለ ይሆን ነበር ማለትም የመሰናዶ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ቢጨምር ጥሩ ነበር፡፡ በዚሁ ይቀጥል፡፡›› ይላል፡፡

ሌሎች ደግሞ ‹‹ከዚህ በፊት ከነበረው መማር እና ማስተማር ለየት ያለ በመሆኑ እና ለተማሪዎች እንዲፅፉ ከመንገር አልፎ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን እንደምሳሌ

በመውሰድ ልምምድ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው።›› በማለት ከመደበኛው የትምህርት አቀራረብ ጋር በማነፃፀር አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል።

‹‹ ጥሩ ፀሀፊ እና ጥሩ ፅሁፎችን አንባቢ እንድሆን ይረዳኛል።››

‹‹ ለወደፊት የሚጠቅመን ስለሆን ጥሩ ነው››

‹‹ መፃህፍትን እንድናነብ አነሳስቶናል›› የሚሉ አስተያየቶች ደግሞ ልምምዱ በተጠኚዎች ላይ አዎንታዊ አመለካከት በማሳደሩ በጥናቱ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ወደፊት ለመፃፍ እና ለማንበብ የሚያስችላቸው መሆኑን ያሳያሉ።

በአጠቃላይ ከተማሪዎች ምላሽ የተሰበሰበው መረጃ እንደሚጠቁመው ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት ያደረጉት ልምምድ የመፃፍ ክሂልን ለማሻሻል አስተዋፅኦ እንዳለው ያሳያል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው ከአጥኚዋ የማስተማር ልምድ እና ከተለያዩ የመስኩ ምሁራን ሀሳብ ለመረዳት እንደተቻለው ተማሪዎች ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር ይታይባቸዋል፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ ከሚያስችሉ ስልቶች መካከል ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በቋንቋ ትምህርት መጠቀም ለችግሩ መቃለል አይነተኛ መፍትሄ መሆኑ በምሁራን ተጠቅሷል፡፡ በመሆኑም ረዥም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር ያለውን ሚና ለማረጋገጥ ሙከራዊ ጥናት ተደርጓል፡፡ ጥናቱም የተካሄደው በጉለሌ ክፍለ ከተማ በሚገኘው በየካቲት 12 መሰናዶ ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

በፍተሻው በተገኘው ውጤት ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

- ረዥም ልቦለድ ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግርን ለማቃለል ሚና አለው?
- መፃፍን በረዥም ልቦለድ አማካይነት የተማሩ ተማሪዎች ውጤት በረዥም ልቦለድ ካልተማሩት ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ይሆናል?

ከላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን እነሱም ምልከታ፣ ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ የጥናቱ አካሄድም በቅድሚያ ተጠኚ ተማሪዎችን በሁለት ምድብ በመክፈል (የሙከራ እና የቁጥጥር) ቅድመ ሙከራ ፈተና በመስጠት ተጀምሯል፡፡ ዓላማውም ተጠኚዎች ያላቸውን ችሎታ ለመለካት ነበር፡፡ ፈተናው በሶስት አራሚዎች ታርሞ አማካይ ውጤቱ የ$11^{07}$ 44 ሲሆን የ$11^{18}$ ደግሞ 42.61 ሆነ፡፡ በቲ ቴስት ቀመር ተሰልቶ 0.5627 አስገኘ፡፡ ውጤቱ የሚያሳው በሁለቱ ተጠኚዎች መካከል ጉልህ ልዩነት አለመኖሩን ነው፡፡ ይህ ከተረጋገጠ በኋላም የሙከራ ቡድኑ በረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማካይነት ለአንድ ወር (13 ክፍለ ጊዜያት) ልምምድ አድርጓል፡፡ ከምልከታው የተገኘው መረጃም ልምምዱ ውጤታማ እንደነበረ ያሳል፡፡ ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ የተማሪዎች ውጤት መሻሻል አለመሻሻሉን ለመፈተሽ ድህረ ሙከራ ፈተና ተሰጥቷል፡፡ ፈተናው አሁንም በሶስት አራሚዎች ታርሞ አማካይ ውጤቱ ተሰልቷል፡፡ የ$11^{07}$ 67.83፣ የ$11^{18}$ 51.68 ሲሆን የቲ ቴስት ቀመር

ውጤቱ 6.565 ነው። ውጤቱ ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ (1.6645) ይበልጣል። መረጃው የሚያሳየው በተጠኚ ቡድኖች መካከል ልዩነት መኖሩን ነው። ይህ ማለት የመፃፍ ክሂልን በረዥም ልቦለድ አማካነት የተማሩ ተማሪዎች ውጤት፣ በረዥም ልቦለድ ካልተማሩት ተማሪዎች ውጤት ይበልጣል ማለት ነው። ይህ የሚያመለክተው ለውጤቱ መሻሻል ምክንያቱ ተማሪዎች በረዥም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን መማራቸው ነው።

ተማሪዎች ልምምዱን አጠናቀው ድህረ ትምህርት ፈተና ከተፈተኑ በኋላ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያላቸውን አስተያየት ለመፈተሽ የፅሁፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል። የመጠይቁ መረጃ በአስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ ተፈትሾ 73.71% ሆኗል። በመሆኑም አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል።

ከፅሁፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው ተማሪዎች ባለፉት የክፍል ደረጃዎች ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የመፃፍ ክህሎትን በበቂ ሁኔታ ልምምድ አለማድረጋቸውን ያሳያል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ አብዛኞቹ ተማሪዎች እንደገለፁት ከሌሎች ክሂሎች በይበልጥ ለመማር የሚከብደው መፃፍ ነው ብለው ያስባሉ። ተጠኚዎች ከልምምዱ በኋላ ያላቸውን አመለካከት ለማወቅ በቀረበላቸው ጥያቄ እንደገለፁት የመፃፍ ችሎታቸው መሻሻሉን ለማረጋገጥ ተችሏል። ከምልከታ እና ከድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል።

## 5.2. አስተያየት

በዚህ ጥናት ከምልታ፣ ከፈተና እና ከፅሁፍ መጠይቅ ምላሾች የተገኘውን መረጃ አስመልክቶ የተደረሰበትን ማጠቃለያ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ የቀረቡት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

1. ተማሪዎች ሀሳብን በፅሁፍ የመግለፅ ችግር እንዳለባቸው በተለያዩ ጊዜያት ከተካሄዱ ጥናቶች ማረጋገጥ ተችሏል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች እንዳሉ ተጠቅሷል። ይህንን ችግር ለማቃለል ረዥም ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር ተጠቃሽ ሲሆን ጥናቱ ይህንኑ አረጋግጧል። በመሆኑም በረጅም ልቦለድ የመፃፍ ክሂልን ማስተማሩ ተጠናክሮ ቢቀጥል
2. ረዥም ልቦለድን ተጠቅሞ የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች ሲኖሩ ሁሉም የየራሳቸው ጥንካሬ እና ድክመት ያላቸው በመሆኑ

መምህራን በአንዱ ላይ አተኩረው ሌላውን መተው ሳይሆን እንደአስፈላጊነታቸው እያፈራረቁ እና እያዋሀዱ ቢጠቀሙ ውጤቱ ያማረ ይሆናል፡፡

3. በረጅም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን ስናስተምር ተማሪዎች የመፃፍ ደረጃዎችን (ቅድመ መፃፍ፣ የመፃፍ ጊዜ እና ድህረ መፃፍ) እንዲያልፉ ቢደረግ
4. የመፃፍ ክሂልን ለማለማመድ የሚመረጡ የልቦለድ ቅንጫቢዎች የመምረጫ መስፈርቶችን (የተማሪዎችን ፍላጎት፣ የክፍል ደረጃ ወዘተ.) መሰረት ያደረጉ ቢሆን

## ዋቢ ፅሁፎች


ማረው አለሙ (1996) *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

__________ (1998) *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ።* አዲስ አበባ፣ ብርሀን እና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ምህረት ደበበ (2005) *የተቆለፈበት ቁልፍ።* አምስተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ ርሆቦት አታሚዎች።

ሰለሞን ደኑ (2003) ‹‹ ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍሎች መማሪያ መፃህፍት ማሳያነት ›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

በድሉ ዋቅጅራ (2007) *በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር። ሁለተኛ እትም።* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

ባየ ይማም (1997) *የአማርኛ ሰዋስው።* የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ።

ተመስገን ፈቀደ (2001) ‹‹የ11ኛ ክፍል መምህራን የፅህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀት ተዛምዶ (በሀድያ ዞን በሾኔ መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ የተካሄደ ጥናት )›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ተስፋዬ ሸዋዬ (1981) *ስነልሳን እና ቋንቋን ማስተማር።* (ያልታተመ)

__________ (1986) *አንብቦ የመረዳት እና የመፃፍ ችሎታን ማዳበር።* አዲስ አበባ፣

ት.መ.ማ.ማ.ድ።

ታዬ አስራት (2002) ‹‹ በሰንዳፋ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ት/ቤት ለ10ኛ ክፍል ኦሮምኛ አፈፊት ተማሪዎች የአማርኛን ድርሰት ለማስተማር የፈጠራ ስራ ቅንጫቢ (ስነፅሁፍ) ያለው ፋይዳ ›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ነብዩ ጋሹ (2005) ‹‹በግጥም አማካይነት በአማርኛ የአንብቦ መረዳት እና የፅህፈት ችሎታን ማዳበር በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ሙከራዊ ጥናት›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

አስቴር መለሰ (2003) ‹‹ ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አመራረጥ እና አደረጃጀት ፍተሻ ›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ካሳሁን ንጉሴ (2009) *ግልፍልፍ።* አዲስ አበባ፣ የማተሚያ ቤት ስም ያልተጠቀሰ።

ዘመንፈስ ባራኪ. (1991) ‹‹በስነፅሁፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

የሻው ተሰማ (1996) *ልሳነ ብዕር ከመ ልሳነ ብዕር።* አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት።

የአምላክሥራ ሕይወት (2008) ‹‹የአማርኛ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ጽሑፍ ላይ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና፤ በአዲስ አበባ ከተማ በተመረጡ ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች

ተተኳሪነት›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

የዝና ወርቁ (2002) *የደራሲዋ ፋይል።* አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት።

ያለው እንዳወቀ (2004) *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።* ሶስተኛ እትም አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ይስማዕከ ወርቁ (2001) *ዴርቶጋዳ ።* አዲስ አበባ፣ ፋር ኢስት ትሬዲንግ።

ደረጀ ገብሬ (1996) *ተግባራዊ የጽህፈት መማሪያ።* አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዳዊት ፍሬው (2000) ‹‹በደቡብ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋንቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ጌትነት አዲስ (2001) ‹‹ በረጅም ልብ-ወለድ ቅንጫቢ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር ያለው ውጤታማነት በተመረጠ አንድ የምስራቅ ጎጃም ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ግርማ ገብሬ (1990) ‹‹በአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር መስተጋብር ስልት /Interactive Approach) ያለው ተግባራዊነት እና ውጤታማነት›› ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)።

ፈቃደ አዘዘ (1991) ‹‹ አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች፣ ስለስርዓተ ትምህርት፣ ስለመማሪያ መፅሀፍት እና

የስነፅሁፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት (1944-1983) ›› ለቋንቋ ጥናት ተቋም ዘጠነኛ ዓመታዊ ሴሚናር ቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

Albesher, K. B. (2012) "Developing the writing skills of ESL students through the collaborative learning strategy". Unpublished Doctoral Dissertation. University of Newcastle, School of Education, Communication and Language Sciences, Newcastle.

*Almalki*, *S. (2016)* Integrating Quantitative and Qualitative Data in Mixed Methods Research–Challenges and Benefits. *Journal of Education and Learning.* Vol. 5, No. 3

Beaumont, R. (2009) *Research Methods & Experimental Design.*

Benaissa, A (2010) "Teaching Writing Skill and Strategies in the Algerian Secondary School Syllabuses and Textbooks" Unpublished Master`s Thesis, University of Tizi-ouzou, Faculty of Letters and Humanities, Tizi ouzou.

Byrne, D. (1988) *Teaching Writing Skills.* Singapore: Longman Singapore Publisher.

Cohen, L. Manion, L and Morrison, K. (2005) *Research Methods in Education.* (5th ed.) London: Routledge.

Collie, J. and Slater,S. (1987). *Literature in language Classroom.* Cambridge: Cambridge University Press.

Elhabiri, H. (2013) "Teaching the Writing Skills through Literary Texts. Case

of 2nd Year EFL Students at Djilali Liabes University" Unpublished Master`s Thesis. University of Tlemcen, Faculty of Letters and *language*, Tlemcen.

Harmer, J. (2004) *How to teach writing.* Malaysia: Longman.

Hill, J. (1986) *Using literature in language teaching.* London: macmilan Publisher Ltd.

Hişmanoğlu, M. (2005) " Teaching English Through Literature. " *Journal of Language and Linguistic Studies.* Vol.1, No.1.

Khatib, M. (2011) Literature in EFL/ESL Classroom. *English Language Teaching.* Vol. 4, No. 1.

Lazar, G. (1990) Using novels in the language learning classroom. *ELT Journal.* Vol. 44/3.

________ (1993). *Literature and language teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

McKay, S. (1982) Literature In the ESL Classroom. *TESOL Quarterly.* Vol. 16, No. 4.

Pincas, A. (1982) *Teaching English Writing.* London: Macmillan Publishers Ltd.

Raimes, A. (1983) *Techniques in Teaching Writing.* Oxford: Oxford University Press.

Santhi, T. (2012) "Teaching Language through Literature." *Journal of English*

*and Literature* Vol.2, Issue 2.

Shazu, R. I (2014) "Use of Literature in Language Teaching and Learning: ACritical Assessment. " *Journal of Education and Practice.* Vol.5, No.7.

Sorenson, S. (2010) *Student Writing Handbook.* ($5^{th}$ ed.) NewJersey: Wiley, Hoboken.

# አባሪ አንድ

# በረዥም ልቦለድ መፃፍን የማስተማሪያ/የማሰልጠኛ ማቴሪያል

## ለ11ኛ ክፍል የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተዘጋጀ

**አጠቃላይ የተሰጠው ጊዜ፡-** አስራሶስት ክፍለጊዜያት (አንድ ወር) በሳምንት ሶስት ክፌለጊዜያት

## 1ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- ጅምር ዓረፍተ ነገሮችን ማሟላት

***መመሪያ***

***ቅድመ መፃፍ፡-***

1. ቀጥሎ የቀረበውን ቅንጫቢ ርዕስ በመመልከት የደራሲውን የህይወት ታሪክ የሚመለከት አጭር መግለጫ ስጥ/ስጪ፡፡
2. ሶስና በሚል ርዕስ የቀረበውን የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ በለሆሳስ በየግል አንብብ/ቢ፡፡

**ቅንጫቢ አንድ**

**ሶስና**

ሁለተኛዋ የሰሎሜ ቤተሰብ አባል ሶስና ትባላለች፡፡ በመስሪያ ቤታቸው በር ላይ የሊስትሮ ስራ ትሰራ የነበረች የዘጠኝ አመት ልጅ ስትሆን ሰሎሜ ደንበኛ አድርጋት ነበር፡፡ አንድ ጊዜ ለጥቂት ቀን ከጠፋች በኃላ ተመልሳ መጣች፡፡ ግራ እጇ በጨርቅ ተጠቅልሎ፣ ጥውልግልግ ብላ፣ በሊስትሮ ሳጥኗ ላይ ተቀምጣ ባካባቢው ያሉ ወንድ ሊስተሮዎች እየቀለዱባት ስታለቅስ ነበር ሰሎሜ የደረሰችው፡፡ እሷን ሲያዩ ሁሉም ዝም አሉ፡፡

ሶስናን ስታይ ደስ ያላት ሰሎሜ ወደሷው አመራች፡፡ አጠገቧ ተቀምጣ “ምን ሆነሽ ጠፋሽ የኔ ቆንጆ” ስትላት የባሰ ለቅሶዋን ለቀቀችው፡፡ ስፍስፍ ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ የሰሎሜም አንጀት ተላወሰ፡፡ “በቃ በቃ ነይ እስኪ ቢሮ እንግባና እናወራለን” ብላ ሊስትሮ ሳጥኗን ይዛላት የቢሮ ዘበኞቹን ሰላም ብላ ሳጥኑን ለነርሱ ሰጥታ ይዛት ገባች፡፡ ቢሮዋ አስቀምጣት ከካፍቴሪያ ለስላሳ እና ኬክ ነገር አዘዘችላት፡፡

"እስኪ እጅሽ ምን ሆኖ ነው ያሰርሽው?" ስትላት እጇን እንደማሸሽ ብላ ለቅሶዋን ቀጠለች። "አይዞሽ ቀስ ብዬ ነው የማየው" ስትላት "ለአንድ ሰው ብታሳዪ ወየው ብለውኛል… " ብላ ዐይኖቿን የሞላውን ፍርሀት በእንባ ለማስወጣት ይመስል መንታ መንታውን ታዘንበው ጀመረች። ከዚያም ሰሎሜ አባብላ እጇ ላይ ያለውን ቆሻሻ ጨርቅ ስትፈታው ያየችውን ማመን አቃታት። ከክንዷ በታች እጇ ተቃጥሏል። ቁስሉ ደግሞ ህክምና በወቅቱ ያላገኘ በመሆኑ መግል መያዝ እየጀመረ ነው። ጨርቁ ሲነሳ የተጣበቀው ቁስል አብሮ መነሳት ስለጀመረ ሁሉንም ማየት አልቻለችም የሶስናም ስቃይ ስለበዛ። ቀጥሎም ቀጭን ሰውነቷ በግርፋት ሰንበር በሰንበር እንደሆነ ለማየት ቻለች። ራሷን ደባብሳ ስታይ አንድ ሶስት እብጠቶችና በቅጫም የተወረሰ ፀጉር ያለበት ሆኖ አገኘችው። ንዴት ሀዘን ቁጭት… በቃ መንገብገብ ሞላት።

"ማነው እንደዚህ ያደረገሽ?" አለቻት። አይኗን ሰበር አድርጋ "እትዬ ናቸው" አለች። "ለምን?"

"የዚያን ለታ ከስራ ስመለስ መንገድ ላይ ዱርዬዎች ይዘው የሰራሁትን ገንዘብ ሁሉ ቀምተው ደበደቡኝ። አምልጬ ቤት ደርሼ ለእትዬ ስነግራቸው 'ውሽታም ሌባ' ብለው መጋረፍ ጀመሩ። 'እውነቱን አውጪ' እያሉ። እውነቴን ነው ብዬ እያለቀስኩ ብነግራቸው 'ሁለተኛ እንዳይለመድሽ' እያሉ በሻማ እጄን ቀስ እያሉ አቃጠሉኝ። ከዚያም ምንም ምግብ ሳይሰጡኝ አስረው ጨለማ ውስጥ ሁለት ቀን አቆዩኝ።" ብላ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ እሪታዋን ለቃቃቸው። በዚህ ጊዜ ከሰሎሚ ቢሮ አጠገብ የነበሩ ሁለት ጓደኞቿም ለቅሶዋን ሰምተው ኖሮ ተቀላቀሏቸው።

"ዛሬ እንዴት ላኩሽ ታዲያ?" አለች ሰሎሜ። "በጣም ሲርበኝ ጊዜ… በቃ መስረቄን አምኜ ይቅርታ ጠይቄ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ነው የመጣሁት … ዛሬም ምንም አልሰራሁም… እጠፋታለሁ እንጂ እዚያች ቤት አልሄድም።" ብላ ማልቀሷን ቀጠለች።

በኋላ እንደተረዱት ከሆነ ሶስና ወላጆቿን በኤድስ ካጣች በኋላ ወይዘሮ አስካለ ለለቅሶ የመጣውን ቤተዘመድ አግባብተው ሊያሳድጓት ያመጧት ልጅ ናት። ወይዘሮ አስካለን አገር ሁሉ የሚያውቃቸው የድኻ እናት ብሎ ነው። በቅርብ የሚያውቋቸው ግን የድኻ ጠር እንደሆኑ ያውቃሉ። ለመጀመሪያ ስድስት ወር እስከ አንድ አመት ልጆቹን ትምህርት ቤት ይልኳቸዋል፤ ተንከባክበውም ይይዟቸዋል። አንድ ጊዜ ዘመድ አምኖ መጠየቁን ካቆመ በኋላ ግን ትንንሾቹን ሊስትሮና የሰው ልጅ ጠባቂነት፣ ከፍ ከፍ ያሉትን ደግሞ መጠጥ

አሻሻጭና ሴተኛ አዳሪነት ውስጥ ያስገቧቸዋል፡፡ እርሳቸው ቤት ውስጥ አስራ አምስት የሚደርሱ ልጆች ይኖራሉ፡፡ እነሰሎሜ ቤታቸው ሄደው ሊያናግሯቸው ሲሞክሩ መጀመሪያ በሳቅ በፈገግታ ተቀበሏቸው፡፡ ወይዘሮ አስካለ ሰሎሜ ስለሶስና ጉዳይ ስትጠይቃቸው ነገሩን ለማድበስበስ ሞከሩ፡፡ ሁሉንም ነገር እንደምታውቅና አሁን ሶስና ሆስፒታል እንደገባች ስትነግራቸው ነብር ሆኑ፡፡ አመናጭቀውና ተሳድበው ሊከሷት እንደሚችሉ ነግረው ከቤታቸው አስወጧቸው፡፡ ሰሎሜና ጓደኞቿ በቀጥታ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ነገሩን ካመለከቱ በኋላ ወደ ማታ ላይ ልጆቹ ሁሉ ሲገቡ ፖሊሶቹ አብረዋቸው ሄደው ነገሩን እንደሚያጣሩ ተስማሙ፡፡ ሰሎሜ ነገሩን ለአለቃዋ አስረድታ ስለነበር መስሪያ ቤታቸውም ጉዳዩን መከታተል ጀመረ፡፡

ቀኑን ሙሉ ሁኔታውን ከሰፈር አካባቢ በማጣራት የዋሉት ፖሊሶች ማታ ሁለት ሰዓት ላይ ሳይታሰብ የወይዘሮ አስካለን ቤት ወረሩት፡፡ እነሰሎሜም አብረው ተገኝተዋል፡፡ ባንድ ክፍል ተጨናንቀው የሚተኙት ከአስር በላይ ህፃናት ሲሆኑ ሌሎች ሁለት ክፍሎች ደግሞ የሴተኛ አዳሪነት ስራ የሚፈፀምባቸው ክፍሎች ናቸው፡፡ ዕድሜያቸው አስራ አራት እና አስራ አምስት የሆኑ አራት ገና ያላደጉ ሴት ልጆች ይህንን እንዲፈፅሙ ይገደዳሉ፡፡ አንዳንዴም በመጠጥ ሀይል፡፡ አንዲት የውሻ ቤት የምታክል ጨለማ ክፍል ደግሞ ከባድ ጥፋት ያጠፉ ልጆች ታስረው ከረሀብ ጋር የሚቀጡባት ክፍል ናት፡፡ የጉዳዩ ዘግናኝነት ያስደነደጠው የአዲስ አበባ ፖሊስም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን ጠርቶ አገር ያስደነገጠ ፕሮግራም ተዘጋጀበት፡፡ ሶስናም ከሆስፒታል ሆና የደረሰባትን ለህዝብ አካፈለች፡፡ ወይዘሮ አስካለ ወደ እስር ቤት ከገቡ በኋላ የነሰሎሜ መስሪያ ቤት የልጆቹን መልሶ ማቋቋም ኃላፊነት ወሰደ፡፡

ሰሎሜ በብዙ ትግል ሶስናን የራሷ ልጅ አድርጋ ለማሳደግ የህጋዊ ወላጅነት ፈቃድ አገኘች፡፡ ይህ የሆነው እንግዲህ ካንድ ዓመት በፊት ነበር፡፡ ሶስናን ከደረሰባት የስነልቦና ቁስል መፈወስ ግን ቀላል ሆኖ አልተገኘም፡፡

/ምህረት ደበበ፣ **የተቆለፈበት ቁልፍ** ገፅ 37-39/

3. ሶስና በሚል ርዕስ በቀረበው ቅንጫቢ ሀሳብ ላይ በቡድን ተወያዩ፡፡

**ጊዜ መፃፍ፡-** የቅንጫቢውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ የሚከተሉትን ጅምር ሀሳቦች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

1. እነሶስና የወይዘሮ አስካለን በደል አሜን ብለው ይኖራሉ፡፡ ምክንያቱም

___

___

___

2. ሶስናን ከደረሰባት የስነልቦና ቁስል መፈወስ አልተቻለም፡፡ ምክንያቱም

___

___

___

3. ወ/ሮ አስካለን አገር ሁሉ የሚያውቃቸው የድኻ እናት ብሎ ነው፡፡ ምክንያቱም

___

___

___

**ድሕረ መፃፍ፡-** *ፅሁፉ በራሳችሁ አገላለፅ መስፈሩን እና በሙሉ ዓረፍተነገሮች መፃፉን አረጋግጡ፡፡*

## 2ኛው ክፍለ ጊዜ

### ትግበራ፡- ህጎችን ማውጣት

***መመሪያ***

**ቅድመ መፃፍ፡-** ሶስና በሚል ርዕስ ባነበባችሁት ቅንጫቢ ውስጥ ባለታሪኳ(ህፃኗ) የደረሰባትን መንገላታት እና የጉልበት ብዝበዛ በሚመለከት በቡድን ተወያዩ፡፡

**ጊዜ መፃፍ፡-** በቡድን በመሆን፣ በህፃናት ላይ የሚደርሰውን መንገላታት እና የጉልበት ብዝበዛ እንዲሁም የግለሰቦችን መጥፎ ድርጊት ለመስወገድ የሚረዳ ባለአምስት ነጥብ መመሪያ በፅሁፍ አዘጋጁ፡፡

**ድኅረ መፃፍ፡-** ፅሁፋችሁን በማንበብ ግልፅ መልዕክት ማስተላለፋችሁን አረጋግጡ፡፡

## 3ኛው ክፍለ ጊዜ

### ትግበራ፡- አሳጥሮ መፃፍ

***መመሪያ***

**ቅድመ መፃፍ፡-**

1. ፅሁፍን አሳጥሮ ስለመፃፍ ምንነት እና ተግባሩን ስኬታማ በሚያደርጉ ጉዳዮች ዙሪያ በቡድን ተወያዩ፡፡

አህፅሮተ ፅሁፍ አንድን ፅሁፍ በሚፈለገው መጠን አሳጥሮ በጥሩ ቋንቋ መፃፍ ማለት ሲሆን የማሳጠር ተግባሩን ስኬታማ የሚያደርጉ ነጥቦችም

- እንግዳ ቃላትን ከአውዳቸው ለመፍታት መሞከር
- እያነበቡ አጫጭር ማስታወችን መያዝ
- ዋናውን ሀሳብ መለየት
- ፅሁፉን በራስ አገላለፅ መፃፍ ናቸው፡፡

2. ሶስና በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ በየግላችሁ ለሰባት ደቂቃ አንብቡ፡፡
3. ዋና ዋና ነጥቦች የትኞቹ እንደሆኑ በቡድን ተነጋገሩ፡፡

**ጊዜ መፃፍ፡-** ፅሁፉን ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት አሳጥራችሁ ፃፉ

**ድኅረ መፃፍ፡-**

1. ፅሁፋችሁ ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት መፃፉን አረጋግጡ፡፡
2. የቅንጫቢውን ሀሳብ ቃል በቃል አለማስፈራችሁን (በራሳችሁ አገላለፅ መስፈሩን አረጋግጡ፡፡

# 4ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- የፈጠራ ምልልስ መፃፍ

### *መመሪያ*

**ቅድመ መፃፍ፡-**

1. የሚከተለውን ቅንጫቢ የመጀመሪያ አንቀፅ አንብባችሁ ስለቀረው ክፍል ግምታችሁን አስቀምጡ፡፡
2. **ባለውለታ** በሚል ርዕስ የቀረበውን የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ በለሆሳስ በየግላችሁ አንብቡ፡፡

**ቅንጫቢ ሁለት**

**ባለውለታ**

ግርማ አቶ ታምሩን ያወቃቸው አዘዞ- ጎንደር ትምህርቱን ከስድስተኛ ክፍል አቋርጦ ሊስትሮ እየጠረገና ቋጠሮ እየተሸከመ ራሱን ይረዳ በነበረ ጊዜ ነው፡፡ አባቱን አያውቅም፡፡ እናቱ አባትህ ሞቷል ብላዋለች፡፡ እሱ ግን ገና ልጅ እያለ ሌሎች ሰዎች ‹‹ልጅ ነው አያውቅም›› ብለው ፊቱ ላይ ስለ አባቱ ሲያወሩ ብዙ ጊዜ ሰምቷል፡፡ አባቱ ባለ ትዳር ስለነበሩ ዲቃላ ወለዱ እንዳይባልና ሚስታቸውንም ፈርተው ክደውት ነው እንጂ ጎንደር ከተማ ውስጥ ደህና ኑሮ እንደሚኖሩ ሰምቷል፡፡ እናቱ በየሰዉ ቤት እየተቀጠረች ትሰራ በነበረ ጊዜ እንደተወለደ ከሰማው ጭምጭምታ ተነስቶ ይገምታል፡፡ እናቱ ግን ስለዚህ ጉዳይ ማውራት አትወድም፡፡ ግርማም ነፍስ ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንዲት ጠባብ ክፍል ቤት ውስጥ በደባልነት ሲኖሩ ነው የሚያውቀው፡፡

በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ አንድ ቀን እናቱ የቀን ስራ ከተቀጠረችበት ቤት የመሸታ ጠላ ቂጣ ስትጋግር አምሽታ እንደተመለሰች ድንገት ራሴን ብላ ተኛች፡፡ ከዚያ በኋላ ዳግም አልተነሳችም፡፡ ገና በወጣትነት እድሜዋ የምትንሰፈሰፍለትን አንድ ልጅዋን ሜዳ ላይ ጥላው አለፈች፡፡ ግርማ ስለ አባቱም ሆነ ስለእናቱ ቤተሰቦች ስለማያውቅ አለም ድንገት ጨለመችበት፡፡ የሚረዳው ስላልነበረው ትምህርቱን አቋረጠና ጫማ እየጠረገና ቋጠሮ እየተሸከመ ራሱን ማስተዳደር ጀመረ፡፡

አቶ ታምሩም ግርማን ያወቁት በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ እሳቸው በመምህርነት ስራ ላይ ወደ አዘዞ ተዛውረው ሲመጡ ነው፡፡ አንድ ሰፈር ውስጥ ስለነበሩ በቅርበት አይተው በፀባዩ

ወደዱትና መክረው ወደ ትምህርት ቤት መልሰው አስገቡት፡፡ ከሌሎች ወንደ ላጤ መምህራን ጋርም አቀራረቡትና ለነሱም እየተላላከና እየተማረ በትርፍ ጊዜውም ሊስትሮ እየጠረገ ኑሮውን መግፋት ያዘ፡፡ በትምህርቱም ጎበዝ ስለሆነ በዓመት ሁለት ክፍሎችን ማለፍ ቻለ፡፡ አቶ ታምሩም በገንዘብ እየረዱት ያበረታቱት ጀመር፡፡ እሱም ከእናቱ ሞት በኋላ በህይወቱ ውስጥ እንደ ወገን የሚያያቸው ብቸኛ ሰው ስለሆኑለት ወደዳቸው፡፡ እናም የጊዜ ርዝመት ሊያደበዝዘው ያልቻለ የፍቅር አሻራ በልጅነት ንፁህ ልቦናው ውስጥ ታትሞ ቀረ፡፡

ወደ ስምንተኛ ክፍል በተዛወረበት ክረምት ግን አቶ ታምሩ ለክረምት ኮርስ አዲስ አበባ እንደሄዱ በዚያው ዝውውር አገኙ፡፡ ግርማ ደነገጠ፡፡ በአጭሯ የህይወት ዘመኑ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የሚወደውን ሰው አጣ፡፡ አቶ ታምሩም ነሀሴ መጨረሻ ላይ ጓዛቸውን ለማንሳት አዘዞ ሄደው በነበረ ጊዜ ለሌላ መምህር በአደራ ሰጥተውትና እሳቸውም እንደሚረዱት ቃል ገብተውለት ተመለሱ፡፡ በመጀመሪያው አመት ላይ በደብዳቤ ያበረታቱትና ገንዘብም ይልኩለት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ደብዳቤያቸውም የሚልኩት ገንዘብም ተቋረጠ፡፡ አባቱን ያጣ ያህል ይናፍቃቸው ነበር፡፡ በአደራ የተረከበውን መምህር ምን አጋጥሟቸው እንደጠፉ እንዲያጠያይቅለት ቢወተውተውም መምህሩ ብዙም ትኩረት አልሰጠውም፡፡

በመጨረሻ ግን የእናቱን አሟሟት እያሰበ እሳቸውም ድንገት የሞቱ እየመሰለው ሄደና ተስፋውን ቆረጠ፡፡ የባእድ ወዳጅነት ሲለዩ የሚቀር፣ ሲሞቱም የመርዶ ስርዓት የሌለው የመሆኑን የህብረተሰብ ወግ እየተቀበለው ሄዶ ፍለጋውን አቋረጠ፡፡ በልቡ ውስጥ ግን ስለርሳቸው ዘመን ያልሻረው ውዴታና ክብር ተቀርፆ ቀርቷል፡፡

ከሶስት ዓመት በፊት ግን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የማስተማር ስራቸውን ጨርሰው ሲወጡ አራት ኪሎ ላይ ተገናኙ ‹‹ጋሼ ጋሼ›› እያለ ሲጠራቸው ዞረው አዩ፡፡ ጥቁር መልከ መልካም ውሀ ሰማያዊ ጅንስ ጃኬትና ሱሪ የለበሰ ረዘም ባለ ቁመናው ከሳቸው በለጥ ያለ ሰው፣ ወተት የመሰሉ ጥርሶቹን በፈገግታ አስቀድሞ እየቀረባቸው ነበር፡፡ አፈጋገጉ ልባቸውን አስደነገጠውና ቆመው ጠበቁት፡፡ የደስታ ስሜት ፊቱ ላይ እየተንቦገቦገ ‹‹ጋሼ ረሳኸኝ?›› አላቸው፡፡

/የዝና ወርቁ፣ **የደራሲዋ ፋይል** ገፅ 19-21/

**ጊዜ መፃፍ፡-** ልቦለዱን ካነበባችሁ በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን አቶ ታምሩን እና ግርማን በመወከል የፈጠራ ምልልስ ፃፉ፡፡

**ድኅረ መፃፍ፡-** ፅሁፋችሁ የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት ተከትሎ መፃፉን (በሆሄ አፃፃፍ፣ በስርዓተ ነጥብ፣ በሰዋስው ወዘተ) አረጋግጡ፡፡

**ከክፍል ውጪ የሚሰሩ ተግባራት፡-** ባነበባችሁት ልቦለድ ውስጥ አቶ ታምሩ ለግርማ ደብዳቤ እንደሚፅፉ ተገልጿል፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግ አቶ ታምሩን በመወከል ደብዳቤ ፃፉ፡፡

## 5ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- ከቅንጫቢው ተመርጠው የወጡ ቁልፍ ዓረፍተነገሮችን መነሻ በማድረግ አንድ ታሪክ መፃፍ

***መመሪያ***

**ጊዜ መፃፍ፡-** የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች መሰረት በማድረግ በቡድን ሆናችሁ አንድ ታሪክ ፃፉ፡፡ (ቅንጫቢውን ከማንበባችሁ በፊት)

1. ሰማዩ የደመና በርኖሱን ደርቧል፡፡
2. ሰማዩን ከሚያርሰው ብልጭታ በቀር የብርሀን ፍንጥቅታ አይታይም፡፡
3. በወጀብና በውሽንፍር በታጀበው ዶፍ ዝናብ ውስጥ ጥቁር ካፖርት በቁመቱ ልክ የለበሰ ባለጊታር ሰውዬ በባህር ዳር ከተማ አውራ ጎዳና ታየ፡፡
4. በዝናቡ ውስጥ እርቃናቸውን የሚፈነጩት ህፃናት የባለጊታሩን ትኩረት ሳቡት፡፡

**ድኅረ መፃፍ፡-**

1. ቅንጫቢውን በለሆሳስ በየግላችሁ አንብቡ፡፡
2. እናንተ ከፃፋችሁት ታሪክ ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት በተመለከተ ውይይት አድርጉ፡፡

**ቅንጫቢ ሶስት**

## የጳጉሜን ሶስት ገፅታ

ሰማዩ የደመና በርኖሱን ደርቧል፡፡ ጥልማሞት መስሎ በጥቁሩ ደመና ቀኑን አጨልሞታል፡፡ ሰማይና ምድሩ በጭጋግና በጉም አውታር ተያይዟል፡፡

የባህር ዳር ከተማዋ ፀሐይ በጠቋቆረውና በጨላለመው ሰማይ ደን ውስጥ የደመና ቆቧን ደፍታ መንናለች፡፡ ሰማዩን ከሚያርሰው ብልጭታ በቀር ብርሀን ፍንጥቅታ አይታይም፡፡ ሰማዩ በመብረቅ ሲታረስ 'ጨርደድ' በሚለው ነጎድጓድ ምድሩ ይንቀጠቀጣል፡፡ ህይወት ይደነብራል፡፡ ድንብዥ… ድንብዥብዥ… በሚለው አስፈሪ ጉርምርምታ ተራራዎች ያቃስታሉ፤ አለቶች ያቃትታሉ፡፡ ብልጭ ድርግም ከሚለው ሰማይ ማህፀን የተወለደው ጥቁር ደመና ይነፋረቃል፡፡ መብረቁ ሰማዩን 'ጨርደድ' 'ድርግምግም' 'ፍግምግም' ሲያደርገው ህይወት ያማትባል፡፡ ውሽንፈሩ የባህር ዳርን ዘንባባዎች ያስጮሀቸዋል፡፡ በወጀቡ ዛፎች ይሰግዳሉ፡፡ አበባዎች ይረግፋሉ፡፡ ቅጠሎች ይቀነጠሳሉ፡፡ አሮጌው ሰማይ መቋጠር አቅቶት ያፈሳል፡፡

አስራ ሶስተኛዋ ወር ጳጉሜ ከባተች ሶስተኛ ቀኗ ነው፡፡ የባህርዳርን ውበት ሶስተኛዋ የጳጉሜ ቀን አጨፍግጋታለች፡፡ የወራቶች ቅንጣቢ ጳጉሜ ቅንጣቢዋን ከነሀሴ በተዋሰችው የአንድ ቀን የመብረቅ እሳት ትጠብሳታለች፡፡

በወጀብና በውሽንፍር በታጀበው ዶፍ ዝናብ ውስጥ ጥቁር ካፖርት በቁመቱ ልክ የለበሰ ባለጊታር ሰውዬ በባህር ዳር ከተማ አውራ ጎዳና ታየ፡፡ ጥቁር ባርኔጣውን ውሽንፍር እንዳይነጥቀው ከአንገቱ ጋር አያይዞ ከጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ወደ አባይ ማዶ በሚወስደው አውራ ጎዳና ሲጓዝ የለበሰውን ጥቁር ካፖርት ንፋሱ እያንሳፈፈው ነበር፡፡

በዝናቡ ውስጥ እርቃናቸውን የሚፈነጩት ህፃናት የባለጊታሩን ትኩረት ሳቡት፡፡ ዶ/ር ሚራዥን፡፡ህፃናቱ ዝናቡ ውስጥ እርቃናቸውን እየቦረቁ እየተሳሳቁ "ሩፋኤል…ሩፋኤል…ሩፋኤል…ሩፋኤል… ከሸንብራው ጎታ ስደደኝ ጌታዬ…" ይላሉ፡፡ ጳጉሜ ሶስት ቀን መሆኑን ያወቀው በህፃናቱ ዜማ ነበር፡፡

/ይስማዕከ ወርቁ፣ **ዴርቶጋዳ** ገፅ 122/

# 6ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- በገለፃ ስልት አንቀፅ መገንባት

### መመሪያ

**ቅድመ መፃፍ፡-**

1. **የጳጉሜን ሶስት ገፅታ** በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ አንብቡ፡፡
2. ቅንጫቢው በየትኛው የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት የተፃፈ ነው?
3. ስለአንቀፅ ማስፋፊያ ስልቶች ምንነት እና ባህሪያት ተወያዩ፡፡

**የገለፃ ስልት፡-** ገለፃ ማካሄድ አንዱ የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት ነው፡፡

- የገለፃ ስልት በአንባቢ አዕምሮ ምስል የሚከስት ነው፡፡
- ገለፃው የሚካሄደው ስለአየር ጠባይ፣ ስለሰው፣ ስለቦታ፣ ስለድርጊት ወዘተ... ሊሆን ይችላል፡፡
- በገለፃ ስልት አንቀፅ ስንገነባ ምስል ከሳች ቃላትን መምረጥ ይኖርብናል፡፡ ተገላጩን ነገር ፍንትው አድርገን በማሳየት በአንባቢያን አዕምሮ ውስጥ ስእል መፍጠር መቻል ይኖርብናል፡፡
- በተደራሲያን ምናብ የጉዳዩን ምስል (ጣእም፣ መልክ፣ ቁመና፣ ሽታ፣ባህሪ፣ ካርታ ወዘተ...) መከሰት መቻል ነው፡፡

**ጊዜ መፃፍ፡-**

ባለጊታሩ የሚለውን ቅንጫቢ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንዱን

መርጣችሁ በገለፃ ስልት የተስፋፋ አንቀፅ ገንቡ፡፡

ሀ) እንጦጦ ተራራ

ሐ) የምወደው ሰው ቁመና

ለ) የሸሮ ሜዳ የበዓል ገበያ

መ) አውቶቢስ ተራ

## 7ኛው ክፍለ ጊዜ

### ትግበራ፡- በገለፃ ስልት አንቀፅ መገንባት

***መመሪያ***

**ድኅረ መፃፍ፡-** (ከስድስተኛው ክፍለ ጊዜ የቀጠለ)

1. በገለፃ ስልት ያስፋፋችሁትን አንቀፅ ካነበባችሁ በኋላ የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት ተከትሎ መፃፉን (በሆሄ አፃፃፍ፣ በስርዓተ ነጥብ፣ በሰዋስው ወዘተ) እና ምስል ከሳች መሆኑን አረጋግጡ።
2. መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን የገነባችሁትን አንቀፅ ተቀያይራችሁ የቢጤ እርማት አካሂዱ።

## 8ኛው ክፍለ ጊዜ

### ትግበራ፡- ትንበያን መጻፍ

***መመሪያ***

**ቅድመ መፃፍ፡-**

1. የሚከተለውን ቅንጫቢ ርዕስ ተመልክታችሁ ይዘቱ ስለምን እንደሚሆን ግምታችሁን በፅሁፍ አስፍሩ።
2. **ቀጠሮ** በሚል ርዕስ የቀረበውን የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ በለሆሳስ በየግል አንብቡ፡ ፡

**ቅንጫቢ አራት**

**ቀጠሮ**

መላኩ እቀጠሮው ስፍራ ለመድረስ ግማሽ ሰዓት ብቻ ቀርቶታል። ልቡ ስቅል ማለቱን አረማመዱ ያሳብቃል። መኪናውን በጥድፊያ አቁሞ ከኋላ ወንበር ሳምሶናይት ቦርሳውን አፈፍ አድረጎ ወረደና ወደ መኖሪያ አፓርታማው ተጣደፈ። የስራ ልብሱን ቀይሮ ሰሞኑን በስንት ምጥ ሲፅፍ የከረመውን ፅሁፍ ይዞ ወደ ፒያሳ ሊከንፍ ነው ዕቅዱ። ሰሎሜ ደግሞ

በሰዓት ጉዳይ ዝንፍ አትልም፡፡ አርፋጅም ከሷ ጋር ከነሙሉ ክብሩ አይሰነብትም፡፡ ከቦሌ ፒያሳ ድረስ ለመሄድ ስንት መሰናክል አለበት፡፡ መብራቱ፣ ታክሲው፣ እግረኛው፣ ኧረ ምኑ ቅጡ! ፒያሳ ለምን እንደተቀጣጠሩ ሲያስብ ለጊዜው በቂ ምክንያት ሊመጣለት አልቻለም፡፡ ደረጃውን በተቻለ ፍጥነት ወጥቶ ሶስተኛ ፎቅ ካለው አፓርትመንቱ ደርሶ ቁልፉን ከኪሱ ቢዳስስ ቢያስስ አጣው፡፡ በመጣበት ፍጥነት ከንፎ ከመኪናው ዘንድ ሲደርስ ሞተሩን እንዳላጠፋው አወቀ፡፡

የሹፌሩን በር ሊከፍት ሳብ ቢያደርገው ተቆልፏል፡፡ በድንጋጤ ክው አለ፡፡ እየዞረ አራቱንም በሮች ፈተሸ፣ አንዳቸውም ክፍት አልነበሩም፡፡ “አ…መ-ላ-ኩ… ምን ነካህ?” አለና እጁን እያወናጨፈ መኪናውን ተደግፎ ቆመ፡፡ ስሜቱን ለማረጋጋት እየሞከረ በሾፌሩ መስኮት አጮልቆ ተመለከተ፡፡ በመኪናው የቁልፍ ማስገቢያ ውስጥ ያለውን ቁልፍ አጅበው ከአምስት የማያንሱ ሌሎች ቁልፎቹ ተንጠልጥለው ላመል ያህል ይወዛወዛሉ፤ እንቁልልጭ ይሉ ይመስል፡፡ ተቀያሪ ቁልፎቹ ደግሞ እቤት ውስጥ ተቆልፎባቸዋል፡፡ “የተቆለፈበት ቁልፍ እኔንም ቆላልፎ አስቀረኝ!” አለና መስኮቱን ለመስበር አሰበ፡፡ ኪሳራው ታየው፡፡ በሽቦም ሰርስሮ ለመክፈት ሞክሮ አቃተው፡፡ መፍትሄ ፍለጋ አንድ ሁለት ጓደኞቹ ጋር ደውሎ ሊያገኛቸው አልቻለም፡፡ የሰሎሜን ስልክ ደጋግሞ ቢሞክር አይመልስም፡፡ መላኩ ሁሉም የጠመመበት መሰለው፡፡ ለቀጠሮው የቀረው አስራ ሰባት ደቂቃ ብቻ ነው፡፡ ግንባሩ ላይ ያቸፈቸፈውን ላብ በእጁ መዳፍ ጠራረገና ለትንሽ ጊዜ አእምሮውን አረጋግቶ ማሰብ ጀመረ፡፡ ድንገት ፈፅሞ ያልጠበቀው የመፍትሄ ብልጭታ ፊቱን እንደ ጠዋት ፀዳል አበራው፡፡

/ምህረት ደበበ፣ **የተቆለፈበት ቁልፍ** ገፅ 1/

**ጊዜ መፃፍ፡-** ካነበባችሁት ፅሁፍ ያገኛችሁትን መረጃ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምታችሁ ከ70 ባላነሱ ቃላት ቀጣዩን ታሪክ አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

## 9ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- ርዕስ በመምረጥና በማጥበብ አስተዋፅ/ቢጋር መንደፍ

***መመሪያ***

**ቅድመ መፃፍ፡-**

1. ስለድርሰት ምንነት፣ ርዕስ አመራረጥ እና አስተዋፅኦ መንደፍ በቃል ግለፁ፡፡
2. ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችሉ ርዕሶችን በቡድን ምረጡ፡፡

**ጊዜ መፃፍ፡-** የመረጣችሁት ርዕስ መሰረት በማድረግ በቡድን አስተዋፅኦ ንደፉ፡፡

**ምሳሌ፡-**

ርዕስ - የጎዳና ህይወት

1. ለጎዳና ህይወት የሚዳርጉ ምክንያቶች
   1.1. የቤተሰብ መፍረስ
   1.2. ከመጥፎ ጓደኛ ጋር መወዳጀት
   1.3. በአጉል ሱሶች መጠመድ
      1.3.1. በሲጋራ
      1.3.2. በጫት
      1.3.3. በአልኮል መጠት
2. የጎዳና ተዳዳሪዎች የሚፈፅሟቸው ተግባራት
   2.1. ልመና
   2.2. ስርቆት
3. የጎዳና ተዳዳሪነትን እንዴት ማስወገድ ይቻላል፡፡

## 10ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- ድርሰት መፃፍ

***መመሪያ***

**ቅድመ መፃፍ፡-** ስለድርሰት ክፍሎች ማብራሪያ ስጡ፡፡

ድርሰት ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ናቸው፡፡ መግቢያ የፅሁፉን ሀተታ መሰረታዊ ቁምነገር ማስተዋወቂያ በመሆኑ ርእሰ ነገሩን ነጥሎ የሚያሳይ እና ገደቡን ወስኖ የሚስቀምጥ ነው፡፡ ሐተታ ደግሞ ርዕሱ ሰብስቦ ያካተታቸውን ፍሬ ሀሳቦች በበቂ መረጃ አዳብሮ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ መደምደሚያ ከአንባቢ የምንሰነባበትበት የመጨረሻ የድርሰት ክፍል ሲሆን ምን ምን ጉዳዮችን እንዳነሳን፣ ስለ ጉዳዩ ያለን አተያይ ምን እንደሆነ አንባቢ ምን ማድረግ እንዳለበት የምናሰፍርበት ክፍል ነው፡፡

**ጊዜ መፃፍ፡-** ባለፈው ክፍለ ጊዜ በቡድን የነደፉችሁትን ቢጋር መሰረት በማድረግ በየግላችሁ ድርሰት ፃፉ፡፡ (ድርሰታችሁ መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያን ያካተተ ሊሆን ይገባዋል፡፡)

## 11ኛው ክፍለ ጊዜ

## ትግበራ፡- የቢጤ እርማት ማካሄድ

### *መመሪያ*

**ድኅረ መፃፍ፡-** (ከ10ኛው ክፍለ ጊዜ የቀጠለ)

1. ባለፈው ክፈለጊዜ የፃፋችሁትን ድርሰት ካነበባችሁ በኋላ የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት ተከትሎ መፃፉን (በሆሄ አፃፃፍ፣ በስርዓተ ነጥብ፣ በሰዋስው በቃላት አመራረጥ ወዘተ)፣ መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ አንቀፆችን ያካተተ መሆኑን አረጋግጡ፡፡
2. መምህራችሁ በሚያዟችሁ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን የፃፋችሁትን ድርሰት ተቀያይራችሁ የቢጤ እርማት አካሂዱ፡፡

## 12ኛው ክፍለ ጊዜ

### ትግበራ፡- ቅድመ ታሪክን መፃፍ

**መመሪያ፡-**

**ቅድመ መፃፍ፡-**

1. የሚከተለውን ቅንጫቢ ርዕስ ተመልክታችሁ ይዘቱ ስለምን እንደሚሆን ግምታችሁን በፅሁፍ አስፍሩ፡፡
2. የጠፋ ሲገኝ በሚል ርዕስ የቀረበውን የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ በለሆሳስ በየግል አንብቡ፡፡

**ቅንጫቢ አምስት**

**የጠፋ ሲገኝ**

ህሊና እንደለመደችው ከት/ቤት ተመልሳ፣ ከቤታቸው በስተጀርባ በመቀመጥ የጠቢቡን ፎቶ አልበም ከጭኗ ላይ አድርጋ አንድ በአንድ እያገላበጠች ታያለች፡፡ በድንገት የእናቷን ጩኸት ሰማች፡፡ በድንጋጤ ከተቀመጠችበት ተነስታ ቆመች፡፡ ጩኸቱ ወደ እልልታ ተቀየረ፡፡ የፎቶ አልበሙን መሬት ላይ እንደዘረረችው የቤቱን ጥግ በመዞር ወደ በር ሮጠች፡፡ ወ/ሮ አትጠገብ ከሶስት ሰዎች መካከል አንዱን አንቀው ይዘውት እልልታው አልቆ ያለቅሳሉ፡፡ እንባቸው ከትከሻው ላይ ዝርግፍግፍ እያለ የትከሻውን ልብስ አርሶታል፡፡ እሱም እንደዚሁ እሳቸውን አንቆ ይዞ ያለቅሳል፡፡ ደጋግመው ይስሙታል፡፡ ለቀውት ወደ ኋላ አንጋደው ከተመለከቱት በኋላ ከደረታቸው አላትመው ይይዙታል፡፡ በእጃቸው ጭንቅላቱን ይዘው አንዴ አንገቱን አንዴ ፊቱን ደጋግመው ይስሙታል፡፡ እጃቸውን ወደ ሰማይ ዘርግተው አምላካቸውን ያመሰግናሉ፡፡ መልሰው አንቀው በመያዝ ይስሙታል፡፡ ቢስሙት ቢስሙት አልጠገቡትም፡፡ ወደሆዳቸው ሊያስገቡት ምንም አልቀራቸውም፡፡ ህሊና ሁሉን ተቋቁማ ድርጊቱን ስትመለከት ቆየች፡፡ ግንባሯ ቁጥር ፊታ ይላል፡፡ እንባዋ ኮለል ኮለል እያለ በፊቷ ይወርዳል፡፡ እንባዋን እየጠረገች ሳቅ ሳቅ ትላለች፡፡ ፊቷ በደስታ ተሞልቷል፡፡ ግንባሯ ወገግ ብሏል፡፡ ጠቢቡ እናቱን አቅፎ እንደያዘ አይኑን ወደ ህሊና በመላክ ተመለከታት፡፡ ህሊና ለመሆኗ ተጠራጠረ፡፡ በጣም ከስታለች፡፡ በጣም አሳዘነችው፡፡ ሆዱ ቦጭ ቦጭ አለ፡፡ በእሱ ምክንያት ቤተሰብ ምስቅልቅል ብለው ሲያገኛቸው በልቡ አለቀሰ፡፡ የእናቱን ሰላምታ ጨርሶ ወደ ህሊና በመሄድ ህሊናን አቅፎ ሳማት፡፡ ህሊና

እንባዋ በፊቷ ከመንከባለል ውጪ አትናገርም፤ አትጋገርም። ውስጧ በደስታ ቢፈነጥዝም ደንዝዛለች። ሲስማት ከመሳም ውጪ መልሳ አልሳመችውም። እንባዋን እየጠራረገ ተመለከታት። አሁንም ማልቀስ ጀመረች። ወ/ሮ አትጠገብ ሁለቱንም አቅፈው በመያዝ አለቀሱ። ሁሉም ተላቀሱ። መንገድ ላይ አግኝተውት አብረው ከመጡት ጓደኞቹ አንዱ ከመሀላቸው በመግባትና በማረጋጋት ማልቀሳቸውን እንዲያቆሙ አደረጋቸው።

/ካሳሁን ንጉሴ፣ **ጥልፍልፍ** ገፅ 271-272/

**ጊዜ መፃፍ**

በቡድን በመሆን ባነበባችሁት ቅንጫቢ ሀሳብ ላይ ከተነጋገራችሁ በኋላ በየግላችሁ ምዕራፍ ዜሮን ፃፉ (ቀደም ብሎ የተፈፀመውን ድርጊት የሚያሳይ ታሪክ ፅፋችሁ አቅርቡ)።

የሚከተለውን ሀሳብ መነሻ አድርጉ

ጠቢቡ ከቤተሰቡ ጋር በዚህ ሁኔታ ከመገናኘቱ በፊት

- ለምን ጠፋ?
- የት ነበር?
- እንዴት ሊመለስ ቻለ?

**ድኅረ መፃፍ፡-** ፅሁፋችሁን ካነበባችሁ በኋላ የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት ተከትሎ መፃፉን (በሆሄ አፃፃፍ፣ በስርዓተ ነጥብ፣ በሰዋስው በቃላት አመራረጥ፣ በአንቀፆች አደረጃጀት ወዘተ)።

**ከክፍል ውጪ የሚሰሩ ተግባራት**፡- ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ ድርሰት ፃፉ።

ሀ) ወይዘሮ አትጠገብ ማን ናቸው?

ለ) የማልረሳው ዕለት

ሐ. እናት

## 13ኛው ክፍለ ጊዜ

### ትግበራ፡- የአፋልጉኝ ማስታወቂያ ናሙና መፃፍ

***መመሪያ፡-***

**ጊዜ መፃፍ**

የጠቢቡን ቤተሰብ (የጠፋ ሲገኝ በሚል ርዕስ በቀረበው ቅንጫቢ የጠፋውን ገፀባህሪ ቤተሰቦች) በመወከል የአፋልጉኝ ማስታወቂያ ፃፉ፡፡

***ድኅረ መፃፍ፡-*** *ፅሁፋችሁን ካነበባችሁ በኋላ የቋንቋውን የአፃፃፍ ስርዓት ተከትሎ መፃፉን* (በሆሄ አፃፃፍ፣ በስርዓተ ነጥብ፣ በሰዋስው፣ በቃላት አመራረጥ፣ በአንቀፆች አደረጃጀት ወዘተ)፡፡

# የትምህርት ዝግጅት

| ቀን | የቅንጫቢ ዎች ርዕስ | የትምህርቱ ይዘት | የትምህርቱ ዓላማ | ተግባራት |
|---|---|---|---|---|
| 26/06/10 | ሶስና | ጅምር ዓረፍተነገሮችን አሟልቶ መፃፍ | ጅምር ዓረፍተ ነገሮች አሟልተው ይፅፋሉ፡፡ | • ቅንጫቢውን ማንበብ<br>• በጥንድ ውይይት ማካሄድ<br>• ቅንጫቢውን መነሻ በማድረግ ጅምር ዓረፍተነገሮችን አሟልቶ መፃፍ |
| 29/06/10 | | መመሪያ ማዘጋጀት | የቅንጫቢውን ታሪክ መነሻ በማድረግ የግለሰቦችን መጥፎ ድርጊት ለማስወገድ የሚረዳ ባለ አምስት ነጥብ መመሪያ በፅሁፍ ያዘጋጃሉ፡፡ | • ሀሳቡ ላይ በቡድን መወያየት<br>• በቡድን መመሪያ ማዘጋጀት |
| 30/06/10 | | ፅሁፍን ማሳጠር | ቅንጫቢውን ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት ያሳጥራሉ፡፡ | • ፅሁፍን የማሳጠር ምንነትና መመሪያን በቃል መግለፅ<br>• ቅንጫቢውን ማንበብ<br>• ዋና ዋና ሀሳቦች ላይ በጥንድ ውይይት ማካሄድ<br>• ፅሁፉን ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት ማሳጠር |
| 03/07/10 | ባለውለታ | የፈጠራ ምልልስ | ጥንድ ጥንድ በመሆን የፈጠራ ምልልስ ይፅፋሉ፡፡ | • ቅምጫቢውን በለሆሳስ ማንበብ<br>• ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን በፅሁፍ መመለስ<br>• ጥንድ ጥንድ በመሆን በቅንጫቢው የቀረቡ ገፀባህሪያትን ወክለው የፈጠራ ምልልስ መፃፍ |
| | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 06/07/10 | የጳጉሜን ሶስት ገፅታ | ቁልፍ ዓረፍተነገሮችን መነሻ በማድረግ አንድ ታሪክ መፃፍ | ቁልፍ ዓረፍተነገሮችን መነሻ በማድረግ አንድ ታሪክ ይፅፋሉ፡፡ | • ቅምጫቢውን ከማንበባቸው በፊት ቁልፍ ዓረፍተነገሮችን መነሻ በማድረግ አንድ ታሪክ መፃፍ<br>• ቅንጫቢውን በየግላቸው በለሆሳስ ማንበብ<br>• እነሱ ከፃፉት ታሪክ ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት ላይ መወያየት |
| 07/07/10 | | በገለፃ ስልት አንቀፅ መገንባት | በገለፃ ስልት አንቀፅ ይገነባሉ፡፡ | • ቅንጫቢውን በየግላቸው ማንበብ<br>• ያነበቡት ቅንጫቢ በየትኛው የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልት እንደተገነባ መግለፅ<br>• ስለገለፃ ስልት ምንነት መግለፅ<br>• ከተሰጡ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ በገለፃ ስልት አንቀፅ መገንባት |
| 10/07/10 | | በገለፃ ስልት የተገነባውን አንቀፅ መከለስ | በገለፃ ስልት አንቀፅ ይገነባሉ፡፡ | • ባለፈው ክፍለ ጊዜ በገለፃ ስልት ያስፋፉትን አንቀፅ አንብበው ማስተካከል /መከለስ (ፅሁፋቸው የስርዓተ ነጥብ፣ የሰዋስው ስርዓት ወዘተ. ተስተካክሎ መመፃፉን ማረም<br>• ጥንድ ጥንድ በመሆን ስራቸውን ተቀያይረው የቢጤ እርማት ማካሄድ |
| 13/07/10 | ቀጠሮ | ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ቀጣዩን ታሪክ መፃፍ | ካነበቡት ፅሁፍ ያገኙትን መረጃ መሰረት አድርገው ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ቀጣዩን ታሪክ አሟልተው ይፅፋሉ፡፡ | • የቅንጫቢውን ርዕስ ተመልክተው ይዘቱ ስለምን እንደሚሆን ግምታቸውን በፅሁፍ ማስፈር<br>• ቅንጫቢውን በየግላቸው በለሆሳስ ማንበብ<br>• ካነበቡት ፅሁፍ ያገኙትን መረጃ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ቀጣዩን ታሪክ አሟልተው መፃፍ |
| 14/07/10 | | ርዕስ በመምረጥ እና በማጥበብ | ርዕስ በመምረጥ እና በማጥበብ ቢጋር ይነድፋሉ፡ | • ስለድርሰት ምንነት፣ ርዕስ አመራረጥ እና አስተዋፅኦ መንደፍ ውይይት ማካሄድ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ቢ.ጋር መንደፍ | | • ርዕሶችን በመምረጥ እና በማጥበብ በጋራ መወያየት<br>• በቡድን በመሆን ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችሉ ርዕሶችን መምረጥ፣ ማጥበብ እና ቢ.ጋር መንደፍ |
| 17/07/10 | | ድርሰት መፃፍ | ድርሰት ይፅፋሉ፡፡ | • ስለድርሰት ክፍሎች በጋራ ውይይት ማካሄድ<br>• ባለፈው ክፍለ ጊዜ በቡድን የነደፉትን ቢ.ጋር መሰረት በማድረግ በየግልቸው ድርሰት መፃፍ |
| 18/07/10 | | ድርሰት መፃፍ | • ድርሰቱን በመከለስ አስተካክለው ይፅፋሉ፡፡<br>• የቢ.ጤ እርማት ያካሂዳሉ፡፡ | • ባለፈው ክፍል ጊዜ የጀመሩትን ድርሰት አጠናቀው መፃፍ<br>• ድርሰቱን በመለዋወጥ የቢ.ጤ እርማት ማካሄድ<br>• በተሰጡ አስተያየቶች ላይ በጥንድ መወያየት |
| 20/07/10 | የጠፋ ሲገኝ | ምዕራፍ ዜሮን መፃፍ | በቅንጫቢው ከቀረበው ታሪክ ቀደም ብሎ የተፈፀመውን ታሪክ ይፅፋሉ፡፡ | • የቅንጫቢውን ርዕስ ተመልክተው ታሪኩን መተንበይ<br>• ቅንጫቢውን በለሆሳስ በየግላቸው ማንበብ<br>• በቅንጫቢው ከቀረበው ታሪክ ቀደም ብሎ የተፈፀመውን ታሪክ በመገመት ምዕራፍ ዜሮን መፃፍ |
| 21/07/10 | | የአፋልጉኝ ማስታወቂያ ናሙና መፃፍ | ባነበቡት ቅንጫቢ ውስጥ የጠፋውን ገፀባህሪ ቤተሰቦች በመወከል የአፋልጉኝ ማስታወቂያ ናሙና ይፅፋሉ፡፡ | • ባለፈው ክፍለጊዜ በፃፉት ድርሰት ላይ በጥንድ ውይይት ማካሄድ<br>• ባነበቡት ቅንጫቢ ውስጥ የጠፋውን ገፀባህሪ ቤተሰቦች በመወከል የአፋልጉኝ ማስታወቂያ መፃፍ |

# አባሪ ሁለት

## የምልከታ ማስታወሻ

**ቀን አንድ፡-** ሰኞ፣ 26/06/10፣ 5ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 37

ይህ ዕለት የመማር ማስተማሩ ስራ የተጀመረበት ቀን እንደመሆኑ የጥናቱን ዓላማ እና ከተማሪዎች የሚጠበቁ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በድጋሚ ለማስታወስ ተሞክሯል፡፡ ከዚህ በኋላ "ሶስና" የሚለውን ቅንጫቢ ለተማሪዎች በነፍስ ወከፍ በማደል የማስተማሩ ስራ ተጀመረ፡፡ ፅሁፉን ከማንበባቸው በፊት የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለመቀስቀስ እና ለትምህርቱ ዝግጁ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ እነዚህም (Lazar 1993፣ 84) የጠቀሷቸው፣ የደራሲውን የህይወት ታሪክ የሚመለከት አጭር መግለጫ መስጠት እና ቅንጫቢን ማስተዋወቅ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ሶስና የሚለው ቅንጫቢ የተወሰደው የተቆለፈበት ቁልፍ ከሚለው ረዥም ልቦለድ እንደሆነ በመግለፅ ደራሲውን ያውቁት እንደሆነ እና ስራዎቹን ስለማንበባቸው መምህርቷ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ሁለት ተማሪዎች እጃቸውን አወጡ፡፡ ሁለቱ ተማሪዎች በየተራ ተጠይቀው ደራሲው ዶ/ር ምህረት ደበበ መሆኑን፣ ነገር ግን መፅሀፉን አለማንበባቸውን ገለፁ፡፡ ሌሎች እጅ ያወጡ ተማሪዎች ባለመኖራቸው ስለደራሲው የህይወት ታሪክ አጭር መግለጫ እና ቅንጫቢውን የሚመለከት ጥቆማ ቀርቧል፡፡

በመቀጠልም ተማሪዎች ቅንጫቢውን በለሆሳስ በየግላቸው እንዲያነቡ ተነገራቸው፡፡ አንብበው ከጨረሱ በኋላ የማያውቋቸው አዳዲስ ቃላት ካሉ፣ እነሱን እንዲያቀረቡ በተጠየቁ ጊዜ አንጀቷ ተላወሰ እና ሰንበር በሰንበር የሚሉ ቃላትን ፍቺ እንደማያውቋቸው ሁለት ተማሪዎች ገለፁ፡፡ በዚህ መሰረት ሌሎች ተማሪዎች ለቃላቱ ፍቺ እንዲሰጡ ተጋብዘው መልሰዋል፡፡ ከዚያም ቅንጫቢውን መነሻ በማድረግ ጅምር ዓ/ነገሮችን እንዲያሟሉ የቀረበውን መልመጃ በጥንድ ከተወያዩ በኋላ በየግላቸው እንዲፅፉ ታዘዙ፡፡ በዚህ ጊዜ ጥቂት ተማሪዎች ወደ ፅሁፍ ስራው ሲገቡ ጥቂቶች ደግሞ ቅንጫቢውን ደግመው ያነባሉ፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች ግን ስለሚፅፉት ነገር የማሰብ አልያም ለመስራት አለመፈለግ እና ፍራቻ ይነበብባቸዋል፡፡ እነዚህን ተማሪዎች በማበረታታት ፅሁፉን እንዲጀምሩት ለማድረግ ተችሏል፡፡

የተማሪዎችን ስራ በመዘዋወር ለማየት እንደተሞከረው፣ በፅሁፋቸው ላይ የተለያዩ ችግሮች ተስተውለዋል፡፡ ከነዚህም ችግሮች መካከል የቅንጫውን ታሪክ ሙሉ ለሙሉ መገልበጥ፣ ዓ/ነገሮችን አሟልቶ አለመፃፍ/ሀሳባቸውን በቃላት እና በሀረጋት መዘርዘር፣ የእጅ ፅህፈት አለመነበብ፣ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህን እንዲያስተካክሉ ተነገራቸው፡፡ ፅፈው ካጠናቀቁ በኂላ ወረቀቱ ተሰበሰበ፡፡

**ቀን ሁለት፡-** ሀሙስ፣ 29/06/10 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 35

የዕለቱ ተግባር፣ የታረመው የተማሪዎች ወረቀት ላይ አስተያየት በመስጠት ተጀመረ፡፡ ይኸውም ልምምዱ የመጀመሪያ እንደመሆኑ የሁሉም ተማሪዎች ሙከራ ጥሩ እንደነበረ በመግለፅና የሶስት ተማሪዎችን ፅሁፍ በማንበብ እነዚህን ስራዎች ከሞላ ጎደል የተሻሉ የሚያደርጓቸውን ነጥቦች በማንሳት መምህርቷ ማብራሪያ ሰጡ፡፡ ከዚያም ወረቀቱን በመመለስ እያንዳንዱ ተማሪ ስህተቶቹን እንዲያጤን እንዲሁም በጥንድ በመሆን እንዲነጋገሩበት ሰባት ደቂቃ ተሰጣቸው፡፡

የዕለቱን ርዕስ በማስተዋወቅ ተማሪዎች ስድስት አባላትን የያዘ ቡድን እንዲመሰርቱ በተነገራቸው ጊዜ ሁለት ዴስኮችን በአንድ ላይ በማድረግ እንዳቀማመጣቸው እንዲቧደኑ ሀሳብ አቀረቡ፡፡ በዚህም በመስማማት ቡድኑ ተመሰረተ፡፡

በመቀጠልም "በቡድን በመሆን፣ በህፃናት ላይ የሚደርሰውን መንገላታት እና የጉልበት ብዝበዛ እንዲሁም የግለሰቦችን መጥፎ ድርጊት ለመስወገድ የሚረዳ ባለአምስት ነጥብ መመሪያ አዘጋጁ፡፡ " የሚለውን ጥያቄ እንዲሰሩ ታዘዙ፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያ ሀሳቡ ላይ በቃል እንዲነጋገሩ፣ ከዚያም ሀሳባቸውን ወደ ፅሁፍ እንዲለውጡ በተነገራቸው መሰረት ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ ስራቸውን በመዘዋወር ለማየት እንደተሞከረው አብዛኞቹ ቡድኖች ሀሳባቸውን ያስቀመጡት በአንድ ዓ/ነገር ነው፡፡ የታዩ ችግሮችም የሰዋስው ስህተት የስርዓተ ነጥቦች አለመካተት፣ የቃላት አመራረጥ ችግሮች ናቸው፡፡ እነዚህን ስህተቶች በመጠቆም እንዲያስተካክሉ ተነገራቸው፡፡

በመጨረሻም በተነገራቸው መሰረት እያንዳንዱ ቡድን ፅሁፉን ማስተካከል ጀመረ፡፡ ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ የእለቱ ትምህርት በዚሁ አበቃ፡፡

**ቀን ሶስት፡-** አርብ፣ 30/06/10 7ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 38

ይህ ክፍለ ጊዜ የመጨረሻ (7ኛ ክፍለ ጊዜ) በመሆኑ ተማሪዎች የድካም ስሜት ይታይባቸዋል። ለማነቃቂያ የሚሆን ሀሳብ እንዲያቀርቡ ተጠየቁ። ጥያቄውም ባነበቡት ቅንጫቢ ውስጥ ከተገለፀችው ገፀባህሪ ህይወት ጋር የሚመሳሰል ታሪክ በአካባቢያቸው ተከስቶ ከሆነ ያንን እንዲገልፁ ነው። አምስት ተማሪዎች እጅ ያወጡ ሲሆን ቀድመው ላወጡ ሁለት ተማሪዎች እድል ተሰጠ። የመጀመሪያው ተማሪ ከገፀባህሪዋ ህይወት ጋር የሚመሳሰል ታሪክ በሚኖርበት አካባቢ የሰማ መሆኑን ገለፀ። ሁለተኛዋ ተማሪ ይህን ታሪክ በፊልም ያየች ስለመሆኑ ስትናገር ተማሪዎች በጥሞና ያዳምጧት ጀመር።

በማነቃቂያ የተጀመረውን ክፍለ ጊዜ በመቀጠል የእለቱ ትምህርት ርዕስ ተገለፀ። የዕለቱ ተግባር "ፅሁፉን ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት አሳጥራችሁ ፃፉ። " የሚል ነው። ፅሁፉን ከመጀመራቸው በፊት በመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት አህፅሮተ ፅሁፍ የሚል ርዕስ ስለመማራቸው በማስታወስ ምንነቱን እና መመሪያዎቹን እንዲገልፁ ተጠየቁ። በዚህ መሰረት አህፅሮተ ፅሁፍ አንድን ፅሁፍ በሚፈለገው መጠን አሳጥሮ በጥሩ ቋንቋ መፃፍ ማለት ሲሆን የማሳጠር ተግባሩን ስኬታማ የሚያደርጉ ነጥቦችም

- እንግዳ ቃላትን ከአውዳቸው ለመፍታት መሞከር
- እያነበቡ አጫጭር ማስታወሻችን መያዝ
- ዋናውን ሀሳብ መለየት
- ፅሁፉን በራስ አገላለፅ መፃፍ መሆናቸውን ተማሪዎች ጠቅሰዋል።

ይህንኑ መሰረት አድርገው ቅንጫቢውን አሳጥረው እንዲፅፉ ተነገራቸው። በመጀመሪያ ቅንጫቢውን ለሰባት ደቂቃ በለሆሳስ እንዲያነቡ ተደረገ። በመቀጠልም ጥንድ ጥንድ በመሆን ዋና ዋና ሀሳቦች የትኞቹ እንደሆኑ በቃል ተነጋገሩ። ከዚያም ፅሁፉን በየግላቸው ማሳጥር ጀመሩ። እንደተለመደው ስራቸውን በመዘዋወር ለማየት እንደተሞከረው የተወሰኑ ችግሮች ታይተዋል። እነዚህም ችግሮች የቅንጫቢውን ሀሳቦች ቃል በቃል ማስፈር (በራስ አገላለፅ አለማስፈር)፣ ፅሁፉን በሀያ ቃላት ብቻ ማሳጠር (መመሪያው ከሰባ እስከ ሰማኒያ በሚደርሱ ቃላት አሳጥሩ ይላል።)፣ የፊደላት አፃፃፍ ችግር ወዘተ.

ሲሆኑ እነዚህን እንዲያስተካክሉ ተነገራቸው። በመጨረሻም የተማሪዎችን የመልስ ወረቀት በመሰብሰብ ክፍለ ጊዜው ተጠናቀቀ።

**ቀን አራት፡-** ሰኞ፣ 3/07/10 5ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 38

በዕለቱ የተማሪዎችን ወረቀት በመመለስ የሁሉም ተማሪዎች ሙከራ ጥሩ እንደሆነ እና በፅሁፋቸው ላይ ሀሳብን በራስ አገላለፅ አለማስፈር፣ ሰዋስዋዊ ስህተት፣ የሀሳቦች አደረጃጀት ወዘተ ችግሮች የታዩ ስለመሆናቸው ከተገለፀ በኋላ የእለቱ ርዕስ ቀረበ።

ይህ ክፍለ ጊዜ ቅንጫቢ ሁለት (ባለውለታ) የሚቀርብበት ነው። ስለሆነም በቅድሚያ ቅንጫቢውን ለእያንዳንዳቸው በማደል የመጀመሪያውን አንቀፅ አንብበው ስለቀረው ክፍል ግምታቸውን እንዲያስቀምጡ በማድረግ ተማሪዎች ቅድመ ንባብ ተግባር እንዲያከናውኑ ተደርጓል። ይህ ተግባር በመጀመሪያ በጥንድ እንዲወያዩ ከዚያም እድል የተሰጣቸው ጥቂት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቃል እንዲያቀርቡ በማበረታታት ተከናውኗል። በመቀጠልም ተማሪዎች ቅንጫቢውን በለሆሳስ አነበቡ።

ከዚያም ከንባብ ጊዜ ተግባራት መካከል የቅንጫቢውን ሀሳብ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ ሁለት ወይም ሶስት ጥያቄዎችን በማቅረብ በፅሁፍ እንዲመልሱ ማድረግ እንደሚቻል (Lazar 1993፣ 85) በገለፁት መሰረት የሚከተሉት ጥያቄዎች ቀርበዋል።

ሀ. አቶ ታምሩ ግርማን ያወቁት በምን ሁኔታ ነበር?

ለ. አቶ ታምሩ ለግርማ የሚልኩትን ደብዳቤ እና ገንዘብ ለምን ያቋረጡ ይመስላችኋል?

ሐ. የባእድ ወዳጅነት ሲለዩ የሚቀር፣ ሲሞቱም የመርዶ ስርዓት የሌለው ነው። የሚለውን

ሀሳብ አብራርታችሁ በፅሁፍ ግለፁ።

እነዚህን ጥያቄዎች በቃል እና በፅሁፍ ከመለሱ በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን አቶ ታምሩን እና ግርማን በመወከል የፈጠራ ምልልስ እንዲፅፉ ተነገራቸው። በድሉ (2007፣ 120) ተማሪዎች በምልልሱ ከጓደኞቻቸው ያላሰቡትን ምላሽ ስለሚያገኙ ልምምዱ አጓጊና አስደሳች ይሆናል ብለው እንደገለፁት ተማሪዎችን በመዘዋወር ለማየት እንደተሞከረው በዚህ ሁኔታ ሲፅፉ ታይተዋል።

ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ የተማሪዎች የመልስ ወረቀት ተሰበሰበ፡፡ ያልጨረሱ ጥቂት ተማሪዎች በመኖራቸው በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ አጠናቀው እንዲያመጡ ተነገራቸው፡፡ በመጨረሻም "ባነበባችሁት ልቦለድ ውስጥ አቶ ታምሩ ለግርማ ደብዳቤ እንደሚፅፉ ተገልጿል፡፡ ይህንኑ መሰረት በማድረግ አቶ ታምሩን በመወከል ደብዳቤ ፃፉ፡፡›› የሚለውን የመልመጃ ጥያቄ ሰርተው እንዲመጡ የቤት ስራ ተሰጣቸው፡፡

**ቀን አምስት፡-** ሀሙስ፣ 6/07/10 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 37

በዚህ ክፍለ ጊዜ በቅድሚያ የተከናወነው ተግባር ተማሪዎች የቤት ስራ መስራታቸውን ማረጋገጥ ነበር፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች ደብዳቤውን ፅፈው መምጣታቸውን ወረቀቱን በማሳየት የገለፁ ሲሆን ሁለት ተማሪዎች ግን ይህን አላደረጉም፡፡ ላለመያዛቸው ምክንያት ሲጠየቁ፣ አንዱ ተማሪ ረስቶት የመጣ መሆኑን ሲገልፅ ሁለተኛዋ ግን የቤት ስራ መኖሩን ስለዘነጋች አለመፃፏን ተናገረች፡፡ በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ እንዲያመጡ በማሳሰብ የተማሪዎች ወረቀት ተሰበሰበ፡፡

በቅድመ ትምህርት ፈተና እና የማስተማሩ ስራም ከተጀመረ በኋላ ተማሪዎች በፃፏቸው ልዩ ልዩ መልመጃዎች ውስጥ ከሚታዩት ችግሮች መካከል ፊደላትን በአግባቡ አለማስቀመጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ችግር ለማቃለል ይረዳ ዘንድ የፊደላትን ዝርዝር የያዘ ወረቀት በማዘጋጀት ለእያንዳንዱ ተማሪ በዚህ ዕለት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም አብዛኞቹ ተማሪዎች ደስተኛ ነበሩ፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ተግባራት ከተከናወኑ በኋላ የዕለቱ ትምህርት ተጀመረ፡፡ በቅድሚያ የዕለቱ ቅንጫቢ ርእስ  እና የትምህርቱ አላማ ቀረበ፡፡ ርዕሱ "የጳጉሜን ሶስት ገፅታ›› ሲሆን የእለቱ ትምህርት ዓላማ ደግሞ ከቅንጫቢው የወጡ ቁልፍ ዓ/ነገሮችን መነሻ በማድረግ/በመጠቀም አንድ ታሪክ መፃፍ ነው፡፡ ይህ ተግባር የተከናወነውም ቅንጫቢውን ከማንበባቸው በፊት ነው፡፡ ልምምዱ ለሀያ ደቂቃ በቡድን ከተካሄደ በኋላ ቅንጫቢውን የያዘ ወረቀት ለእያንዳንዱ ተማሪ ታደለ፡፡

በመቀጠል ተማሪዎች በየግላቸው ቅንጨቢውን በሰባት ደቂቃ ውስጥ በለሆሳስ እንዲያነቡ ስለተነገራቸው ይህንኑ አደረጉ፡፡ ከዚያም እነሱ ከፃፉት ታሪክ ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት በተመለከተ ውይይት ተካሄደ፡፡

በመጨረሻም ቅንጫቢውን በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ይዘው እንዲመጡ በማሳሰብ የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ፡፡

**ቀን ስድስት፡-** አርብ፣ 7/07/10 7ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 36

በዕለቱ ተማሪዎች ክፍለ ጊዜው አማርኛ መሆኑን በማወቀቸው "የጳጉሜን ሶስት ገፅታ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ቅንጫቢ ይዘው በመጠበቅ ላይ ነበሩ፡፡ በመሆኑም ያልያዘ ተማሪ መኖሩን በማረጋገጥ የዕለቱ ትምህርት ተጀመረ፡፡ በቅድሚያ የእለቱን ርእስ እና አላማ በማስተዋወቅ ተማሪዎች ቅንጫቢውን ለአምስት ደቂቃ እንዲያነቡ ተነገራቸው፡፡ ይህን ካደረጉ በኋላ በመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልቶችን ስለመማራቸው በማስታወስ ያነበቡት ፅሁፉ በየትኛው የማስፋፊያ ስልት እንደተፃፈ ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች የገለፃ ስልት መሆኑን ከነምክንያታቸው የገለፁ ሲሆን ጥቂት ተማሪዎች ግን የትረካ ስልት፣ የማወዳደርና የማነፃፀር ስልት በማለት መለሱ፡፡ መምህርቷ የገለፃ ስልት ያሉ ተማሪዎች ትክክል መሆናቸውን ማስረጃ በመጠቀስ ከገለፁ በኋላ ስለምንነቱ እንዲያብራሩ ለሁለት ተማሪዎች እድል ሰጡ፡፡ ተማሪዎችም የገለፃ ስልት በአንባቢ አእምሮ ምስል የሚከስት ስለመሆኑ ገለፁ፡፡ የተማሪዎችን ሙከራ በማድነቅ ተጨማሪ ነጥቦች ቀረቡ፡፡

በመቀጠልም ተማሪዎች ከቀረቡት አራት ርእሶች መካከል አንዱን በመምረጥ በገለፃ ስልት የተስፋፋ አንቀፅ እንዲገነቡ ተነገራቸው፡፡ ርዕሶቹም

ሀ) እንጦጦ ተራራ

ለ) የሸሮ ሜዳ የበዓል ገበያ

ሐ) የምወደው ሰው ቁመና

መ) አውቶቢስ ተራ የሚሉ ናቸው፡፡

አብዛኖቹ ተማሪዎች የሸሮ ሜዳ የበዓል ገበያ የሚለውን መርጠዋል፡፡ ተማሪዎች ይህን ተግባር በግላቸው የሚያከናውኑ ቢሆንም ፅሁፉን ከመጀመራቸው በፊት አንዳንድ ሀሳቦች ላይ መወያየት እንደሚችሉ ተነገራቸው፡፡ ልምምዱን በመዘዋወር ለማየት እንደተሞከረው ተማሪዎች ጥሩ እየሰሩ ነው፡፡ ነገር ግን አብዛኖቹ ተማሪዎች ሳይጨርሱ ደወል በመሰማቱ

በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ጨርሰው ይዘው እንዲመጡ ተነገራቸው፡፡ ስምምነታቸውንም በእሺታ ገለፁ፡፡

**ቀን ሰባት፡-** ሰኞ፣ 10/07/10 5ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 38

በዚህ ቀን፣ በመጀመሪያ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ ጀምረውት ነገር ግን ሳያጠናቅቁት በመቅረታቸው ለዛሬ ሰርተው እንዲመጡ የታዘዘዙትን ተግባር ይዘው ስለመምጣታቸው ሲጠየቁ አዎንታቸውን ገለፁ፡፡ ይህን ለማየት እንደተቻለው ሁሉም ተማሪዎች ሞክረው መምጣታቸው ተረጋገጠ፡፡ በመቀጠልም በዕለቱ የሚሰሩት አዲስ ርዕስ እንደሌለ ነገር ግን ቀደም ብለው የፃፏቸውን ስራዎች የማረም እና የማስተካከል ወዘተ. ስራዎች እንደሚያከናውኑ ተነገራቸው፡፡ በዚሁ መሰረት በቀን አምስት (6/07/10) የተሰበሰበው ደብዳቤ ታርሞ የመጣ በመሆኑ ለእያንዳንዳቸው ተመለሰ፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች ጋር የታዩ ዋና ዋና ችግሮችን በመጠቀስ በጋራ ውይይት ተካሄደ፡፡ ይህ ከተከናወነ በኋላ በእያንዳንዳቸው ስራ ላይ የታዩትን ችግሮች እንዲመለከቱ እና በጥንድ በጥንድ እንዲነጋገሩበት ተነገራቸው፡፡

ከዚያም የገለፃ ስልትን በመጠቀም ፅፈው የመጡትን አንቀፅ አንድ ጊዜ አንብበው እንዲያስተካክሉ (ፅሁፋቸው የሆሄ አፃፃፍ፣ የስርዓተ ነጥብ፣ የሰዋስው ስርዓት ተከትሎ መፃፉን እንዲያርሙ) ታዘዙ፡፡ ይህንን ለአስር ደቂቃ ካከናወኑ በኋላ ጥንድ ጥንድ በመሆን ስራቸውን ተቀያይረው እንዲያርሙ ተደረገ፡፡ ስለፅሁፉ ያላቸውን አስተያየት በወረቀቱ ላይ እንዲያሰፍሩም ተነገራቸው፡፡ የተማሪዎችን አስተያየት ለማየት በተደረገው ሙከራ የሚከተሉትን አስፍረዋል፡፡

- ቃላት ተደጋግመዋል፡፡
- ፅሁፉ ምስል ከሳች አይደለም፡፡
- ሀሳቡ ጥሩ ቢሆንም የእጅ ፅሁፉ አይነበብም፡፡
- እንደጥይት ተፈንጥሮ ከማለት ተስፈንጥሮ ብትለው ይሻላለል፡፡ የሚሉ አስተያየቶች ቀርበዋል፡፡

**ቀን ስምንት፦** ሀሙስ፣ 13/07/10 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 35

በዚህ ዕለት ቅንጫቢ አራት ቀርቧል፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስ ከሚከናወኑ ተግባራት መካከል ርዕሱን ተመልክተው ይዘቱ ስለምን እንደሚሆን ግምታቸውን በፅሁፍ እንዲያስቀምጡ ማድረግ ከቅድመ ንባብ ተግባራት አንዱ መሆኑን (Lazar 1993፣ 84) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ቅንጫቢው ለእያንዳንዱ ተማሪ ከተሰጠ በኂላ ርዕሱን ብቻ እንዲመለከቱ ታዘዙ፡፡ ከዚያም ግምታቸውን በፅሁፍ እንዲያሰፍሩ ተነገራቸው፡፡ ይህንንም በጥንድ አከናወኑ፡፡ ተግባሩን ሲያጠናቅቁ ሁለት ጥንድ ተማሪዎች የፃፉትን በንባብ አቀረቡ፡፡ በመቀጠልም ምንባቡን በለሆሳስ፣ በየግላቸው እንዲያነቡ በታዘዙት መሰረት በሰባት ደቂቃ አንብበው ጨረሱ፡፡ ካነበቡት ፅሁፍ ያገኙትን መረጃ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ምን ሊሆን እንደሚችል በመገመት ከ70 ባላነሱ ቃላት ቀጣዩን ታሪክ አሟልተው እንዲፅፉ ተነገራቸው፡፡ ፅሁፉን ከመጀመራቸው በፊት በሀሳቡ ላይ መወያየት ጀመሩ፡፡ የተወሰኑ ቡድኖች በሀሳቡ እርስ በርስ ያልተስማሙ ሲሆን ያልተስማሙበት ሀሳብም ቀጣዩ ታሪክ በገፀባህሪው ቁልፍ የማግኘት ሂደት ላይ ወይስ ቀጠሮው ቦታ ለመገኘት የሚያደርገው ጥረት ላይ ማተኮር አለበት የሚል ነበር፡፡ ከሁለት አንዱን መርጠው አልያም ሁለቱን ሀሳቦች አጣምረው መፃፍ እንደሚችሉ ተገለፀላቸው፡፡ ተማሪዎች የተነጋገሩበትን ሀሳብ ወደፅሁፍ በመለወጥ ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ የክፍለ ጊዜው የማጠናቀቂያ ደወል ሲደወል ሁሉም ቡድኖች ያልጨረሱ በመሆናቸው፣ አጠናቀው በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ እንዲያመጡ ስለተነገራቸው በዚሁ ተስማሙ፡፡

**ቀን ዘጠኝ፦** አርብ፣ 14/07/10 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 37

በቅድሚያ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ አጠናቀው እንዲያመጡ የተነገራቸውን የቡድን ስራ መስራታቸውን በማረጋገጥ ተሰበሰበ፡፡ ከዚያም በቀን ሰባት በተሰበሰበው ወረቀት ላይ አስተያየት በመስጠት ለተማሪዎች ተመለሰ፡፡ በተሻለ ሁኔታ የተፃፉ የአራት ተማሪዎች ስራ ተነበበላቸው፡፡ እነዚህ ፅሁፎች የተሻሉ የተባሉበት ምክንያትም በቃላት አመራረጣቸው እና በዘይቤአዊ አገላለፃቸው ምስል ከሳች በመሆናቸው እንዲሁም የአረፍተ ነገሮች ውህደት እና የስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም ጥሩ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

ፅሁፋቸው ላይ የታዩ ችግሮችን በመጥቀስ ውይይት ተካሂዷል፡፡ እነዚህም ችግሮች የቃላት ድግግሞሽ፣ የፅሁፉ ምስል ከሳች አለመሆን፣ የዓ/ነገሮች አለመዋሀድ ወዘተ ናቸው፡፡ ከአንዲት ተማሪ ፅሁፍ ውስጥ ‹‹የፊቷ ገፅታ ቀላ ያለ ነው›› እና ‹‹ጉንጮቿ ልክ እንደ ፅጌረዳ አበባ የፈካ ነው፡፡ ›› የሚሉ ዓ/ነገሮችን  በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመፃፍ ስህተቱ ምን እንደሆነ ጠቅሰው ዓ/ነገሩን አስተካክለው እንዲፅፉ ለተማሪዎች ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ ‹‹በመጀመሪያው ዓ/ነገር ገፅታ የሚለው ቃል የፊት ቀለምን አይገልፅም፡፡ ስለዚህ መልኳ ቀላ ያለ ነው፡፡ ወይም ቀይ ናት ቢባል ይሻላል፡፡ ሁለተኛው ዓ/ነገር ደግሞ ጉንጮቿ የሚለው ጉንጯ መባል አለበት፡፡ ምክንያቱም ጉንጮች ብዙ ቁጥር ሲሆን ግሱ ደግሞ ነጠላ ነው፡፡›› የሚል ምላሽ አምስት ተማሪዎች ተቀባብለው መለሱ፡፡ ሌሎች ተማሪዎችም መስማማታቸውን ገለፁ፡፡

እነዚህ ተግባራት ከተጠናቀቁ በኋላ የዕለቱ ትምህርት ርዕስ እና አላማ ቀረበ፡፡ ርእሱ "የድርሰት አፃፃፍ" ሲሆን አላማው "ርዕስ በመምረጥ እና በማጥበብ ቢጋር/አስተዋፅኦ ትነድፋላችሁ" የሚል ነው፡፡ በመቀጠልም ስለድርሰት ምንነት፣ ርዕስ አመራረጥ እና አስተዋፅኦ መንደፍ በጥያቄና መልስ፣ በውይይት አጭር ገለፃ ተሰጠ፡፡ ከዚያም የጎዳና ህይወት እና ጤንነትን መንከባከቢያ ብልሀት በሚል ርዕስ የቀረበ ቢጋር ለተማሪዎች በማደል እንዲያነቡት ተነገራቸው፡፡ ይህን ሲያጠናቅቁ በቡድን ሆነው ርዕስ በመምረጥ እና በማጥበብ ቢጋር እንዲነድፉ ተገለፀላቸው፡፡ በዚህ መሰረት ተማሪዎች ርዕስ የመምረጡን እና የማጥበቡን ተግባር ማከማወን ጀመሩ፡፡

አብዛኞቹ ቡድኖች ድርሰት ለመፃፍ የሚያስችሉ ርእሶችን መርጠዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ትምህርት ቤት፣ የውሀ ጥቅም፣ ሱስ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስና መዘዙ፣ ግብርና የሚሉት ይገኛሉ፡፡ ትምህርት ቤት እና ግብርና የሚሉ ርዕሶችን የመረጡ ቡድኖች ርእሱ ሰፊ በመሆኑ እንዲያጠቡ ተነገራቸው፡፡

ርእስ የማጥበቡን ተግባር ያጠናቀቁ ተማሪዎችም አስተዋፅኦ የመንደፍ ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ በቢጋሩ ላይ በንኡስ ርዕስነት የሚቀርቡ ሀሳቦች ድርሰቱን ሲፅፉ የሚብራሩ ሊሆኑ እንደሚገባቸው በተነገራቸው መሰረት በማስተካከል ተግባሩን ማከናወናቸውን ቀጠሉ፡፡ አብዛኞቹ ቡድኖች ስራቸውን ሳይጨርሱ የክፍለ ጊዜው ማጠናቀቂያ ደወል ተሰማ፡፡ ስለዚህም በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ ይዘውት እንዲመጡ በማሳሰብ የዕለቱ ትምህርት ተጠናቀቀ፡፡

**ቀን አስር፡-** ሰኞ፣ 17/07/10 5ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 37

በቅድሚያ ተማሪዎች ባለፈው ክፍለ ጊዜ የጀመሩትን ስራ(አስተዋፅኦ) ይዘው መምጣታቸውን ሲጠየቁ አዎንታቸውን ገለፁ፡፡ ይህንን በማረጋገጥ አስተዋፅኦውን በአስር ደቂቃ እንዲያጠናቅቁ ተገፀላቸው፡፡ በመቀጠልም ስለድርሰት ክፍሎች ያውቁ እንደሆነ ጥያቄ ቀረበላቸው በዚህ ጊዜ ለመልስ እጅ ያወጣ ተማሪ አልነበረም፡፡ በመሆኑም የድርሰት ክፍሎች ሶስት መሆናቸው ከተገለፀ በኋላ በጥያቄና መልስ በውይይት ማብራሪያ ቀረበ፡፡ በውይይቱም የተነሱ ሀሳቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ድርሰት ሶስት ክፍሎች ሲኖሩት እነሱም መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ናቸው፡፡ መግቢያ የፅሁፉን ሀተታ መሰረታዊ ቁምነገር ማስተዋወቂያ በመሆኑ ርእሰ ነገሩን ነጥሎ የሚያሳይ እና ገደቡን ወስኖ የሚስቀምጥ ነው፡፡ ሐተታ ደግሞ ርዕሱ ሰብስቦ ያካተታቸውን ፍሬ ሀሳቦች በበቂ መረጃ አዳብሮ የሚያስቀምጥ ነው፡፡ መደምደሚያ ከአንባቢ የምንሰነባበትበት የመጨረሻ የድርሰት ክፍል ሲሆን ምን ምን ጉዳዮችን እንዳነሳን፣ ስለ ጉዳዩ ያለን አተያይ ምን እንደሆነ አንባቢ ምን ማድረግ እንዳለበት የምናሰፍርበት ክፍል ነው፡፡

ከዚያም ድርሰት የመፃፉን ተግባር እንዲጀምሩ፣ ድርሰታቸውም መግቢያ ሀተታ እና መደምደሚያን ያካተተ እንዲሆን ተነገራቸው፡፡ ይህንንም የሚያከናውኑት በየግላቸው ነው፡ ፡ ርዕስ የመምረጡ እና አስተዋፅኦውን የመንደፉ ተግባር በቡድን የተከናወነ በመሆኑ ርዕሱና ንዑሳን ርዕሶች ቢመሳሰሉም ፅሁፋቸው ግን የተለያየ መሆን እንዳለበት ወይም አንዱ ከአንዱ መገልበጥ እንደሌለበት ማሳሰቢያ ተሰጣቸው፡፡ በመሆኑም አብዛኞቹ ተማሪዎች ፅሁፉን ጀምረዋል፡፡ ጥቂቶች በማሰብ ላይ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ከአጠገባቸው ከተቀመጡ ተማሪዎች ጋር ውይይት እና ክርክር ይዘዋል፡፡ ያከራከራቸው ሀሳብም በቢጋሩ ላይ የተቀመጡ ቁጥሮች በድርሰቱ ውስጥ መካተት አለባቸው ወይስ የለባቸውም የሚለው ሲሆን መካተት እንደሌለባቸው ተገለፀ፡፡ በዚህ በመስማማት ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ ከሀያ ደቂቃዎች ልምምድ በኋላ ክፍለ ጊዜው በማብቃቱ ደወለ ተደወለ፡፡ ስለዚህ በቀጣዩ ክፍለ ረቂቁን በመከለስ አስተካክለው ፅፈው እንዲመጡ ተነገራቸው፡፡

**ቀን አስራ አንድ፡-** ማክሰኞ፣ 18/07/10 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 36

የዕለቱ ተግባር የተጀመረው ተማሪዎች ድርሰቱን አጠናቀው ይዘው መምጣታቸውን በማረጋገጥ ነበር፡፡ መያዛቸውን ሲጠየቁ ሁሉም ተማሪዎች ወረቀታቸውን ጠረጴዛቸው ላይ አስቀመጡ፡፡ ለማረጋጥ በተደረገው ሙከራ ሶስት ተማሪዎች አለማምጣቸውን ተናገሩ፡ ፡ ምክንያታቸውን ሲጠየቁም ሁለቱ ረስተውት ሲሆን አንዱ ተማሪ ደግሞ ባለፈው ክፍለ ጊዜ አለመኖሩን ገለፀ፡፡ በመሆኑም በቀጣዩ ክፍለ ጊዜ እንዲያመጡ ተነገራቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው እንዲቀመጡ በመንገር የእለቱ ስራ የቢጤ እርማት ማካሄድ እንደሆነ ተገለፀ፡፡ ከዚያም የፅህፈት ስራዎች ማረሚያ መስፈርት ለእያንዳንዳቸው ተሰጠ፡፡ ይህንን ለአምስት ደቂቃዎች ካነበቡ በኋላ ፅሁፉን ተለዋውጠው በመስፈርቱ መሰረት በማረም አስተያየት እንዲፅፉበት ታዘዙ፡፡ ድርሰቱን ያላመጡ ተማሪዎች ደግሞ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን እንዲያርሙ ተደረገ፡፡

ሁሉም ተማሪዎች ድርሰቱን ማንበብ ጀምረዋል፡፡ ንባቡን ካጠናቀቁ በኋላ መስፈርቱን መሰረት በማድረግ ወደማረሙ ተግባር ገቡ፡፡ ተማሪዎች በሚያርሙት ወረቀት ላይ አስተያየታቸውን በማስፈር ላይ ናቸው፡፡ ሁለት ተማሪዎች በመከራከር ላይ ሲሆኑ የሚከራከሩትም የተሰጠኝ አስተያየት ትክክል አይደለም በሚል ነው፡፡ የተሰጣቸው አስተያየት ላይ የመወያያ ጊዜ እንደሚኖር፣ አሁን ግን የማረሙን ስራ እንዲቀጥሉ ተነገራቸው፡፡ ተማሪዎች የሚከተሉትን አስተያየቶች አስፍረዋል፡፡

- የአደረጃጀት ችግር ይታይበታል፡፡ ማለትም በመደምደሚያ መስፈር ያለበት ሀሳብ በመግቢያ ላይ ሰፍሯል፡፡ ስለዚህ ይስተካከል፡፡
- ፊደላት በአግባቡ አልተፃፉም፡፡ ለምሳሌ አልኮን ሳይሆን አልኮል መባል ነበረበት፡፡
- ስርዝ ድልዝ በዝቷል፡፡
- መግቢያና መደምደሚያ መኖሩ ጥሩ ነው፡፡
- በቂ ማብራሪያ የለውም፡፡ (አባሪ አስራ ሁለትን በገፅ 126 ይመልከቱ)

በመጨረሻም ፅሁፉን ተለዋውጠው የተሰጣቸውን አስተያየት እንዲመለከቱና እንዲወያዩበት ታዘዙ፡፡ ይህንንም ለአስር ደቂቃዎች ካከናወኑ በኋላ ወረቀቱ ተሰበሰበ፡፡ ክፍለ ጊዜው በመጠናቀቁ ወይዘሮ አትጠገብ ማን ናቸው?፣ የማልረሳው ዕለት እና እናት

ከሚሉ ርዕሶች መካከል አንዱን መርጠው በየግላቸው ድርሰት ፅፈው እንዲመጡ የቤት ስራ ተሰጣቸው፡፡

**ቀን አስራ ሁለት፡-** ሀሙስ፣ 20/07/10 4ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 38

በዚህ ክፍለ ጊዜ የመጨረሻው ቅንጫቢ (ቅንጫቢ አምስት) ቀርቧል፡፡ በቅድሚያ ለተማሪዎች ቅንጫቢው ታደለ፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት ለመቀስቀስ ማንበበብ ከመጀመራቸው በፊት ቅድመ ንባብ ተግባራት ተከናወኑ፡፡ ቅድመ ንባብ ተግባሩም ርዕሱን ተመልክተው ታሪኩን እንዲተነብዩ የቀረበ ነው፡፡ ይህንንም በጥንድ አከናወኑ፡፡ ርዕሱ "የጠፋ ሲገኝ" ሲሆን ከደቂቃዎች ውይይት በኋላ ሀሳባቸውን ለክፍሉ እንዲያቀርቡ ለሶስት ተማሪዎች እድል ተሰጠ፡፡ የመጀመሪያው ተማሪ "አንድ ሰው የጠፋበትን እቃ በብዙ ውጣ ውረድ ያገኛል" አለ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ "የጠፋችው ገፀባህሪ ትገኛለች" ሲል ሶስተኛዋ ተማሪ "አንድ ሰው የጠፋበትን ነገር ሲያገኝ የሚኖረውን ደስታ ያሳያል" በማለት ገለፀች፡፡ ሙከራቸውን በማድነቅ ቅንጫቢውን በየግላቸው በለሆሳስ እንዲያነቡ ታዘዙ፡፡ ይህንንም ለሰባት ደቂቃዎች ካከናወኑ በኋላ በቡድናቸው እንዲቀመጡ ተነገራቸው፡፡ ባነበባችሁት ቅንጫቢ ላይ ከተነጋገራችሁ በኋላ ምዕራፍ ዜሮን ፃፉ (ቀደም ብሎ የተፈፀመውን ድርጊት የሚያሳይ ታሪክ ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡) የሚለውን መልመጃ በቡድን እንዲሰሩ ተነገራቸው፡፡ የፅሁፍ ስራውን ከመጀመራቸው በፊት ሃሳቡ ላይ ውይይት አደረጉ፡፡ ውይይታቸውም ደመቅ ያለ ሲሆን ድምፃቸው ከፍ ብሎ ይሰማል፡፡ በዚህም መማሪያ ክፈሉ እንዳይረበሽ ድምፃቸውን እንዲቀንሱ ተነገራቸው፡፡ አብዛኞቹ ቡድኖች የተስማሙበትን ሀሳብ በማስፈር ላይ ናቸው፡፡ በመጨረሻም ከሀያ አምስት ደቂቃዎች ልምምድ በኋላ የጨረሱ ተማሪዎች ወረቀት ተሰበሰበ፡፡ የጨረሱት ቡድኖች አምስት ሲሆኑ ሁለቱ በቀጣይ ክፍለ ጊዜ እንዲያመጡ ታዘዙ፡፡ እንዲሁም በቀን አስራ አንድ(18/07/10) ድርሰት እንዲፅፉ የተሰጣቸው የቤት ስራ ተሰበሰበ፡፡ የእለቱ ትምህርት በዚሁ ተጠናቀቀ፡፡

**ቀን አስራ ሶስት፡-** አርብ፣ 21/07/10 7ኛ ክፍለ ጊዜ

የተማሪዎች ብዛት 36

ይህ ዕለት የመጨረሻው የማስተማር ስራ የተከናወነበት ቀን ነው፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎች ይህንኑ በማሳወቅ፣ በቅድሚያ በግል እና በቡድ በፃፏቸው ፅሁፎች ላይ

መሻሻል የታየ መሆኑ ሲገለፅላቸው አብዛኞቹ ተማሪዎች ፊት ላይ የደስታ ስሜት ይነበባል፡፡ ከዚያም የታረመውን ድርሰት በመመለስ አስተያየቱ ላይ በጥንድ በጥንድ ተወያዩ፡፡ በመቀጠልም ምዕራፍ ዜሮን እንዲያሚሉ በቡድን የተሰጣቸው ተግባር ለተማሪዎች ተመልሶ፣ በየቡድናቸው አስተያየቱ ላይ ውይይት ተካሄደ፡፡ በእለቱ ሳያጠናቅቁ የቀሩ ሁለት ቡድኖች ደግሞ ፅሁፉን ተለዋውጠው የቢጤ እርማት አከናወኑ፡፡ እነዚህን ተግባራት ለሀያ ደቂቃ ካከናወኑ በኂላ ወደ እለቱ ስራ ተሸጋገሩ፡፡ ተግባሩ የጠቢቡን ቤተሰብ (የጠፋ ሲገኝ በሚል ርዕስ በቀረበው ቅንጫቢ የጠፋውን ገፀባህሪ ቤተሰቦች) በመወከል የአፋልጉኝ ማስታወቂያ እንዲፅፉ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በቡድን በመሆን ተግባሩን ማከናወን ጀመሩ፡፡ ሁሉም ተማሪዎች በንቃት በመሳተፍ ላይ ናቸው፡፡ አንዲት ተማሪ ጥያቄ አቀረበች፡፡ ጥያቄምም "የጠቢቡ እድሜ በቅንጫቢው ያልተገለፀ በመሆኑ በማስታወቂው ላይ እድሜውን ስንት እንበል?" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ እድሜውን፣ ልብሱን፣ ቁመቱን፣ መልኩን ወዘተ ለመግለፅ ቅንጫቢውን መነሻ በማድረግ ገምተው እንዲያስቀምጡ ለሁሉም ተማሪዎች ተነገራቸው፡፡ የጨረሱ ተማሪዎች እንዲታረምላቸው ጠየቁ፡፡ ፅሁፉ አጭር በመሆኑ የሁለት ቡድኖች ስራ እዚያው ክፍል ውስጥ ታርሞ ተመለሰላቸው፡፡ በመጨረሻም የሌሎች ቡድኖች ወረቀት ተሰበሰበ፡፡ በረጅም ልቦለድ አማካይነት የመፃፍ ክሂልን የማለማመዱ ሂደትም በዚሁ ተጠናቀቀ፡፡

# አባሪ ሶስት

## የምልከታ ቅፅ (check list)

1. የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎች በክፍል ውስጥ እንዴት ቀረቡ?
2. ለትምህርት የቀረቡ ቅንጫቢዎች ከሌሎች ክሂሎች በይበልጥ የመጻፍ ክህሎትን ለማለማመድ አስችለዋል?
3. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተግባራቱን በንቁ ተሳታፊነት አከናውነዋል?
4. የቤት ስራዎችን እና የክፍል ስራዎችን በአግባቡ እና በወቅቱ ይሰራሉ?
5. ተማሪዎች ቅንጫቢዎችን የሚያነቡት በፍላጎት እና በራስ ተነሳሽነት ነው?
6. ተማሪዎች ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ? የተጠየቁትንስ ይመልሳሉ?
7. በጥንድ እና በቡድን የሚከናወኑ ተግባራት የተማሪዎችን የመፃፍ ክህሎት ለማሻሻል አስተዋፅኦ አላቸው?
8. ፅሁፋቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር በመለዋወጥ አስተያየት ሰጥተዋል? ተቀብለዋል?
9. ከመምህርቷ እና ከጓደኞቻቸው የሚሰጣቸውን አስተያየት ተቀብለው ፅሁፉን አስተካክለው ፅፈዋል?
10. በተማሪዎች የመፃፍ ልምምድ ላይ ጎልተው የሚታዩ ችግሮች/ስህተቶች የትኞቹ ናቸው?
11. ተማሪዎች ድርሰት በመጻፍ ሂደት ርእስ የመምረጥ፣ የማጥበብ፣ ረቂቁን የመፃፍ እና የመከለሱን ተግባር በአግባቡ አከናውነዋል?
12. የተማሪዎች ፅሁፍ መሻሻል አሳይቷል?

# አባሪ አራት

## ለሙከራ እና ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተዘጋጀ

## ቅድመ ትምህርት ፈተና

***መመሪያ*** **፡-** ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ የአንቀፅ ማስፋፊያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ አንድ አንቀፅ ፃፉ፡፡

1. መጥፎ አጋጣሚ
2. የቤተሰብ ሞት
3. የምግብ እጥረት
4. የትምህርት ፍቅር
5. የቤተሰብ ፍቅር

## ለሙከራ እና ለቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች የተዘጋጀ

## ድህረ ትምህርት ፈተና

***መመሪያ፡-*** ከሚከተሉት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ ከአንድ ገፅ ያልበለጠ ድርሰት ፃፉ፡፡

1. የትውልድ አካባቢዬ መልከዓ ምድራዊ ውበት
2. የትምህርት እርምጃዬ እና የቤተሰቦቼ አዎንታዊ ድርሻ
3. የፈተና ወቅት
4. ጎጂ ልማድ
5. የምኖርበት ከተማ
6. የትምህርት ቤት ትዝታዬ
7. የተፈጥሮ አደጋዎች
8. አረጋውያንን መንከባከብ

# አባሪ አምስት

## ቅድመ ትምህርት ሀ

| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | /x-mean/ | /x-mean/ square | አራሚ ሁለት | /x-mean/ | /x-mean/ square | አራሚ ሶስት | /x-mean/ | (x-mean) squaer | አማካይ ውጤት | /x-mean | /x-mean/ square |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01ሀ | 34 | 7.9 | 62.4 | 44 | 0.9 | 0.81 | 42 | 5 | 25 | 40 | 4 | 16 |
| 02ሀ | 48 | 6.1 | 37.2 | 48 | 4.9 | 24.01 | 44 | 3 | 9 | 46.67 | 2.67 | 7.111 |
| 03ሀ | 26 | 15.9 | 253 | 22 | 21.1 | 445.2 | 30 | 17 | 289 | 26 | 18 | 324 |
| 04ሀ | 38 | 3.9 | 15.2 | 46 | 2.9 | 8.41 | 48 | 1 | 1 | 44 | 0 | 0 |
| 05ሀ | 56 | 14.1 | 199 | 66 | 22.9 | 524.4 | 50 | 3 | 9 | 57.33 | 13.3 | 177.8 |
| 06ሀ | 46 | 4.1 | 16.8 | 34 | 9.1 | 82.81 | 38 | 9 | 81 | 39.33 | 4.67 | 21.78 |
| 07ሀ | 46 | 4.1 | 16.8 | 54 | 10.9 | 118.8 | 50 | 3 | 9 | 50 | 6 | 36 |
| 08ሀ | 34 | 7.9 | 62.4 | 46 | 2.9 | 8.41 | 38 | 9 | 81 | 39.33 | 4.67 | 21.78 |
| 09ሀ | 50 | 8.1 | 65.6 | 60 | 16.9 | 285.6 | 62 | 15 | 225 | 57.33 | 13.3 | 177.8 |
| 10ሀ | 46 | 4.1 | 16.8 | 54 | 10.9 | 118.8 | 54 | 7 | 49 | 51.33 | 7.33 | 53.78 |
| 11ሀ | 52 | 10.1 | 102 | 64 | 20.9 | 436.8 | 58 | 11 | 121 | 58 | 14 | 196 |
| 12ሀ | 48 | 6.1 | 37.2 | 38 | 5.1 | 26.01 | 48 | 1 | 1 | 44.67 | 0.67 | 0.444 |
| 13ሀ | 48 | 6.1 | 37.2 | 40 | 3.1 | 9.61 | 38 | 9 | 81 | 42 | 2 | 4 |
| 14ሀ | 42 | 0.1 | 0.01 | 40 | 3.1 | 9.61 | 46 | 1 | 1 | 42.67 | 1.33 | 1.778 |
| 15ሀ | 20 | 21.9 | 480 | 10 | 33.1 | 1096 | 18 | 29 | 841 | 16 | 28 | 784 |
| 16ሀ | 26 | 15.9 | 253 | 24 | 19.1 | 364.8 | 22 | 25 | 625 | 24 | 20 | 400 |
| 17ሀ | 50 | 8.1 | 65.6 | 48 | 4.9 | 24.01 | 54 | 7 | 49 | 50.67 | 6.67 | 44.44 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 18ሀ | 44 | 2.1 | 4.41 | 38 | 5.1 | 26.01 | 44 | 3 | 9 | 42 | 2 | 4 |
| 19ሀ | 40 | 1.9 | 3.61 | 38 | 5.1 | 26.01 | 52 | 5 | 25 | 43.33 | 0.67 | 0.444 |
| 20ሀ | 50 | 8.1 | 65.6 | 48 | 4.9 | 24.01 | 62 | 15 | 225 | 53.33 | 9.33 | 87.11 |
| 21ሀ | 64 | 22.1 | 488 | 56 | 12.9 | 166.4 | 54 | 7 | 49 | 58 | 14 | 196 |
| 22ሀ | 66 | 24.1 | 581 | 68 | 24.9 | 620 | 74 | 27 | 729 | 69.33 | 25.3 | 641.8 |
| 23ሀ | 44 | 2.1 | 4.41 | 48 | 4.9 | 24.01 | 46 | 1 | 1 | 46 | 2 | 4 |
| 24ሀ | 30 | 11.9 | 142 | 38 | 5.1 | 26.01 | 56 | 9 | 81 | 41.33 | 2.67 | 7.111 |
| 25ሀ | 30 | 11.9 | 142 | 26 | 17.1 | 292.4 | 38 | 9 | 81 | 31.33 | 12.7 | 160.4 |
| 26ሀ | 34 | 7.9 | 62.4 | 24 | 19.1 | 364.8 | 32 | 15 | 225 | 30 | 14 | 196 |
| 27ሀ | 46 | 4.1 | 16.8 | 44 | 0.9 | 0.81 | 52 | 5 | 25 | 47.33 | 3.33 | 11.11 |
| 28ሀ | 44 | 2.1 | 4.41 | 54 | 10.9 | 118.8 | 48 | 1 | 1 | 48.67 | 4.67 | 21.78 |
| 29ሀ | 46 | 4.1 | 16.8 | 40 | 3.1 | 9.61 | 48 | 1 | 1 | 44.67 | 0.67 | 0.444 |
| 30ሀ | 44 | 2.1 | 4.41 | 52 | 8.9 | 79.21 | 50 | 3 | 9 | 48.67 | 4.67 | 21.78 |
| 31ሀ | 50 | 8.1 | 65.6 | 62 | 18.9 | 357.2 | 60 | 13 | 169 | 57.33 | 13.3 | 177.8 |
| 32ሀ | 38 | 3.9 | 15.2 | 48 | 4.9 | 24.01 | 56 | 9 | 81 | 47.33 | 3.33 | 11.11 |
| 33ሀ | 30 | 11.9 | 142 | 22 | 21.1 | 445.2 | 38 | 9 | 81 | 30 | 14 | 196 |
| 34ሀ | 54 | 12.1 | 146 | 70 | 26.9 | 723.6 | 72 | 25 | 625 | 65.33 | 21.3 | 455.1 |
| 35ሀ | 32 | 9.9 | 98 | 28 | 15.1 | 228 | 44 | 3 | 9 | 34.67 | 9.33 | 87.11 |
| 36ሀ | 14 | 27.9 | 778 | 10 | 33.1 | 1096 | 26 | 21 | 441 | 16.67 | 27.3 | 747.1 |
| ድምር | 1510 | 323 | 4500 | 1552 | | 8236 | 1692 | | 5364 | 1585 | | 5293 |
| አማካይ | 41.9 | | | 43.1 | | | 47 | | | 44 | | |
| ልይይት | | | 129 | | | 235.3 | | | 153.3 | | | 151.2 |
| መደበኛ ልይይት | | | 11.3 | | | 15.33 | | | 12.37 | | | 12.29 |

## ቅድመ ትምህርት ለ

| መለያ ቁጥር | አራሚ አንድ | /x-mean/ | /x-mean/ square | አራሚ ሁለት | /x-mean/ | /x-mean/ square | አራሚ ሶስት | x-mean | (x-mean) square | አማካይ ውጤት | /x-mean/ | /x-mean/ square |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 01ለ | 52 | 10.9 | 119 | 58 | 18.9 | 356 | 60 | 12.7 | 161.9 | 56.7 | 14.2 | 200.43 |
| 02ለ | 30 | 11.1 | 123 | 32 | 7.14 | 51 | 44 | 3.28 | 10.74 | 35.3 | 7.18 | 51.494 |
| 03ለ | 44 | 2.89 | 8.35 | 34 | 5.14 | 26.4 | 40 | 7.28 | 52.97 | 39.3 | 3.18 | 10.087 |
| 04ለ | 40 | 1.11 | 1.23 | 52 | 12.86 | 165 | 48 | 0.72 | 0.522 | 46.7 | 4.16 | 17.284 |
| 05ለ | 48 | 6.89 | 47.5 | 52 | 12.86 | 165 | 46 | 1.28 | 1.633 | 48.7 | 6.16 | 37.914 |
| 06ለ | 42 | 0.89 | 0.79 | 40 | 0.861 | 0.74 | 58 | 10.7 | 115 | 46.7 | 4.16 | 17.284 |
| 07ለ | 36 | 5.11 | 26.1 | 34 | 5.139 | 26.4 | 46 | 1.28 | 1.633 | 38.7 | 3.84 | 14.766 |
| 08ለ | 38 | 3.11 | 9.68 | 42 | 2.861 | 8.19 | 36 | 11.3 | 127.2 | 38.7 | 3.84 | 14.766 |
| 09ለ | 30 | 11.1 | 123 | 21 | 18.14 | 329 | 32 | 15.3 | 233.4 | 27.7 | 14.8 | 220.3 |
| 10ለ | 48 | 6.89 | 47.5 | 52 | 12.86 | 165 | 46 | 1.28 | 1.633 | 48.7 | 6.16 | 37.914 |
| 11ለ | 44 | 2.89 | 8.35 | 42 | 2.861 | 8.19 | 52 | 4.72 | 22.3 | 46 | 3.49 | 12.185 |
| 12ለ | 46 | 4.89 | 23.9 | 48 | 8.861 | 78.5 | 60 | 12.8 | 163 | 51.3 | 8.82 | 77.864 |
| 13ለ | 38 | 3.11 | 9.68 | 34 | 5.139 | 26.4 | 54 | 6.72 | 45.19 | 42 | 0.51 | 0.2593 |
| 14ለ | 34 | 7.11 | 50.6 | 40 | 0.861 | 0.74 | 42 | 5.28 | 27.85 | 38.7 | 3.84 | 14.766 |
| 15ለ | 44 | 2.89 | 8.35 | 42 | 2.861 | 8.19 | 52 | 4.72 | 22.3 | 46 | 3.49 | 12.185 |
| 16ለ | 34 | 7.11 | 50.6 | 22 | 17.14 | 294 | 38 | 9.28 | 86.08 | 31.3 | 11.2 | 124.9 |
| 17ለ | 50 | 8.89 | 79 | 46 | 6.861 | 47.1 | 52 | 4.72 | 22.3 | 49.3 | 6.82 | 46.568 |
| 18ለ | 46 | 4.89 | 23.9 | 48 | 8.861 | 78.5 | 60 | 12.7 | 161.9 | 51.3 | 8.82 | 77.864 |
| 19ለ | 16 | 25.1 | 631 | 8 | 31.14 | 970 | 22 | 25.3 | 639 | 15.3 | 27.2 | 738.53 |
| 20ለ | 32 | 9.11 | 83 | 32 | 7.139 | 51 | 46 | 1.28 | 1.633 | 36.7 | 5.84 | 34.136 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21ለ | 58 | 16.9 | 285 | 52 | 12.86 | 165 | 62 | 14.7 | 216.7 | 57.3 | 14.8 | 219.75 |
| 22ለ | 56 | 14.9 | 222 | 48 | 8.861 | 78.5 | 60 | 12.7 | 161.9 | 54.7 | 12.2 | 147.8 |
| 23ለ | 58 | 16.9 | 285 | 44 | 4.861 | 23.6 | 55 | 7.42 | 55.01 | 52.3 | 9.72 | 94.522 |
| 24ለ | 36 | 5.11 | 26.1 | 32 | 7.139 | 51 | 44 | -3.6 | 12.84 | 37.3 | 5.18 | 26.79 |
| 25ለ | 36 | 5.11 | 26.1 | 42 | 2.861 | 8.19 | 48 | 0.42 | 0.174 | 42 | 0.51 | 0.2593 |
| 26ለ | 34 | 7.11 | 50.6 | 30 | 9.139 | 83.5 | 46 | 1.28 | 1.633 | 36.7 | 5.84 | 34.136 |
